# የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

## ከሐዋሪያው ዮሐንስ እስከ ዮሐንስ ሁስ (100-1400 ዓ.ም.)

## የቤተ ክርስቲያን ታሪክ
## መግቢያ

የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ አጀማመር ማወቅ የሚፍልጉ ሰዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኘውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ህይወትና የጳውሎስን እሏሏር ማጥናት አለባቸው። ከኢየሱስ ዕርገት በኋላ የግሪክ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑና የግሪክን ባህል የተቀበሉ ከእስራኤል አገር ውጪ የሚኖሩ አይሁድ ወንጌልን መቀበል ጀመሩ። ከእነዚህ አይሁድ መካከል ሁለቱ ለአህዛብ ታላቅ ምስክሮች የሆኑት የቆጵሮሱ በርናባስና የጠርሴሱ ሳውል ነበሩ። ብዙ ሳይቆይ የክርስትና እምነት ከኢየሩሳሌም ተነሥቶ በምሥራቅ እስከ ህንድና በምዕራብ እስከ ስፔን ተሰራጨ። በሮማዊያን ዘመን የመገናኛ መንገዶች በባህርም ሆነ በምድር ብዙ ችግር ስላልነበራቸው የወንጌልን መልዕክት ይዘው የሚሄዱ ሰዎች ተጠቅመውባቸዋል።

የብዙ አህዛብ ማመን ወዲያው በርካታ አሻሚ ጥያቄዎች ፈጠረ። ለምሳሌ አዲስ አማኞች ከሙሴ ሥርዓቶች ጋር የተቀራኙት እንዴት ነበር? የአይሁድ ወግ አጥባቂዎች አዲስ ያመኑት ሰዎች እንዲገረዙ ፈልገው ነበር። ይሁን እንጂ ጳውሎስ እነዚህን ወግ አጥባቂዎች በጣም ተቃዋውሟቸዋል። የሐዋ 15 በሚነግረን መሠረት ይህ ችግር በአጠቃላይ በ49 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም በተሰበሰበው ጉባዔው ውሳኔዎችን ቢያስተላልፍም እንኳ ይህ ችግር በጳውሎስ አገልግሎት ውስጥ ሁሉ ለብዙ ዓመታት አልተወገደም።

ክርስቶስ "አገልጋይ ከጌታው አይበልጥም . . . እኔን አሳድውኝ እንደሆኑ እናንተንም ደግሞ ያሳድዷችኋል።" በማለት ደቀ መዛሙርቱን አስጠንቅቋቸዋል። ቀደም ብለው ክርስቲያኖችን ያሳደዱት ሮማዊያን ሳይሆኑ አይሁድ ነበሩ። በመጀመሪያ ላይ የሮም መንግሥት በክርስትያኖችና በአይሁድ መካከል ያለውን ልዩነት በጉልህ አላወቁም ነበር። ይሁን እንጂ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ከተገደለ በኋላ ማለትም በጳውሎስ የህይወት ዘመን ሁሉ የአይሁድ ወግ አጥባቂዎች ወንጌልን ክፉኛ ተቃውመዋል።

በሮማው ቄሳር በኔሮ ዘመን መንግሥት ከ62-68 ዓ.ም. በክርስቲያኖች ላይ ይደረግ የነበረው ስደት በጣም የከፋ ነበር። ከዚያም በእስራኤል የነበሩ አይሁድ በሮም ላይ ብዙ ችግር ስለ ፈጠሩ ሮማዊያን ያለ ርህራሄ ቀጧቸው። ይህ ችግር የተፈጠረው በክርስትያኖች ሳይሆን አገራቸውን ከሮማዊያን ነፃ ለማውጣት በሚፈልጉ ቀናተኞች በተባሉ የአይሁድ ብሔራዊ ነፃ አውጭ ቡድን አባላት ነበር።

በዚያ ዘመን የሮማዊያን አስተዳደር በጣም የተግማማ ስለነበር ቀናተኞቹ አገራቸውን ነፃ ለማውጣት እንዲጥሩ መንገድ ሰጥቷቸዋል። በትግሉ ባለመተባበራቸው ክርስቲያኖች በቀናተኞቹም ሆነ በሮማዊያን ይጠሉ ነበር።

ቀናተኞቹ በ66 ዓ.ም. የሮማዊያንን ወታደሮች በገደሉበት ወቅት በመካከላቸው ግጭት ይጀምራል። ከአራት ዓመታት በኋላ ቲቶ የተባለው የሮማ ቄሳር ኢየሩሳሌምን ድል አድርጎ አቃጥሏታል።

ክርስቲያኖች ክርስቶስ በማቴ 24፡15-16 ውስጥ የሰጠውን ማስጠንቀቂያ በማስታወስ ዮርዳኖስን ተሻግረው ፔላ ወደተባለው ሥፍራ በመሸሽ አምልጠዋል። አስከፊው የኢየሩሳሌም ወረራ በፋሲካ አካባቢ ተጀምሮ እስከ መስከረም ድረስ ቆይቷል፣ በመጨረሻም ቤተ መቅደሱ ተደምስሶ ኢየሩሳሌም ከተማ ተቃጥላለች። በጦርነቱ ወቅት ከተማይቱ የፋሲካን በዓል ሊያከብሩ ከተለያዩ ሥፍራዎች በሚመጡ አይሁድ የተጥለቀለቀች ነበረች።

ቤተ መቅደሱ በመደምሰሱ የካህናት አገልግሎት እንዲሁም የሥራዓቶችና የበዓላት መከበር ሁሉ እንዳለ ወድሟል። ክርስቶስ በሞቱ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን የተሻለ መንፈሳዊ አምልኮ አስገኝቷል።

የጥንት ቤተ ክርስቲያን አምልኮ ከቤተ መቅደስ ሥነ-ሥርዓት ይልቅ የምኩራብ አገልግሎትን ይመስል ነበር። እነዚህ ክርስቲያኖች መሰብሰቢያ ሕንጻዎች ባይኖሯቸውም ከሮማዊያንም ግዛት ብዙ ተቃውሞ የደረሰባቸውና በአራማዊዎችም ደግሞ የተጠሉ ቢሆኑም እንኳ ቤተ ክርስቲያን ታድግና ወንጌልም ይሰራጭ ነበር።

## ምዕራፍ አንድ - ሁለተኛው ምዕተ ዓመት

ከሐዋሪያት መካከል በመጨረሻ የሞተው ዮሐንስ ሳይሆን አይቀርም። ዶምጥያን የተባለው የሮማ ቄሳር ባስነሳው ስደት ሳቢያ ዮሐንስ ራዕዩን በተቀበለበትና በፃፈበት ፍጥሞ በተባለው ሥፋራ በግዞት ላይ ነበር። ሐዋርያው ዮሐንስ የሞተው ምናልባት በ2ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ በኤፌሶን ይሆን ይሆናል።

በ2ኛው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያ ሰባ ዓመታት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን የተግባር እንቅስቃሴዎች በጉልህ አይታወቁም። ክሌመንት የተባለው የሮማ ጳጳስ ችግር መነሣቱን ሐዋሪያት ያውቁ ስለነበር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማለት ጳጳሳትን ዲያቆናትን ሊሾሙ አቅደዋል በማለት ድፏል። ሆኖም እነዚህ አዲስ መሪዎች ጠንካራ መንፈሳዊ መሪዎች አልነበሩም። ጽሑፎቻቸውም በአዲስ ኪዳን ጥራዝ ውስጥ ካሉት ጽሑፎች ጋር የሚስተካከል ጥራት የላቸውም።

## የሁለተኛው ምዕተ ዓመት ጸሐፊዎችና ጽሑፎቻቸው

የቤተ ክርስቲያን አባቶች ብለን የምንጠራቸው ሰዎች ከጻፏቸው የሁለተኛው ምዕተ ዓመት ጽሑፎች መካከል ጥንታዊ የሆነው የክሊመንት መልዕክት የተሰኘው ጽሑፍ ሳይሆን አይቀርም። ይህ ጽሑፍ በ96 ዓ.ም. ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ነበር። በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ምናልባት በጳውሎስ ዘመንም እንኳ ከነበረው የበለጠ መከፋፈል ነበር።

ከአንድ መቶ ዓመታት በኋላ ኢራኒዮስ የተባለው ሰው ክሌመንት ሦስተኛው የሮም ጳጳስ መሆኑን ጽፏል። ይሁንና ክሌመንት ራሱ ይህንን ነገር በጽሑፎቹ ውስጥ አልጠቀሰም። ክሌመንት የጠቀሰው ራሱ ያገለገለበትን ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበር። በኋላ የሮም ቤተ ክርስቲያን የኛ ጳጳስ ከሌሎች ቀደምትነት አለው ብላ ብታስተምርም በክሌመንት ዘመን ጳጳስና ሽማግሌ በተሰኘው ቃላት መካከል ምንም ልዩነት አልነበረም። የአዲስ ኪዳንም አጠቃቀም እንዲሁ ነው።

በረጅሙ መልዕክቱም ውስጥ ክሌመንት በተደጋጋሚ መጽሐፍ ቅዱስን ይጠቅሳል። ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳንን በተለይም የጳውሎስ መልዕክቶችን ይጠቅሳል። የቆሮንቶስ ክርስትያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓትና አንድነት እንዲጠብቁ ለምኗቸዋል። በትክክለኛው መንገድ ከሐዋሪያት ቀጥለው በሥልጣን ላይ የተቀመጡትን መሪዎች እነርሱ ስላልሾሟቸው ብቻ ከሥልጣን አውርደዋቸው ነበር። ይሁንና ክሌመንት በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ከትምህርተ ክርስትና ፈቀቅ ያለ አስተሳሰብ አላገኘም። ክሌመንት ከኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ያሉትን የአርባ ቀናት ድርጊቶች በትክክል ሊያስተላልፉ የሚችሉት በጴጥሮስና በጳውሎስ የተሾሙት መሪዎች ናቸው ብሎ ያምን ነበር። በዚህም ወቅት ወንጌሎች በሙሉ የተጻፉ ቢሆንም እንኳ ገና በአፍ የሚተላለፉ አንዳንድ የጌታ ንግግሮች ነበሩ። በርናባስ የተባለው በ132 ዓ.ም. አካባቢ ይጽፍ የነበረ ጸሐፊ ነው። ጽሑፎቹ በሐዋሪያትና በነቢያት የተሰጠውን ቃል አይከተሉም ነበር። በርናባስ ስለ ሙሴ ሕግ ከእውነት የራቁ ነገሮችን ጽፏል። ሔርማስ የተባለው የእግዚአብሔርን ቃል የማይከተሉ ብዙ እንግዳ ሐሳቦችን የጻፈ ሌላው ጸሐፊ ነው።

በ140-150 ዓ.ም. ውስጥ "እረኛ" የተባለውን ጽሑፍ ጽፏል። በጥምቀት አማካይነት የኃጢአት ይቅርታ እንደሚገኝ ጠቁሟል። በተጨማሪ ያምንና ከሥጋዊ ፍላጎቶች መገለልን በሚመለከት ትኩረት አድርጓል።

ይህም በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ትኩረት የማያደርግና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጥምቀት ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር የማይስማማ ነበር።

## የአንፆኪያ ጳጳስ ኢግናጢዮስ

ኢግናጢዮስ ከ110-117 ዓ.ም. ወደ ሮም በመጓዝ ላይ ሳለ ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ሰባት መልዕክቶችን ጽፏል። መልዕክቶቹም የሚያተኩሩት በሰርየት በኢየሱስ ልደት በአይሁድ እምነትና በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ነበር። የጳጳሱን ሥልጣን የሐሰት ትምህርትን ለመዋጋት ዓይነተኛው መንገድ እርሱን መታዘዝ እንደሆነ አጠንክሮ ተናግሯል። ጳጳሱ ተቃውሞ የሌለበት ሥልጣን እንዲኖረው እና እንደ እግዚአብሔር ወኪል እንዲታይ ይፈልግ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እንደ እግዚአብሔር ጉባዔና የሐዋሪያት ባልደረባ ተደርገው እንዲቆጠሩ ፈልጓል። ይሁንና የኢግናጢዮስ ሰባት ደብዳቤዎች የተጻፉት ለቤተ ክርስቲያን እንጂ ለጳጳሳት አልነበረም። ለሮም እንኳ ሲጽፍ በዚያ ከሚገኙት ሽማግሌዎች ለአንዱ ልዩ ማዕረግ የተሰጠ መሆኑን አልጠቀሰም።

## የሰምርኔሱ ፓሊካርፕ

ፓሊካርፐ ከሁለተኛው ምዕተ ዓመት የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሰማዕታት መሐከል እጅግ ታዋቂ የሆነው ነው። የሐዋሪያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ነበር። በ156 ዓ.ም. ከግንድ ጋር ታስሮ ሲቃጠል የ86 ዓመት ሰው ነበር። ሐዋሪያው ዮሐንስም በሞተበት ወቅት 30 ዓመት ሳይሞላው አይቀርም።

ፓሊካርፐ ንፁህ እምነትና አፍቃሪ ልብ የነበርው መሆኑ ይነገርለታል። የእርሱ ተማሪ የነበርው ኢሬኒዮስ ፓሊካርፐ ዘውትር የሐዋሪያትን በተለይም የዮሐንስን ሥራዎች ይጠቅስ እንደነበር ተናግሯል።

በ155 ዓ.ም. ፓሊካርፐ የፋሲካን በዓል ቀን በሚመለከት ውይይት ለማድረግ ወደ ሮም ሄዶ ነበር። እዚያም በነበረበት ወቅት ከሮሙ ጳጳስ ከአንሴቱስ ጋር ተገናኝቷል። በውይይቱ ነጥብ ላይ ባይስማማ እንኳ መልካም ወዳጆች እንደሆኑ ኖረዋል። ፓሊካርፐ በቤተ ክርስቲያን እንዲሰብክ ተጋብዞ ነበር። ይህም በዚህ ወቅት የሮም ጳጳስ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ላይ ምንም የበላይነት እንዳልነበረው በግልፅ ያሳያል።

በሮማው ቄሳር አንቶኒዮስ ፒዮስ ዘመነ መንግሥት ፓሊካርፐ በሰርሚንስ ከግንድ ጋር ታስሮ ተቃጥሏል። ክርስቶስን ቢክድ እንደማይገድሉት ሲነግሩት - “ክርስቶስን ለ86 ዓመታት ሳገለግለው በድሎኝ አያውቅም ታዲያ እንዴት ያዳነኝን ንጉሤን እክደዋለሁ” የሚል መልስ ሰጥቷቸዋል።

በ111 ዓ.ም. ፕሊኒ ከጥቁር ባህር በስተደቡብ የሚገኘው የቢታንያ አስተዳዳሪ ሲሆን በዚያ አካባቢ ክርስትና በጣም በመጠናከሩ ምክንያት የአራሚ ቤተ መቅደሶች ተረስተው እንደነበር ተመልክቷል።

የክርስትናንም መስፋፋት ለመግታት ዕቅዶችን አውጥቷል። ይሁን እንጂ በክርስቲያኖች ባሕርይ ተደንቆ ነበር። ክርስቲያኖች ማለዳ ጀምበር ስትወጣ ተገናኝተው መዝሙር ይዘምሩ ለአምላክ እንደሚጸልዩት ለክርስቶስ ይፀልዩ ከሌብነትና ከዝሙት እንደሚርቁና እምነታችውንም እንደማይክዱ ይማማሉ ስለነበር ፕሊኒ በጣም ተደንቆ ነበር። ይህ በዛሬው ዘመን በክርስቲያኖች መካከል አዲስ ባይሆንም ሥነ-ምግባር በጎደለውና በክፉ የሮማዊያን ዓለም ውስጥ የሚያስገርም ኑሮ ነበር።

ፕሊኒ ከሮማው ቄሳር ጋር በመመካከር ክርስቲያኖችን ለማጥፋት ዕቅዶችን ቀይሷል። እነዚህም ዕቅዶች ህዝቡ በጥቆማ መልክ ያቀረባቸውን ክሶች አስተዳዳሪዎቹ እንዳይቀበሉና ክርስቲያኖችን ለማጥመድ

እንዳይፍጨረጨሩ የሚያግዱ ናቸው። ይሁን እንጂ ተከሰው ቢቀርቡና ጥፋተኞች ሆነው ቢገኙ አስተዳዳሪዎቹ ቅጣት እንዲበይኑባቸው ታዘዋል። ክርስቲያኖች ቀደም ብለው ያደርጉት ስህተት መሆኑን አምነው የአራሚ አምላኮችን ካመለኩ ይቅርታ ሊደረግላቸው ነበር። ክርስቲያኖቹም የቀረቡባቸው ክሶች በጣም ጥቂት ስለሆኑ ይህን ያህል አላስጨነቃቸውም።

## <u>ቀድራቶስና አርቴደስ</u>

እነዚህ ሁለት ሰዎች የክርስትናን እምነት ለመጠበቅ የጣሩ ተሟጋቾች ነበሩ። በዚህ ዘመን በክርስትና እምነት ላይ የሚወራ ብዙ መጥፎ ወሬ ስለነበር በእነርሱና በአስተዳዳሪዎች መካከል ብዙ አለመግባባት አስከትሎ ነበር።

የቋድራቶስና አርቴደስ ጽሑፎች የክርስትና እምነታቸውን ለመጠበቅ የተጻፉ ዘገባዎች ነበሩ። ይሁን እንጂ በሁለተኛው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያ አኩሌታ ስለ እምነታቸው ያደረጓቸውን ሙግቶች በሚመለከት የተጻፈው በጣም ትንሽ ነው።

## <u>ጀስቲን ማርቲር</u>

ጀስቲን ማርቲር ከጥንት የክርስትና ተሟጋቾች መካከል ከፍተኛው ነው። ይህ ሰው እውነተኛ ክርስቲያንና ሐቀኛ መማር የሚወድ ሰው ነበር። ጀስቲን ቄሳር በማርኮስ ኤሬሊዮስ ዘመነ መንግሥት በ163 ዓ.ም. በእስራኤል አገር ተወለደ።

የጀስቲን ማርቲር <u>የመጀመሪያ ሙግት</u> የተሰኘው ጽሑፍ ለሮማው ቄሳር ለአንቶኒዮስ ፒዮስ፤ ለምክር ቤቱና ለሮም ሕዝብ በአጠቃላይ የተጻፈ ነበር። <u>ሁለተኛው ሙግት</u> በማለት የጻፈው አጭር ሲሆን የተጻፈውም ለምክር ቤቱ ብቻ ነበር። ጀስቲን ካቀረባቸው ጽሑፎች መካከል ረጅሙ ለአይሁድ ህዝብ ስለ ክርስትና ማብራሪያ ለመስጠት “ከአይሁዳዊው ትራይፎ ጋር የተደረገው ንግግር” በሚል ርዕስ የጻፈው ጽሑፍ ነው።

የጀስቲን ጽሑፎች የባህል ፍቅር የአክብሮት መንፈስና የእምነትን ዕውቀት የማስፋፋት ልባዊ ፍላጎት ይታይባቸዋል። ጀስቲን የተወለደው ከአራሚ ቤተሰብ ሲሆን የፍልስፍና ተማሪ ነበር። እውነትም ሊፈልግ ከሮም ወደ አቴንስ ከዚያም ወደ እስክንድሪያና ሌሎች ዋና ዋና ከተማዎች ተጉዟል። ከዕለታት አንድ ቀን በኤፌሶን አካባቢ ሲንሸራሸር ከአንድ ሽማግሌ ሰው ጋር ይገናኛል። ይህም ሰው ወደ እግዚአብሔር ቃልና ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መርቶት ለነበሩት ጥያቄዎች ሁሉ እውነተኛ መልስ አግኝቷል።

ክርስቲያኖች እምነት የለሽ ተደርገው መቀጠራቸውን ለመንግሥት የማይታዘዙ መደረጋቸውንና በድብቅ ስብሰባዎቻቸውም ወቅት ዝሙት እንደሚፈፅሙና የሰውን ሥጋ እንደሚበሉ ተደርጎ መታሰቡን ለመቃወም <u>የመጀመሪያውን ሙግት</u> የተሰኘውን ጽሑፍ አቅርቧል። ጀስቲን የፕሌቶ ፍልስፍና መልካም ነው ብሏል፤ ይሁን እንጂ ፍፁም መልስ ሊሰጥ እንደማይችል ተሰምቶታል። እውቀትና ፍልስፍና መልካም ነገሮች ቢሆኑም እንኳ ክርስቲያኖች የተለወጡት በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ነው በማለት አጥብቆ ይናገራል። ክርስቶስ ስለ መተላለፋችን አልፎ እንደተሰጠና የብዙዎችን ኃጢአት እንደተሸከመ በጉልህ አስተምሯል።

ጀስቲን “እሁድ ተብሎ በተጠራውም ቀን በከተሞች ወይም በገጠር ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች በአንድነት ይሰባሰቡ፤ ወንጌሎች ወይም የነቢያት ጽሑፎች ይነበቡ፤ ከዚያም መሪው እነዚህ መልካም ነገሮች በሁሉም ሕይወት እንዲታዩ ያስተምርና ይመክር፤ ሁላችንም ተነስተን እንጸልይ፤ ከዚያም ፀሎታችን ያበቃና እንጀራ ወይንና ውሃ ይቀርብና መሪውም ፀልዮና አመስግኖ ሁላችንም እንጀራውንና ወይኑን እንከፋፈል ነበር” ብሏል።

የሁለተኛው ምዕተ ዓመት ቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጊዜያት ይህን ያህል ውስብስብ አልነበሩም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ያነቡ፤ በመሪው አማካይነት ይማሩና መሪው የሚችለውን ያህል ይፀልይ ነበር። በዚያ ወቅት ይደረጉ የነበሩት ጸሎቶች በጽሑፍ የሰፈሩ ሳይሆን መሪው መንፈስ ቅዱስ ባሳሰበው መሠረት ብቻ ይጸልይ ነበር። አገልግሎት ይሰጥ የነበረው ሰው መሪ ተብሎ ይጠራ ስለነበር ከወንድሞች መካከል አንዱ ለመሪነት ይመረጥ እንደነበር እንጂ የካህናት ቤተሰብ እንዳልነበር ይጠቁማል።

በ163 ዓ.ም. ወይም ከዚህ ትንሽ ቀየት ብሎ ጂስቲንና በርካታ ባልደረቦቹ ጁኒዮስ ሩስቲቀስ ተብሎ በሚጠራው ንጉሥ በርም የሞት ፍርድ ተፍርዶባቸዋል። እነዚህም ሰዎች "ከሞትን በኋላ ተነሥተን ለዘለዓለም እንኖራለን ብላችሁ ታስባላችሁ?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ጂስቲን ሲመልስ "ማሰብ ሳይሆን እናውቃለን" ብሏል።

በማርቆስ ኦሬሊዮስ ዘመን እንደገና በክርስቲያኖች ላይ ስደት ቀጥሏል። አንድ የግሪክ ኅብረተሰብም በፈረንሳይ አገር የሮን ሸለቆ በተባለው ሥፍራ እንዲት ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን መሥርቷል። ሊዮንስና ቢዮን በተባሉት ሥፍራዎች በ177 ዓ.ም. በቤተ ክርስቲያን ላይ አስከፊ ስደት ተነሥቶ ነበር። የዘጠና ዓመት ዕድሜ የነበረውን ጳጳስ ፓቲኖስን ገድለውታል። ብላንዲና የተባለችውን እንዲት ልጃገረድ በየዕለቱ ያሰቃይዋት ነበር። ሆኖም እርሷ እምነቷን አልካደችም። በመጨረሻም ላይ በህዝብ ፊት በአሰቃቂ ሁኔታ ስይፈዋታል።

## የስህተት ትምህርቶች

በሁለተኛው ምዕተ ዓመት ላይ አዲስ ኪዳንን የሚቃረን የስህተት ትምህርት የሚያስተምሩ ብዙ ቡድኖች ነበሩ።

## ናዝራዊያን

ይህ ስም በመጀመሪያው የተሰጠው ለመላው ቤተ ክርስቲያን ነበር። በኋላ ደግሞ ጳውሎስን በጣም ያሰጨንቁት የነበሩት የአይሁድ እምነት ተከታዮች ናዝራዊያን በሚል ስም ይጠሩ ነበር።

ቤተ መቅደሱና ኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም. ከመደምሰሳቸው አስቀድሞ የኢየሩሳሌም ክርስቲያኖች የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገረው ፔላ ወደ ተባለው ስፍራ ሸሽተዋል። ሌሎች ክርስቲያኖች የአይሁድ ልማዶችን መጠበቅ ሲተው የእነዚህ ሰዎች ልጆች ለብዙ ዘመን ይጠብቁ ነበር። ሌሎችን የመማረክ ችሎታቸው ጠንካራ ባይሆንም እስከ 4ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ድረስ በዚህ መልክ ቀጥለዋል።

## ኢብዮናዊያን

እነዚህ ሰዎች ናዝራዊያንን ይመስላሉ፤ ይሁን እንጂ በትምህርታቸው ላይ ከእነርሱ ይልቅ በጣም ሙጭጭ ያሉ ሰዎች ናቸው። እያንዳንዱ ክርስቲያን የአይሁድን ሕግ መጠበቅ አለበት በማለት አጥብቀው ይናገራሉ። የጳውሎስን ጽሑፎች በሙሉና በስተቀር ወንጌሎችን ሁሉ ይቃወማሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ የሆነው በሚጠመቅበት ወቅት መንፈስ ቅዱስ ሲወርድበት ብቻ ነበር ብለው ያምኑ ነበር። ከመሞቱ አስቀድሞ መንፈስ ስለተለየው በመስቀል ላይ ስቃይ የተቀበለ ከማንኛውም ተራ ሰው በማይለይ አኳኋን ነበር ብለው ተናግረዋል።

## የኖስቲኮች ትምህርት

ይህ ትምህርት ቀደም ብለው ከተጠቀሱት ሁለት ትምህርቶች ይልቅ ጨሌነት የተሞላበትና አደገኛ ነው። ብዙ የተለያዩ የኖስቲክ ትምህርቶች ነበሩ። የዚህ እምነት ተከታዮች ምንም ክርስቲያናዊ እውነት የሌለው

የኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ትንታኔ አላቸው። አንዳንድ ጉልህ ያልሆኑ የክርስትና አስተሳሰቦችን ወስደው ከግሪክ፣ ከግብጽ፣ ፋርስና ህንድ ልብ ወለዶችና ፍልስፍናዎች ጋር ያዋህዷቸዋል። "ኖስቲክ" የሚባለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ እውቀት ማለት ነው። ይህ እውቀት ሚስጥር እንደሆነና ሊያገኙትም የሚችሉት የዚህ እምነት ከፍተኛ መንፈሳዊያን ብቻ መሆናቸውን የሚያምኑ ሲሆን የተቀሩትን ሰዎች በሁለት ምድቦች ይከፍሏቸዋል፤ እነርሱም "ሳይኪክ" የሚሏቸው ስለ ምድራዊ ነገሮች ትንታኔ ማቅረብ የሚችሉ ሲሆኑ ከእምነት ባሻገር ሊሄዱ አይችሉም፤ ነቢያትና አይሁድ የተመደቡት በዚህ ዝቅተኛ ምድብ ውስጥ ነበር። አብዛኛው ሕዝብ የተመደበው "ሐይሌክ" ተብሎ በሚጠራው ምድብ ነበር። ይህም ማለት የቁስ አካል ተገዢ ወይም ለሥጋቸው የሚኖሩ እንስሳት ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ተስፋ በሌለው የሰይጣንና የሥጋቸው ምኞት ባርነት ውስጥ ናቸው።

የዚህ እምነት ተከታዮች ቁስ አካል መጥፎ መሆኑንና ደህንነት ደግሞ የሚገኘው እርሱን በቁጥጥር ስር አውሎ በማጥፋት እንደሆነ ያስተምራሉ። ይህንንም ሊያደርጉ የሚችሉ እውቀት ያላቸው ሰዎች ብቻ ናቸው። ቁስ አካልንም ለመቋቋምና ድል ለማድረግ ከቁስ አካላዊ ደስታዎች ይገለላሉ። በመጀመሪያ ላይ የእነዚህ ሰዎች ሥነ-ምግባራዊ ህይወት በጣም ጥብቅ ነበር፤ ይሁን እንጂ ቀይተው አሽቀልቁለዋል።

በ2ኛው ምዕተ ዓመት አጅግ ታላቅ የነበሩት የዚህ እምነት መምህራን ቫለንቲኖስና ባሲለደስ የተባሉት ነበሩ። እነዚህ ሁሉቱም የእስክንድሪያ ተወላጆች ነበሩ። ሌላው የዚህ እምነት መሪ በ170 ዓ.ም. በሮም የሞተው የሲኖኙ ማርሲዮን ነበር። ማርሲዮን የብሉይ ኪዳን አምላክ የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት አይደለም በማለት ብሉይ ኪዳንን በመቃወም አስተምሯል። ቤተ ክርስቲያን ብታወግዘውም እንኳ ከነበረው የህይወት ንጽህናና ትህትና የተነሳ ብዙ ተከታዮች ነበሩት።

በዚህ እምነት ተከታዮች አባባል መለኮት በራሱ የተፈጠረ፣ ሊታወቅ የማይችልና የማይደረስበት ነው፤ መለያ ባህርያት የሌሉት ሲሆን ጊዜና ለውጥ በእርሱ ላይ ምንም ስልጣን የላቸውም። ሆኖም እነዚህ ሰዎች ሊፈቱት ያልቻሉት ጥያቄ ይህ አምላክ መጥፎ ብለው የቆጠሩትን ቁስ አካልን እንዴት ሊፈጥረው ቻለ? የሚለው ነበር።

የዚህ እምነት ሥርዓቶች ሁሉ ፍልስፍና ነክና ውስብስብ የሆኑ ናቸው። ከኖስቲክ ትምህርት ቤቶች አንዱ ፊርያንና አክዓብን ቅዱሳን ሲያደርጋቸው ሙሴና ኤልያስ ደግሞ ኃጢአተኞች ነበሩ ብሎ አስተምሯል። በተጨማሪ የብሉይ ኪዳን አምላክም እንኳ መጥፎ ነበር ብለው ተናግረዋል። ክርስቲያኖችን በከፍተኛና በዝቅተኛ ደረጃዎች ከፋፍለዋል።

አንዳንድ የኖስቲክ ምሁራን የራሳቸውን ትምህርት ለመደገፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያዎችን መጻፋቸው ክርስቲያን ምሁራን እውነተኛውን ትርጉም እንዲፈልጉ ቀስቅሷቸዋል። ይህም ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለመጠበቅ የሚረዷቸው ዘገባዎችን እንዲጽፉና ትምህርተ ክርስትናቸውንና የአዲስ ኪዳንን ጥራዝ በሚመለከት ጉልህ መግለጫ እንዲያገኙ ረድቷቸዋል።

## የሞንታኒስ ትምህርት

ይህ የስህተት ትምህርት የጀምረው ቤተ ክርስቲያን በደከመችበት ዘመን ነበር። የኖስቲክ ትምህርት የክርስትናን መሰረቶች በማናጋት ላይ ነበር። በዚህ ዘመን ሐዋሪያት በሙሉ በህይወት አልነበሩም፤ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችም ጨርሶ አይታዩም ነበር። ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት ተነሥተው ስለነበር ትንቢት አጠራጣሪ ነበር። ይህ እምነት በክርስቶስና በእግዚአብሔር ቃል ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ ሰሚቶችንና ከፍላጎታቸው የመነጩ አስተሳሰቦችን ያጋንን ነበር።

ቤተ ክርስቲያን የምትደገፈው በመንፈስ ቅዱስ ላይ መሆኑን የሚናገር ምስክርና ማስተዋል ያስፈልግ ነበር። ይህ እምነት በመንፈስ ቅዱስ ላይ በተለይም በመንፈሳዊ ስጦታዎችና በትንቢታዊ መገለጦች ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርግ ነበር። ይሁን እንጂ ልክ ኖስቲኮች እንደሚያደርጉት ይህም የእምነት ክፍል የሰውን አስተሳሰቦች ከመለኮታዊ መገለጥ በላይ ያደርጋቸው ነበር።

ይህ ትምህርት የተጀመረው ሚሲያ በሚባል ሥፍራ ይኖር በነበረ ምንታኖስ በተባለ ሰው ነበር። ይህም ሰው ከመንፈስ ቅዱስ ልዩ መገለፅ ተቀብያለሁ በማለት ታላቅ የማነቃቃት ዘመቻ አድርጓል። ሁለት ባለፀጋ ሴቶች ባሎቻቸውን ትተው ከእርሱ ጋር ተቀላቅለዋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓት የማስያዝ ሥልጣን አለን በማለት ደግሞ ጋብቻ ይከለክሉና ሳያገቡ መኖር በጣም ከፍተኛ ነገር መሆኑን በጥብቅ ይናገሩ ነበር። ከትዕቢታቸውም የተነሳ በትምህርታቸው ከክርስቶስ እንደሚበልጡ ይሰማቸው ነበር።

የካርቴጁ ተርቶሊዮን ከዚህ እንቅስቃሴ ጋር ሲደባለቅ የእምነት ክፍሉ ታላቅ ኩራት ተሰምቶታል። ይሁንና ይህ የእምነት ክፍል በ370ዓ.ም. ከአፍሪካ ምድር ሲጠፋ በ6ኛው ምዕተ ዓመት ደግሞ ከሌሎች ሥፍራዎችም ጠፍቷል።

በዚህ ምድር ይቅር የሚባሉ ኃጢአቶች መኖራቸውንና የማይባሉም ኃጢአቶች እንዳሉ የዚህ እምነት ተከታዮች አስተምረዋል። የሺህ ዓመት ዘመን የሚመጣው ሰው ሁሉ የሰማዕት እርካታ ሲያገኝ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህ ምክንያት ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን ምፅዓት በሚመለከት ትምህርት ማስተማሯን በማቋረጥ ክርስቶስም በጣም የራቀ ተደርጎ እንዲቆጠር አድርጋለች።

ካህናቱ የክርስቶስን መስዋዕት መልሰን በመሰዊያው ላይ ልናቀርብ ነው ብለው ስላሰቡ ተኩራርተው ነበር። ስሜታዊ የሆነው የዚህ እምነት ተከታዮች ስብከት በአጠቃላይ ስብከቱን የሚመለከት ነገር ሁሉ ደግሞ እንዲጠላ አድርጓል። ይህም በተራው ካህናትን ወደ መኩራራት መርቷቸዋል። ህዝቡም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚችሉት በካህናት በኩል ብቻ እንደሆነና በቤተ ክርስቲያን አማካይነት በስተቀር ደህንነት የሌለ መስሎ ተሰምቷቸው ነበር። ካህናቱም ሥልጣናቸውን የተቀበሉት በቀጥታ ከሐዋሪያት እጅ መሆኑን ተናግረዋል። ይህም ከሐዋርያት ትምህርት በጣም የራቀ ነበር።

## <u>የሮም ቄሳሮች</u>

| <u>ስም</u> | <u>የግዛት ዘመን</u> | <u>ከቤተ ክርስቲያን አንፃር የነበራቸው አቋም</u> |
|---|---|---|
| ቬስፓሲያን | 69-79 ዓ.ም. | ኢየሩሳሌምን ደምስሷል |
| ቲቶ | 79-81 ዓ.ም. | ኢየሩሳሌምን ደምስሷል |
| ደሚቲያን | 81-96 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳደደ |
| ነርቫ | 96-98 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳደደ |
| ትራጃን | 98-117 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳደደ |
| ሐጽሪያን | 117-138 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳደደ |

| | | |
|---|---|---|
| አንቶኒዮስ ፒዮስ | 138-161 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳዷል |
| ማርቆስ ኦሬሊዮስ | 161-180 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳዷል |
| ወታደራዊ ቄሳሮች | 192-248 ዓ.ም. | የርስ በርስ ጦርነት ዘመን |
| ሲፐቲሚዮስ ሰቨረስ | 193-211 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳዷል |
| ካራካላ | 211-227 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አልነካም |
| ኤላጋባሉስ | 218-222 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አልነካም |
| አስክንድር ሰቨረስ | 222-235 ዓ.ም. | ክርስትናን ይደግፍ ነበር |
| ማክሲሚን | 235-238 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳዷል |
| አረባዊው ፊሊጶስ | 244-249 ዓ.ም. | ክርስትናን በጣም ይደግፍ ነበር |
| ዲሲዩስ | 249-251 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን ክፍኛ አሳዷል |
| ቬለሪያን | 253-260 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን አሳዷል |
| ጋሊየነስ | 260-268 ዓ.ም. | ክርስትናን ይደግፍ ነበር |
| ኦሬሊያን | 270-275 ዓ.ም. | ክርትስናን አሳዷል |
| ዲዮክሌቲያን | 284-305 ዓ.ም. | ክርስቲያኖችን ክፉኛ አሳዷል |
| ኮንስታንቲን | 306-337 ዓ.ም. | ክርስቲያን ሆነ ክርስትናን ደገፈ |
| ጁሊያን | 361-363 ዓ.ም. | ጣኦት አምልኮን ለማቋቋም እንዲሁም ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደድ ጥሯል |
| ጆቪያን | 363-364 ዓ.ም. | ቤተክርስቲያንን መልሶ አቋቋመ |
| ቴዎዶሲዮስ | 378-395 ዓ.ም. | ክርስትናን የመንግሥት ሃይማኖት አድርጓል |
| | ግዛቱ ተከፋፈለ | |

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተጀመረው የት ነበር?
2. በጥንት ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከግሪክ ባህል ወጥተው ታላቅ የወንጌል ምስክሮች የሆኑት ሁለት አይሁዳዊያን ማንና ማን ናቸው
3. ብዙ አህዛብ የክርስትናን እምነት ሲቀበሉ በአማኞች መካከል የተፈጠረው ችግር ምን ነበር?
4. በሮሙ ቄሳር በኔሮ ዘመን በእስራኤል የተፈጠረውን አመፅ የቀሰቀሰው ማን ነበር?
5. በ66-70ዓ.ም. ኢየሩሳሌም ስትወረር ክርስቲያኖች የት ነበሩ?
6. ቤተ መቅደሱ ሲደመሰስ ቀድሞ ይካሄድ የነበረው አምልኮ ምን ሆነ?
7. ከሐዋሪያት መካከል ምናልባት በመጨረሻ የሞተው ሐዋሪያ ማን ነበር? መቼ?
8. "የክሌመንት መልዕክት" የተጻፈው ለማን ነበር? የደብዳቤውስ ዓላማ ምን ነበር?
9. በርናባስ በ132 ዓ.ም. ስለጻፈው መልዕክትና ሄርሚስ በ140-150ዓ.ም. መካከል ስለጻፈው መልዕክት ባጭሩ ግለጽ።
10. ኢግናቲዮስ ማን ነበር? ትምህርቶቹስ የሚያተኩሩት በምን ላይ ነበር?
11. የ2ኛው ምዕተ ዓመት እጅግ ተወዳጅ የቤተ ክርስቲያን አባት ማን ነበር? የማን ተማሪ ነበር? የሞተውስ እንዴት ነበር?
12. የቢታኒያ አስተዳደሪ የነበረውን ፐሊኒን ያስደነቀው የ2ኛው ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች መሐላ ምን ነበር?
13. ቋድራቶስና አርዴቴስ ምንድን ናቸው?
14. የ2ኛው ምዕተ ዓመት ታላቅ የክርስትና ተሟጋች ማን ነበር?
15. ጀስቲን ማርቲር የሙግት ጽሑፎችን የጻፈው ለማን ነበር?

## ምዕራፍ ሁለት - የጥንት ቤተ ክርስቲያን አባቶች 180-250 ዓ.ም.

በሁለተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ኖስቲኮች በፍልስፍናዎቻቸው እንዲሁም ሞኖታኒስቶች ለመማር ባላቸው ጥላቻና በስሜታዊነት ላይ በተመሰረተው አክራሪነታቸው አማካይነት ቤተ ክርስቲያንን በመንፈሳዊ ሁኔታ አዳክመዋት ነበር። እርቀ አስተዋይነትና ሙሉ የልብ ፈቃደኝነት የነበራቸው ጥቂት ሰዎች በጣም ጠቃሚ ሥራ የጀመሩት በዚህ ዘመን ነበር። እነዚህም ሰዎች ኤሬኒዮስ፣ ተርቱሊያን፣ ሲፐሪያን፣ የእስክንድሪያው ክሌመንትና ኦሪጅን ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በሦስት ከባድ ችግሮች ማለትም፡

1. በአዲስ ኪዳን ጥራዝ
2. በእምነት መመሪያና
3. በሐዋሪያት የሥልጣን ተዋረድ ላይ ትኩረት አድርገዋል።
   የአዲስ ኪዳን ጥራዝ የተሰኘው በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

እነዚህ ሰዎች በጣም ጠቃሚ ሥራ ቢያከናውኑም እንኳ ከሰጧቸው ውሳኔዎች መካከል ጥቂቶቹ በኋለኞቹ ዘመናት አወዛጋቢ ሆነዋል።

## የአዲስ ኪዳን ጥራዝ

በ2ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ በአዲስ ኪዳን ጥራዝ ውስጥ ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚገባት መጽሐፍት ዝርዝር ውሳኔ አልተሰጠውም ነበር። ኖስቲኮች የራሳቸው ወንጌሎችና መልዕክቶች በአዲስ ኪዳን ጥራዝ ውስጥ እንዲጠረዙላቸው አጥብቀው ጠይቀዋል። ኢሬኒዮስ በዚህ ጥራዝ ውስጥ መጠቃለል ያለባቸው በሐዋሪያትና ከእነርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት በነበራቸው ሰዎች የተጻፉት ብቻ ናቸው በማለት

ደንግጓል። ተርቱሊያንም በዚህ ተስማምቶ በጥራዙ ውስጥ የሚገኙትን መጻሕፍት "አዲስ ኪዳን" ብሎ በመሰየም ልክ እንደ "ብሉይ ኪዳን" መለኮታዊ እስትንፋስ ያለበት መጽሐፍ እንደሆነ ተናግሯል።

የአዲስ ኪዳን ጥራዝ ማለት መለኮታዊ ሥልጣን ያለባቸው መጻሕፍት ዝርዝር ማለት ነው። እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ሌሎቹን ጽሑፎች ሁሉ የምትፈትንባቸው መጠይቆችን ያቀፈ አንድ መመሪያ እንደሚያስፈልጋት ተገንዝባለች። ስለዚህ የመጀመሪያ ጥያቄ "ጽሑፉን የጻፈው ሐዋሪያ ነው ወይስ ከሐዋሪያት ጋር የቅርብ ግኑኝነት የነበረው ሰው?" የሚል ሲሆን 2ኛ ጥያቄ "የጻፈው ጽሑፍ ሐዋሪያት ከሰጧቸው መመዘኛ ባህሪያት ዝቅ ባለ የሥነ-ምግባር መመሪያ የተሞላ ነው ወይስ መለኮታዊ ትምህርት ይዟል?" የሚል ነበር።

አሁንም ጥቂት ያልተመለሱ ጥያቄዎች ቢኖሩም እንኳ በአዲስ ኪዳን ጥራዝ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት በሙሉ በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ውስጥ የተጻፉ መሆናቸውን በርካታ መረጃዎች ይጠቅሳሉ። በዚህም ዘመን ጥቂት መጻሕፍት ተቀባይነት ስለማግኘታቸው አንዳንድ ጭቅጭቅ ተነሥቶ ነበር፤ ይኸውም – ዕብራዊያን የጻሐፊው ስም ስላልተጠቀሰበት፤ 2ኛ ጴጥሮስ የአጻጻፍ ስልቱ ከ1ኛ ጴጥሮስ ስለተለየና 2ኛና 3ኛ ዮሐንስ ደግሞ ዮሐንስ ስሙን ሲጠቅስ ሐዋርያው በማለት ፈንታ ሽማግሌው ስላለ ነበር። በኋላ እነዚህም መጻሕፍት ተቀባይነት አግኝተው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጨምረዋል።

የአዲስ ኪዳንን ጥራዝ ለማዘጋጀት ረጅም ዘመን የፈጀ ሲሆን ሊሳካ የቻለው ብዙ የሃሳብ ስምምነት ከተደረገ በኋላ ነበር። የአዲስ ኪዳን ጥራዝ ሲዘጋጅ የታዩት ሦስት ሁኔታዎች መለኮታዊ ምሪት፤ የልዩ ጽሑፎች በቤተ ክርስቲያን አባቶች ተለይቶ መታወቅና ከዚያ በመጨረሻ ላይ በይፋ መፅደቅ ነበሩ። በ397 ዓ.ም. እና እንደገና በ419 ዓ.ም. በቀልሴዶን በተሰበሰበው ጉባኤም ይህንኑ ውሳኔ አጽድቋል። 27ቱ መጻሕፍት በሥልጣን ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የተገለጹት አትናቴዎስ በ367 ዓ.ም. ለነበረችው ቤተ ክርስቲያን በጻፈው ደብዳቤ ነው።

## የእምነት መግለጫ

ለቤተ ክርስቲያን ችግር ምላሽ ለመስጠት የአዲስ ኪዳን ጥራዝ እንደተጠረዘ ሁሉ የእምነት መግለጫዎችም ተዘጋጅተዋል። የአዲስ ኪዳን ጥራዝ ተዘጋጅቶ ከማለቁ በፊትና ብዙ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቅጂዎች በማይገኙበት ዘመን አማኞች የሐሰት ትምህርቶችን የሚመዝኑበት አንድ መመዘኛ ነገር አስፈልጓቸው ነበር። ከዚህም ችግር የተነሣ "የእምነት መግለጫ" ተዘጋጅቶ ነበር። ይህም መግለጫ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ ልዩ ይዘት ነበረው። በኋላ ከእነዚህ መግለጫዎች መካከል አንዱ የሐዋሪያት የእምነት መግለጫ በመባል ታዋቂ እይሆነ ሄዷል። ይህም ቀጥሎ የተጠቀሰው ነው - "ሰማይንና ምድርን በፈጠረው በእግዚአብሔር አብ አምናለሁ። ከመንፈስ ቅዱስ በተጸነሰና ከድንግል ማሪያም በተወለደው በእግዚአብሔር አንድ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ። እርሱ በጲላጦስ የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል፣ ተሰቅሏል፣ ሞቷል፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር አብ ቀኝ ተቀምጧል። በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ይመጣል። በመንፈስ ቅዱስ አምናለሁ። በቤተ ክርስቲያንና በአማኞች ኅብረት አምናለሁ። በኃጢአት ስርየት በሙታን ትንሳኤና በዘላለም ሕይወት መኖር አምናለሁ።"

በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያንን የከፋፈሉ አንዳንድ ውዝግቦችን ለማብረድ ሌሎች የእምነት መግለጫዎች ተጽፈው ነበር። ከእነዚህ ውዝግቦች መካከል አንዳንዶቹ የኢየሱስ ክርስቶስን ባህሪይ በሚመለከት የተነሱ ሲሆኑ ጥቂቶቹ መንፈስ ቅዱስን የሚመለከቱ ነበሩ።

ኢሬኒዮስ እነዚህን የትምህርተ ክርስትና ችግሮች በሐዋሪያት ዘመን ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን እምነት ጋር አዛምዷቸዋል። በተጨማሪ ከአብያተ ክርስቲያናት ትውፊትም ጋር አያይዟታል። ምዕመናን የጥንቱን

ትውፊቶች ረስተው ብዙ አዳዲስ የሆኑ ትውፊቶች ስለጨመሩባቸው ቆይቶ ለቤተ ክርስቲያን አንቅፋት ሆነዋል።

## የሐዋሪያት የሥልጣን ተዋረድ

ኤሬኒዮስ ሐዋሪያትን የተኩትን ሰዎች ስም ዝርዝር በማውጣት የቤተ ክርስቲያን አመራር ለመጠበቅ ሙከራ አድርጓል። በዚያ ዘመን ጳጳሶችና ሽማግሌዎች የሚለዩበት ነጥብ አልነበረም። በሦስተኛው ምዕተ ዓመት አኩሌታ አካባቢ ቤተ ክርስቲያን በጳጳሳት መመራት ጀመረች። የካርቴጁ ጳጳስ ሲፐሪያን ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ትመራ የነበረው ሐዋሪያትን በተኩት ጳጳሳት ነበር በማለት አስተምሯል። ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ደህንነት የሌለ ሲሆን ሐዋሪያዊ ሥልጣንም በመጀመሪያ የተሰጠው ለጴጥሮስ ነበር ሲሉ ጳጳሳት አስተምረዋል። ስለዚህ ነጥብ ሲያስተምር "ትውፊት" ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በእኩልነት ይታይ ነበር።

## የጎሉ ኤሬኒዮስ

ኤሬኒዮስ ከታላላቆች የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወይም መምህራን መካከል የመጀመሪያው ነበር። ኤሬኒዮስ በእስያ ክፍለ ሃገር በ130 ዓ.ም. ተወለደ። የሐዋሪያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረው የፖሊካርፕ ተማሪ ነበር። በፖሊካርፕ ዘመን ትውፊት ምናልባት ጭብጥነት ሳይኖረው አይቀርም።

በ177ዓ.ም. ፓቲኖስ የተባለው ሽማግሌ በህዝብ አመፅ ከተገደለ በኋላ ኢሬኒዮስ ሊዮን በተባለው ጎል ተብሎ በሚጠራው አገር ጳጳስ እንዲሆን ጥሪ ተደርጎለታል። ለቤተ ክርስቲያን ካበረከታቸው አገልግሎቶች መካከል አጅግ ከፍተኛዎቹ ጽሑፎች ናቸው። ኢሬኒዮስ በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያንን ከኖስቲክ ትምህርት ለመጠበቅ ከጻፋቸው መካከል "ፀረ-መናፍቅ ትምህርቶች" የተሰኙት አምስት መጽሐፍት በእጃችን ይገኛሉ። ናፈቀ ማለት ሃይማኖቱን ተጠራጠረ፤ እምነት ጎደለው፤ በሃሳቡ ማመንታት ጀመረ፤ ነገሩን አምታታ፤ አወላወለ ማለት ነው።

## የካርቴጁ ተርቱሊያን

ወንጌል በመጀመሪያ ወደ ሰሜን አፍሪካ እንዴት እንደመጣ የሚናገር ታሪካዊ ዘገባ አይገኝም። ይሁን እንጂ በ180 ዓ.ም. በሰሜን አፍሪካ ብርቱ ቤተ ክርስቲያን ትገኝ ነበር። በመሐል አገር ይገኙ ከነበሩት የዚች ቤተ ክርስቲያን አባላት በሰማዕትነት አልፈዋል።

ተርቱሊያን ሲፐሪያንና አውግስቲን ሦስቱም የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባላት ነበሩ። እስክንድሪያ የግሪክ ከተማ ስትሆን ካርቴጅ የላቲን ቋንቋ ተናጋሪዎች ከተማ ነበረች። ካርቴጅ ዋጋ የነበራት የላቲን ባሕል ማዕከልና ሰፊ ያማረች ከተማ ነበረች። የመጀመሪያው የላቲን ቋንቋ የክርስትና ጽሑፍ የተጻፈው በዚህች ከተማ ነበር።

ተርቱሊያን የተወለደው በካርቴጅ ሲሆን ይኸውም ከ155-160ዓ.ም. መካከል ነበር። ወላጆቹ የአረማዊ እምነት ተከታዮች ሲሆኑ እርሱም ያደገው በዚያው ኅብረተሰብ ውስጥ ነበር። ተርቱሊያን በጥብቅና ሙያ የሰለጠነ ሰው ነበር። ይህም መለኮታዊ ትምህርቶችን በሚመለከት በነበረው የአገላለጽ ዘዴ ላይ ተንጸባርቆአል። እግዚአብሐርን በማስመልከት በጻፈው ጽሑፍ ውስጥ "ሥላሴ" የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት እርሱ ነው።

ተርቱሊያን ወንጌልን በመካከል በርካታ መጽሐፍት ጽፏል። ሠላሳ የሚያህሉ መጽሐፍትና ሌሎች ጽሑፎች እስካሁንም ድረስ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል እንዱና ወደር የማይገኝለት በ197ዓ.ም. የተጻፈው "መከላከያ ሃሳብ" የተባለው ጽሑፍ ነው። አንዳንድ ጽሑፎቹ እንድ ክርስቲያን በብዙ ልማዶች በተሞላ

የአራሚ ኅብረተሰብ ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን ትክክለኛ ባህሪይ በሚመለከት የተጻፉ ናቸው። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ወንጌልን ከማያምኑ ሰዎች ጋር አንዳንድ እውነትን አስመልክቶ ውይይት ማድረግን እስኪከለክል ድረስ በጣም አከራካሪ ነበር። ታላላቅ ሥጦታዎች የነበሩት ቢሆንም እንኳ አንዳንድ ስህተቶችም ይታዩበት ነበር። ተርቱሊያን ወገናዊ፣ መንቻካና በቀለኛ ሰው ነበር።

## የካርቴጁ ሲፐሪያን

ሲፕሪያን በ200ዓ.ም. ገዳማ በካርቴጅ ከተማ ከባለጠጋ ወላጆች ተወለደ። አርባ ስድስት ዓመት ሲሆነው በአንድ ባረጀ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ አማካይነት ጌታን አግኝቶ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ጀመረ። መኖሪያ ቤቱን ሸጦ ገንዘቡን ለድሃ አከፋፈለ። ከተጠመቀ ከ2 ዓመት በኋላ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆኗል። ከዚህ ጊዜ በኋላ ወዲያው የካርቴጅ ጳጳስ እንዲሆን ተመርጧል። ሲፐሪያን ይህንን ከፍተኛ ሥልጣን አልፈለገውም፣ ሕዝቡ ግን በሃሳባቸው ላይ ፀንተዋል። ይሁን እንጂ ይህ አዲስ አማኝ ለጽጽስና መመረጡ ሌሎቹን ነባር ሽማግሌዎች አስቆጭቷቸው ወደ መከፋፈል አምርተዋል።

በ250ዓ.ም. ዲሲየስ በተባለው ቄሳር አማካይነት ከፉ ስደት ተጀመረ። ይህም ብዙዎቹን ታማኝ ያልሆኑ የስም ክርስቲያኖችን አበጥሮ አውጥቶአቸዋል። በዚህም ወቅት ሲፐሪያን ከካርቴጅ ወጥቶ ነበር፤ ቢሆንም ከዓመት በኋላ ተመልሷል። ሲፐሪያን በሚከተሉት ምክንያቶች በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ከፍተኛውን ሥፍራ ይዟል።

1. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከፍተኛ የመንፈስ ብቃት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው አጥብቆ ተናግሮአል። ይህም ተቀናቃኝ ጳጳስ በሆነው በኖቫቱስ የሚመራ ተቃዋሚ ቡድን እንዲፈጠር አድርጓል። ይህ ማህበር "ተፀፃቾች" በሚል መጠሪያ ይጠራ ነበር። በቤተ ክርሲቲያን አባልነት ይቀበላቸው የነበሩትም ሰዎች ክርስቶስን ክደው የነበሩትን ሰዎች ሲሆን ይኸውም ንስሐ መግባታቸውን እንኳ በውል ሳያረጋግጥ ነበር።

   ኖባቲያን የተባለው ደግሞ በሮም የነበረ ተቀናቃኝ ጳጳስ ነበር። ማኅበሩም እምነትን የካደ ወይም "የሚገባው ኃጢአት" የሠራ ጭራሽ ተመልሶ የቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆን አይችልም የሚል ጥብቅ መርሆ ነበረው።

   ሲፐሪያን ከእነዚህ ሁለት ማኅበራት በጣም የበረታ ተቃውሞ ድርሶበታል። ይህንንም ተቃውሞ ለማቃለል የቤተ ክርስቲያን አንድነት አስፈላጊ መሆኑን አጥብቆ ተናግሯል። ጳጳስ ሥልጣኑን የሚቀበለው በቀጥታ ከእግዚአብሔር መሆኑንና በእግዚአብሔር የተሾመ የቤተ ክርስቲያን መሪ እንደሆነ አውጆአል። ምዕመናን ለጳጳሱ ፍጹም መታዘዝ ማሳየት እንዳለባቸው ተናግሯል። ቆየት ብሎ በኋለኞቹ ዓመታት ይህ ነገር በሰፊው ተቀባይነት አግኝቷል በዚህም ሳቢያ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በአንድ ሰው መሪነት ስር ወደመሆን ደርሳለች።
2. ቀሳውስት መስዋዕት የሚሰው ካህናት እንዲሆኑ አድርጎ የሚያቀርብ ሃሳብ አፍልቋል። የጌታን እራት በመሰዊያ ላይ የተሰዋ የራሱ የክርስቶስ ሥጋና ደም አድርጎ ቀጥሮታል። ከጊዜ በኋላም በእርግጥ ሕብስቱና ወይኑ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይለውጣል ወደሚለው ትምህርት አምርተዋል። እስከዚህም ዘመን ድረስ ቤተ ክርስቲያን መሠዊያ የሌላትና መስዋዕት እንደማትሠዋ ለአራሚ እምነት ተከታዮች ያስተምር ነበር።
3. እያንዳንዱ ጳጳስ በራሱ ሰበካ ውስጥ ሙሉ ሥልጣን አለው ብሎ አስተምሯል። ይህም የሮማ ጳጳስ እስጢፋኖስ መናፍቆችን ስለ ማጥመቅ አብያተ ክርስቲያናትን ሁሉ ለማስማማት ያደረገው ሙከራ ውጤት ነበር። ከእርሱ በፊት የነበሩት ፖሊካርፕና ኢሬኒዮስ እንዳደረጉት ሲፐሪያንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ለሮም ጳጳስ ይገዙ የሚለውን ሃሳብ ፍንክች ሳይል ተቃውሟል።

## የእስክንዲሪያው ክሌመንት

የእስክንድሪያ ከተማ በ332 ዓክልበ በታላቁ እስክንድር የተቆረቆረች ከተማ ነበረች። ይህችም ከተማ ሁለት ተኩል ሚሊዮን ሕዝብ የሚኖርባት ከዓለም እጅግ ታላላቅ ከተማዎች መካከል አንዷ ሆናለች። ባህሏ የግሪክ ሲሆን ብዙ የአይሁድ ሕዝቡ ይኖርባት ነበር። ከብሉይ ኪዳን የግሪክ ቅጂዎች አንዱ የሆነው "ሴፕቱአጂንት" በ200 ዓክልበ ገደማ በዚህች ከተማ ውስጥ ተተርጉሟል። ሴፕቱአጂንት በግሪክ 70 ማለት ነው፡ ስለዚህ የተተረጎመው በ70 ምሁራን ነው ማለት ነው። ይህም ግሪክ ተናጋሪ በሆኑት ሰዎች መካከል ለወንጌል መንገድ አዘጋጅቶለታል። በ2ኛውና በ3ኛው ምዕተ ዓመታት በዚህች ከተማ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ተከታታይ የሆኑ ታላላቅ መሪዎች አፍርታ ነበር፡ ከእነዚህም አንዱ ክሌመንት ነበር።

በእስክንድሪያ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማስተማሪያ ማዕከል ተቋቁሯል። ቤተ ክርስቲያን በአካባቢዋ ያለውን ዓለም ልትቋቋም መቻል አለባት የሚል እምነት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ልብ አድሮ ነበር። በመጀመሪያ ትምህርት ቤቱ የሚያስተምረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ብቻ ነበር፤ ይሁን እንጂ ወዲያው የፍልስፍና የስዋስው የሥነ ጽሑፍ የሂሳብና የሳይንስ ትምህርቶችን ማስተማር ጀምሯል። ወደዚህ ትምህርት ቤት ይመጡ የነበሩት በርካታ ተማሪዎች የክርስትያንና የአራሚ እምነት ተከታይ ከሆኑ ኅብረተሰብ ነበር። ብዙ ሰዎችም እውነትን ይፈልጉ ነበር።

በ190ዓ.ም. አካባቢ ክሌመንት የዚህ ት/ቤት አስተዳዳሪ ሆኗል። ክሌመንት ትምህርትን ከክርስቲያንም ሆነ ከአራሚ እምነት ከተለያዩ ምንጮች ሰብስቦ ለክርስቶስ አገልግሎት በማዋል ያምን ነበር። ቤተ ክርስቲያን የአራሚ ፍልስፍናን ችል ልትለው እንደማይገባ አምኗል።

በ202ዓ.ም. ክሌመንት በሮሙ ቄሳር በሴፕቲመስ ሰቨረስ አማካይነት በተነሳው ስደት ከእስክንድሪያ ተባሯል። በ220ዓ.ም. በቂሳሪያ እንዳለ ሞቷል። ክሌመንት ብዙ ጽሑፎችን ጽፏል።

## ኦሪጂን

ኦሪጂን የኖረው ከ185-254ዓ.ም. ነበር። ከቤተ ክርስቲያን ወደር የሌላቸው መምህራንና ጸሐፊዎች መካከል አንዱ ነበር። አባቱ ሰማዕት ሲሆን ያደገው በጣም መንፈሳዊ በሆነ ቤተሰብና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር። ገና የ18 ዓመት ወጣት ሳለ ክሌመንት ያስተዳድረው የነበረው የእስክንድሪያ ትምህርት ቤት መሪ ሆኗል። በዚህ ዘመን ስደት የነበረ ቢሆንም እንኳ ትምህርት ቤቱ በእርሱ አመራር አማካይነት ዝነኛ ሊሆን ችሏል።

የእግዚአብሔርን ቃል ይወድ ነበር፤ ከፍተኛ ቃሉን የመፍታት ችሎታም ነበረው። በመፆም ያምን፣ የወይን ጠጅ መጠጣት ይቃወምና በመሬት ላይ ይተኛ ነበር።

"ኦሪጂን ማንኛውም ሰው በህይወት ዘመኑ አንብቦ ሊጨርሳቸው የማይችሉ መጽፍት ጽፏል" ሲል ጀሮም የተባለው ታሪክ ጸሐፊ ተናግሯል። የጻፋቸው መጽሐፍት ማብራሪያዎችን፣ የመለኮታዊ ትምህርትና የመከላከያ ጽሑፎችን ያጠቃልላሉ።

የጥንት ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን እግዚአብሔር አድርጋ ትቀበለው ነበር። ይሁን እንጂ በ2ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ አዳዲስ ሃሳቦች ፈልቀዋል። ከእነዚህም መካከል ቀንደኛው ሞናርክ በሚለው ቃል ላይ የተመሰረተ ነበር። ሞናርክ የተሰኘውን የግሪክ ቃል የመረጡት ምክንያት እግዚአብሔር የሚለው ስም

አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅድሱን የሚያጠቃልል መሆኑን ለመካድና እግዚአብሔር በእነዚህ ሦስት ስሞች ቢጠራም እንኳ እነዚህ ስሞች ሥራዎቹን የሚገልፁ እንጂ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በመሆን አለመገለፁን ለማስተማር ነበር። አንዳንዶቹ ሰው በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መለኮታዊ ኃይል ወረደበት የእግዚአብሔርን ሥራዎች እንዲሠራ አስችሎታል ብለው ያምኑ ነበር። ሌሎች ደግሞ የእግዚአብሔር ሙላት ሁሉ በክርስቶስ ውስጥ አድሮበታል የሚል እምነት ነበራቸው። በአንዳንድ ጊዜያት እግዚአብሔር ራሱን እንደ አብ፣ በሌላ ጊዜያት እንደ ወልድ፤ አልፎ አልፎ ደግሞ እንደ መንፈስ ቅዱስ አድርጎ ገልጿል እንጂ ምንጊዜም ከስም ልዩነት በቀር የአካል ለውጥ የለውም ሲሉ እነዚህ ሰዎች ያስተምሩ ነበር።

የዚህ እምነት ተከታዮች በመስቀል ላይ የኃጢአታኞችን ዋጋ የተቀበለው እግዚአብሔር አብ እንጂ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አልነበረም ብለው በማስተማራቸው ፅኑ ተቃውሞ ደርሶባቸዋል። በቤተ ክርስቲያ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ አምላክ መሆኑንና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለው አንድነት እንደተጠበቀ ሆኖ የራሱ የተለየ ማንነት እንዳለው የሚያስተምር ነበር። ኦሪጅን ይህንን እውነት በመጠበቅ በ325ዓ.ም. በኒቂያ ለተሰበሰበውና ከዚያም በኋላ ለተደረጉት ጉባኤዎች የኢየሱስን አምላክነት እንዲያውጅ ጥርጊያ መንገድ ከፍቶላቸዋል።

ኦሪጂን የሰው ነፈስ በተደጋጋሚ ሥጋ ለብሶ ይወለዳል፤ አዲስ ነፍስ በቀጥታ በእግዚአብሔር የሚፈጠር እንጂ ከአባት እናት አይገኝም ብሎ አስተምሯል። እግዚአብሔት ፃድቅ ስለሆነ ሁሉ የተፈጠረው በእኩልነት ነው በማለት ተናግሯል። ይሁን እንጂ ሰዎች መላዕክትና አጋንንት እኩል ካለመሆናቸው የተነሣ በተፈጠሩበት ሌላ ዓለማት ላይ የፈፀሟቸው ድሪጊቶች ይህንን ሁኔታ ለውጠታል። ነፍሳት ከድርጊቶቻቸው የተነሣ እንደሚነሡና እንደሚወድቁ እንዲሁም ሽልማት ወይም ቅጣት እንደሚቀበሉ ያምን ነበር። ቅጣት የሚመጣው ለማስተካከል ብቻ እንደሆነና በዘመን መጨረሻ ሰው ሁሉ እንደሚድንም ተናግሯል። ይህ ትምህርት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚስማማ አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከፍልስፍና ጋር ሊያስማማ በመፍጨርጨሩ አንዳንድ የተሳሳቱ ትምህርቶችን አስተምሯል።

የእስክንድሪያው ጳጳስ ዲሜትሪያስ በኦርጂን ላይ በምቀኝነት ተነሥቶበታል። ለ28 ዓመታት የእስክንድሪያ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ በመሆን ካገለገለ በኋላ ዲሜትሪዮስ ኦርጂንን ከሥልጣኑ አስወግዶታል። ከዚያም ኦርጂን ወደ እስራኤል ሄዶ ቂሳርያ በተባለው ሥፍራ ሌላ ትምህርት ቤት በማቋቋም ለ20 ዓመታት አስተምሯል።

ዴሲያን ስደት ባስነሣበት ወቅት ኦርጂን ታሥሮ ነበር። በ254ዓ.ም. ከእስር ከተፈታ በኋላ ቤት ውስጥ ከደረሰበት ስቃይ የተነሣ ወዲያውኑ ሞቷል።

## <u>ማጠቃለያ</u>

በ3ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ ተቀባይነት ያገኙትንና በምዕመናን ፊት በቤተ ክርስቲያን ለመነበብ ተስማሚ ናቸው የተባሉትን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር እንድታዘጋጅ የወቅቱ የእድገት ሁኔታዎች አስገድደዋል። በ1ኛው ምዕተ ዓመት ማብቂያ ላይ ከኢየሱስና ከሐዋሪያት ጋር ይኖሩ የነበሩት የትምህርታቸው መስካሪዎች ከሞላ ጎደል በአጠቃላይ ሞተዋል። አንዳንዶቹ ትውፊቶች ስህተት አዘል በመሆናቸው ሐዋሪያዊ ሥልጣን ያላቸው የትኞቹ ናቸው? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ሆኗል። የኖስቲኮችና ሥላሴን የሚክደው ትምህርት ቤተ ክርስቲያንን አዳክሟታል። በኋላ በአዲስ ኪዳን ጥራዝ ውስጥ ከተጠቃለሉት ጽሑፎች ጋር የማይስተካከሉ ብዙ ጽሑፎች ብቅ ብለዋል። ጥቂት ቡድኖች ጽሑፎቻቸውን በምዕመናን ፊት ተነባቢ ለማድረግ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እንዲያፀድቁላቸው

ይሯሯጡ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ስደት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ እንዲቃጠሉ ስላሳወጀ የሐዋሪያት ዘመን ሐቀኛ ጽሑፎች ለይቶና ሸሽጎ ማስቀመጥ ያስፈለግ ነበር።

በዚህ ወቅት እምነትን የሚጠብቁ አያሌ ድንቅ ሰዎች ተነሥተዋል። ይሁን እንጂ እነዚህ ምሁራን በኋለኛው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮች የሆኑ አንዳንድ ትምህርቶችንም ደግሞ አስተምረዋል።

ኢሬኒዮስ አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠርና በመዋጀት ላይ ያላቸውን አንድነት ጠብቆ አቆይቷል።

ተርቱሊያን ዝነኛ የሆነው በጽሑፎቹ አማካይነት ነው። ጠቅለል ባለ አኳኋን ምናልባት በጣም የታወቀው ጽሑፍ “መከላከያ ሃሳብ” የተሰኘው ሳይሆን አይቀርም። በተጨማሪም ክርስቲያኖች በአራሚ ኅብረተሰብ ውስጥ ሊኖራቸው ስለሚገባው ባህርይ ጽፏል።

ሲፕሪያን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከፍተኛ መንፈሳዊ ብቃት ሊኖራቸው እንደሚገባ አጠንክሮ ተናግሯል። ይሁን እንጂ ጳጳሳት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፍፁም ሥልጣን ሊኖራቸው እንደሚገባ አስተምሯል።

የእስክንድሪያው ክሌመንት የእስክንድሪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ነበር። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአካባቢያቸው ባለው ዓለም ውስጥ በፅናት መቆምና ፍልስፍና፣ ሥነ-ጽሁፍ፣ ሒሳብ ሳይንስና መንፈሳዊ ትምህርት መማር ይገባቸዋል የሚል እምነት ነበረው።

ኦርጂን የሚታወሰው እምነትን ሥርዓት ባለው አገላለፅ በመግለፁና ከመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ አብራሪዎች አንዱ ተደርጎ ነው። የኒቂያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ስለ ክርስቶስ አምላክነት ያለውን አቋም እንዲገልፅ ጥርጊያ መንገድ ከፍቶለታል። ይሁን እንጂ ነፍስ በተደጋጋሚ ሥጋ ስለ መልበሱ ያስተማረው ትምህርት ብዙዎችን ወደ ተለያዩ የስህተት ትምህርቶች መርቷቸዋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በ2ኛ ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ ቤተ ክርስቲያንን ያዳከሟት ሁለት የስህተት ትምህርቶች ምንና ምን ናቸው?
2. “የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍት ዝርዝር” ማለት ምን ማለት ነው?
3. መንፈሳዊ ጽሑፎችን ለመመዘን ቤተ ክርስቲያን የምትጠይቃቸው ሁለት ጥያቄዎች ምንና ምን ነበሩ?
4. ሥልጣን ያለው የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ዝርዝር እንዲዘጋጅ ያደረጉት ሦስት መመዘኛዎች ምን ምንድን ናቸው?
5. “የእምነት መግለጫ” ያስፈለገው ለምን ነበር?
6. የጥንት ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ምን ደርሰበት?
7. በሐዋሪያት ዘመን በሽማግሌዎችና በጳጳሳት መካከል የተደረገው መለያ ምንድን ነው?
8. እስካሁን ድረስ በእኛ እጅ የሚገኙት የኢሬኒዮስ አምስት ጽሑፎች ርዕስ ምንድነ ነው?
9. የካርቴጁ ሲፕሪያን የሚታውሰባቸው ሦስት ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?
10. በ3ኛው ምዕተ ዓመት እስክንድሪያ ዝነኛ የነበረችው በምንድን ነው?
11. በ190 ዓ.ም. የእስክንድሪያ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ማን ነበር?

12.ኦሪጂን ለቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ እውነት ሽንጡን ገትር በመቆም ለኒቂያ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ጥርጊያ መንገድ ከፍቶለታል። በዚህ ወቅት አቢይ መወያያ የሆነ የትምህርተ ክርስትና ነጥብ ምን ነበር?
13.ብዙ የስህተት ትምህርቶችን ያስከተለው የኦሪጂን ትምህርት ምንድን ነው?
14.ኦርጂንን የእስክንድሪያ ትምህርት ቤት አስተዳዳሪነቱን ማዕረግ ነጥቆ ከሥልጣን ያወረደው ማን ነበር? ለምን?

<u>ማስታዎሻ</u> - በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የአዲስ ኪዳን ጥራዝ ማለት በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ጉባኤ የመነበብ መብት ያገኙት የሐዋሪያትና ከእነርሱ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው የሥራ ባልደረቦቻቸው የጻፏቸውና አሁን አዲስ ኪዳን ብለን በምንጠራው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የተጠቃለሉት ጽሑፎች ማለት ነው።

## <u>ምዕራፍ ሦስት - የቤተ ክርስቲያን መከራና ድል</u>

ከ222-235ዓ.ም. በገዛው በእስክንድር ሰቨረስና ከ244-249ዓ.ም. በመራው በአረባዊው በፊልጶስ ዘመነ መንግሥታት የሮም መንግሥት ከቤተ ክርስቲያን ጋር ወዳጅ ነበር፡ የሮማውያን ነገሥታትን ዝርዝር ተመልከቱ። ይህ በሮማዊያን ግዛት ውስጥ በአጠቃላይ ሰዎች ከየሃማኖቶቹ ሁሉ ዓይነተኛ የሆኑትን ነገሮች በመውሰድ የጋራ እምነት እንዲኖራቸው የሚጣጣሩበት ዘመን ነበር። ኦሪጂን ከፊሊጶስ ቄሳር ጋር ያልተቆጠበ የወዳጅነት ግኑኝነት ስለፈጠረ ቤተ ክርስቲያን ለ38 ዓመታት ዕረፍት አግኝታለች። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ቁጥሯ ጨምሮና ክብሯ ከፍ ብሎ ነበር። ከዚህ ቀጥሎ ከ250-260ዓ.ም. በዴሲዮስና በቫሌሪያን አማካይነት አስከፊ ስደቶች ተደርገዋል።

የሮም ግዛት ከየአቅጣጫው በውጫዊ ሕዝቦች ግፊት በስጋት ላይ ወድቃ ነበር። በተለይ ጎቶች የፈፀሙት ወረራ በጣም በጣም ከባድ ነበር። ከ249-251 የገዛው ዲሲዩስ ግዛቱን ለመጠበቅ ዓይነተኛው መንገድ ጥንታዊ የሮም አምልኮን እንደገና ማስጀመር መሆኑን አምኖ ነበር፤ ክርስትናም ጭራሽ መጥፋት ይኖርበታል ብሎ ወስኖ ነበር።

ከ254-260ዓ.ም. በነበረው የቫሌሪያን ዘመነ መንግሥት የአስተዳደር ሁኔታ ከዚህ በከፋ ያልተረጋጋ ነበር። ንጉሡ በአማኞች ላይ የተደረገው ስደት እንዲያገረሽ አምኖበት ነበር። ስለዚህ በጣም ጥበብ የተሞላበትና አስከፊ የሆነ ስደት አስነስቷል። በዚህ ዘመን የካርቴጉ ሲፕሪያንና ሌሎች እስጢፋኖስና ዳግማዊ ሲክስተቱስ የተባሉ ሁለት የሮም ጳጳሳት ተገድለዋል።

ቫሌሪያን ካደረገው ስደት በኋላ ቤተ ክርስቲያን ለ40 ዓመታት ዕረፍት አግኝታለች። ሦስተኛው ምዕተ ዓመት ከማለቁ ቀደም ብሎ በየኑሮ መስኩ ሁሉ ክርስቲያኖች ይገኙ ነበር። በ284ዓ.ም. በሮም ግዛት ምስራቃዊ ክፍል ዲዮክሌቲያን ነገሰ። ዲዮክሌቲያን በግዛቱ ላይ ውድቀት ያስከትላል በሚል ፍራቻ በመጀመሪያው ላይ ምንም ዓይነት ስደት ከማስነሣት ተቆጥቦ ነበር። ይሁን እንጂ በ303ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ሙከራ እንዲያደርግ ጋለሪዩስ ያቀረበለትን ሃሳብ ተቀብሏል። ከዚያም ክርስቲያኖች የአምልኮ ሥፍራዎችና ቅድሳት መጽሐፍት ሁሉ እንዲደመሰሱ ትዕዛዝ አውጥቷል። ህዝቡ የኒኮመዲያን ውብ ቤተ ክርስቲያን ዘረፈ፤ ደመሰሰ፤ እንዲሁም በእጁ የገቡትን መጽሐፍ ቅዱሶች በሙሉ አቃጠለ። ህዝቡም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንም የአምላክ ምስል ባለማግኘታቸው ተደነቁ።

ጋለሪዮስ ያስተዳድረው በነበረው በዲዮክሌቲያን ግዛት ስደቱ በጭካኔ የተሞላ ከመሆኑም በላይ ከሞት በፊት ግርፊያና ሥቃይ ነበር።

በማክሲሚያን ቄሳር ትዕዛዞች አማካይነት በጣሊያንና በአፍሪካ አስከፊ ስደት ተደርጓል። በማክስሚያን ሥር የጎል፣ የቢታኒያና እስፓኝ አስተዳዳሪ የነበረው ኮንስታንቲዩስ ማንንም በሃይማኖቱ ሳቢያ አልገድልም አለ። ኮንስታንቲዩስ - "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ" የሆነ የሰው አካል ያለ አግባብ ጉዳት ሊደርስበት አይገባም ብሏል። ይህንንም አመራሩን ጋለሪዩስ በቄሳርነት በማስክሲሚያንና በዲዮክሌቲያን እግር በተተካበት ወቅትም እንኳ ቀጥሎበታል። በ306ዓ.ም. ኮንስታንቲዩስ ሞቷል።

የኮንስታንቲዩስ ልጅ ኮንስታንቲን በዙፋን ላይ ለመቀመጥ የነበሩትን ተቀናቃኞች ሁሉ ድል አድርጎ የቄሳርነት ማዕረግ ጨብጧል። ጥቅምት 27 ቀን 312 ዓ.ም. ማክሴንቲዮስን ባሸነፈበት ወቅት አንድ መንፈሳዊ መገለጥ አግኝቷል። በግሪክ ቋንቋ "በዚህ ምልክት ድል አድርግ" የሚል ጽሑፍ የተቀረፀበት በእሳት የሚንበለበል መስቀል በሰማይ ላይ አይቷል ተብሎ ተነግሯል። ቀስቃሽ ሃሳቦቹ አንዳንዴ ትክክል አልነበሩም፤ እንዲያውም አልፎ አልፎ የቀድሞ አጉል እምነቶች ያገረሹበት ነበር፤ ይሁን እንጂ በክርስቲያኖች አምላክ ማመኑን ተናግሯል።

የኮንስታንቲን ማመን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት እንዲሁም መልካምና መጥፎ ውጤቶች ለቤተ ክርስቲያን ያስገኘ ነበር። ይኸውም ቤተ ክርስቲያን ሰፊ ነፃነት ብታገኝም በከፍተኛ የአስተዳደር ውሳኔዎች ውስጥ ጣልቃ መግባት ጀምራለች። በ312ዓ.ም. ኮንስታንቲን ከሊሲኒዩስ ጋር ጣምራ ቄሳር ሆኗል። በ313ዓ.ም. ለክርቲያኖች እምነት ሙሉ ነፃነት የሚሰጥ ትዕዛዝ በአንድነት አውጥተዋል። አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሊታደሱና የጠፉ ንብረቶች ሁሉ ሊተኩ ችለዋል። ይህም አዋጅ በምዕራብ ለነበሩት ሁሉ ታይቶ የማይታወቅ የሃይማኖት ነፃነት አጎናፅፏቸዋል። ከ11 ዓመታት በኋላ ኮንስታንቲን ከሊሲኒዩስ ጋር ግጭት ፈጥሮ እርሱን ድል በማድረግ ምሥራቅንና ምዕራብን አዋህዶ በጠቅላላ ግዛት ላይ ነገሠ። ከዚህም በኋላ ክርስትና በሮማዊያን ዓለም ውስጥ በማንኛውም ሥፍራ ሙሉ ነፃነት ተጎናፅፏል።

ኮንስታንቲን ያመነው በይበልጥ ለወታደራዊ ጉዳይ ነበር። ስለ ክርስትና ትምህርት የተገነዘበው ነገር ይህን ያህል ግልፅ አይደለም። በሮም ከነበረው ተቀናቃኙ ከማክሴንቲዮስ ጋር ባደረገው ጦርነት እግዚአብሔር ድል ሰጥቶታል ሲሉ ክርስቲያኖች ያምኑ ነበር። ይሁን እንጂ ኮንስታንቲን በክርስትናና በአራሚ አምላኩ "ድል አድራጊው ፀሐይ" በተባለው ላይ በነበረው እምነቱ መካከል ያለውን ልዩነት በጉልህ አልተገነዘበም። አማኞቹ አሁድ ተሰብስበው ፊታቸውን ወደ ምስራቅ በማዞር ይጸልዩ ስለነበር ብዙ የአራሚ እምነት ተከታዮች ክርስቲያኖች ያመለኩት ፀሐይን ይመስላቸው ነበር ሲል ተርቱሊያን ተነግሯል።

ከ313ዓ.ም. ወዲህ ኮንስታንቲን ራሱን እንደ ክርስቲያን መቁጠሩ የጻፋቸው ደብዳቤዎች ቁልጭ አድርገው ያሳያሉ። ንጉሥ እንደመሆኑ መጠን የተባበረች ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር መጣር እንዳለበት ተሰምቶት ነበር። በ337 ዓ.ም. ህይወቱ እስካለፈችበት ወቅት ድረስ አልተጠመቀም ነበር። በዚያ ዘመን ወንጀለኞችን ማሰቃየትና መግደልን ጨምሮ የመንግሥት ሥራ ያከናውኑ በነበሩ ሰዎች ዘንድ ጥምቀትን እስከ ዕለተ ሞታቸው ማዘግየት የተለመደ ነበር።

ኮንስታንቲን ለምሥራቃዊ ግዛቱ አዲስ ዋና ከተማ ቢዘንታም ላይ ሲመሰርት በዚያ ሁለት ቤተ ክርስቲያኖችን አሠርቷል። ይሁን እንጂ በገበያው ሥፍራ እርሱን የሚመስል ሐውልት ለፀሐዩ አምላክ አስገንብቶለት ነበር። በተጨማሪ እናት አምላክ ለሆነችው ለሲቤልም ደግሞ ሐውልት አሠርቶላታል።

የኮንስታንቲን ክርስትናን መቀበል ጨርሶ ግልፅ ባይሆንም እንኳ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ጥቅሞችን አስገኝቶአል። የመጽሐፍ ቅድስ ቅጂዎችን አባዝቷል፡ በስደት የፈረሱትን አብያተ ክርስቲያናት አሠርቷል። ቤተ ክርስቲያን ለዕርዳታ የምታውለው የገጠር ግብር ገቢም እንኳ እንድታገኝ ወስኗል።

ሕጻናትን፣ ባርያዎችንና እስረኞችን አድኗል። "ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ስለተፈጠረ" ወንጀለኞች ፊታቸውን በእሳት እንዳይጠበሱ የሚከለክል ትዕዛዝ በ316 ዓ.ም. አውጥቷል።

ኃይሉ እየጨመረ ሲሄድ ኮንስታንቲን ትዕቢተኛ ሆኗል። በጣም ውድ የሆኑ ካባዎችን መልበስ ይወድ ነበር፡ ለኢየሩሳሌም ጳጳስም ጥቂት ክባዎችን በሥጦታ መልክ ሠጥቷል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክህነት ልብስ መልበስ የተጀመረውም በዚህ ወቅት ሳይሆን አይቀርም።

ኮንስታንቲን ቄሳር ከጳጳሳት ጋር የጠበቀ ወዳጅነት መሥርቶ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩትን አወዛጋቢ ሁኔታዎች የማረጋጋት ሙከራ አድርጓል። ይሁን እንጂ ይህ የመንግሥት በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ መግባት በኋለኞቹ ዘመናት ከባድ ችግር አስከትሏል። ከአንዳንድ አንጻር ሲታይ ይህ ሕዝብን ረድቶታል፤ ምሳሌ- 1/ የሴቶች ሁኔታ ዕድገት አሳይቷል፤ 2/ የባርነት አስተሳሰብ ተነቅፏል፤ 3/ የጌታ ቀን የአምልኮና የዕረፍት ቀን ተደርጓል። ይሁን እንጂ መንግሥት በሚሰጠው ከፍተኛ ድጋፍ ሳቢያ አንዳንድ ካህናት ታብየዋል።

ከኮንስታንቲን በኋላ ልጆቹ በእርሱ እግር ተተክተው ሥልጣን ይዘው ነበር፤ ሆኖም ልጆቹ የእርሱ ችሎታና የባህሪይ ጥንካሬ አልነበራቸውም። ዘመነ መንግሥታቸውም ያልተረጋጋ ነበር፤ አርዮስ ያስተምረው የነበረውንም የስህተት ትምህርት ተቀብለው መላውን ቤተ ክርስቲያን አስጨንቀዋል።

ከ361-363 ዓ.ም. ጁሊያን የተባለው የኮንስታንቲን የልጅ ልጅ ክርስትናን ክዶ አንድ ዓይነት የአራሚ እምነት እንደገና ለመመስረት ሞክሯል። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት አጎቶቹ ዘመዶቹን ስለገደሉበትና እርሱን ስላጎሳቆሉት ነበር። ይህ ብዙ አማልክትን የማምለክ የአራሚ እምነት በጣም የተግማማ ከመሆኑም በላይ በህዝቡ እንዲመለክ የተደረጉት ሙከራዎች ከሽፈዋል።

## ማጠቃለያ

4ኛው ምዕተ ዓመት የተጀመረው በዲዮክሌቲያን አማካይነት በቤተ ክርስቲያን ላይ በተነሣው በጣም አስጨናቂ ስደት ነበር። ይሁን እንጂ በዚህ በተጠቀሰው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ የአራሚ እምነት ከሞላ ጎደል ክርም ግዛት ጭራሽ ጠፍቷል። በዚህ ዘመን "በሮም የሚገኝ የአሕዛብ መሠዊያ ሁሉ ተትቶና እያንዳንዱም ቤተ መቅደስ ተራቁቶ ነበር" ሲል ጀሮም የተባለው ታሪክ ጸሐፊ ተናግሯል።

ይህ ሁሉ ነፃነት ሲገኝ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መከፋፈል የሚፈጥሩ አንዳንድ ድርጊቶች ተጀምረዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የካህናትን ተግባር፣ ሥርዓቶችንና የገዳማትን ኑሮ ከልክ ያለፈ ማጋነን ጀምረው ነበር። እነዚህም ነገሮች በቤተ ክርስቲያን የወደፊት ሁኔታ ውስጥ አደገኛ ችግሮች ሆነዋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በሦስተኛው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያ እኩሌታ ላይ የቤተ ክርስቲያን ደጋፊ የነበሩት የሁለት ቄሳሮችን ስም ጥቀሱ።
2. በ3ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ቤተ ክርስቲያንን ያሳደዱት ሁለት ቄሳሮች ማንና ማን ነበሩ?
3. ቤተ ክርስቲያን የ40 ዓመታት ዕረፍት ያገኘችው ከማን አገዛዝ በኋላ ነበር?
4. ኮንስታንቲን ክርስቲያኖችን ላለማሳደድ ያቀረበው ምክንያት ምንድን ነው?
5. ኮንስታንቲን ቄሳር የሆነው መቼ ነበር? የቄሳሮችን ቻርት ተመልከቱ።
6. ኮንስታንቲን ተቀብሏል ተብሎ የተነገረለት መንፈሳዊ ራዕይ ምን ነበር?
7. የኮንስታንቲን ክርስትና የተምታታው ከምን ጋር ነበር?

8. ኮንስታንቲን ለቤተ ክርስቲያን ማድረግ እንድሚገባው የተሰማው ነገር ምንድን ነው?
9. ኮንስታንቲን ለቤተ ክርስቲያን ያስገኛቸው አንዳንድ ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?
10. የካህናት ልብስ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሰፋው ማን ነበር? ለምን?
11. ኮንስታንቲን ለቤተ ክርስቲያን የሰጠው ድጋፍ ምን ምን ችግሮች ፈጠረ?
12. የኮንስታንቲን በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ጣልቃ መግባት ለሕዝቡ ያስገኛቸውን ሦስት ጥቅሞች ጥቀሱ።
13. የኮንስታንቲን ልጆች የደገፉት የስህተት ትምህርት ምን ነበር?
14. ጁሊያን እንደገና ሊያስጀምር የሞከረው ነገር ምንድን ነው? ለምን?

## ምዕራፍ አራት - የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ፣ ምዕመናንና ድርጊቶች
## 325-500 ዓ.ም.

በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በሚመለከት ብዙ ጥልቅና መራራ ውስብስብ ክርክር ተፈጥሮ ነበር። አንዳንድ የትምህርተ ክርስትና ጥያቄዎች ማብራሪያ ያሻቸው ነበር። እነዚህም ጥያቄዎች ከተለያዩ አገሮች በተሰበሰቡ ብዛት ባለቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውይይት ተደርጎባቸዋል። ከአራቱ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች የክርስትና እምነትን ፍቺ የሚያጠናክሩ የእምነት መግለጫ ትምህርቶች ተዘጋጅተዋል።

በተለይ በአምስተኛው ምዕተ ዓመት በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ብዙ ግጭት ነበር። በርካታ አሳፋሪ ነገሮች ተወርተዋል፤ ተቃዋሚ ቡድኖችም በጉልበት ኃይል ድል ሊጎናፀፍ ሞክረዋል። ይሁን እንጂ ይህ ግጭት ለሚቀጥለው ትውልድ ዕርዳታ የሚሰጡ አንዳንድ የእምነት አዋጆችን አስገኝቷል።

### የአርዮስ የስህተት ትምህርት

ይህ የስህተት ትምህርት ለጥቂት ዘመን ቤተ ክርስቲያንን የከፋፈለ ከመሆኑም በላይ ለሦስት ምዕት ዓመታት ያህል በክሏት ነበር። አርዮስ በ318 ዓ.ም. ገደማ የክርስቶስን መለኮታዊነት በሚመለከት ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችውን ትምህርተ ክርስትና የሚፃረሩ አመለካከቶች ማስፋፋት ጀመረ። ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ አስቀድሞ ህልውና ያልነበረው መሆኑን አስተምሯል። ክርስቶስ የመጀመሪያው ፍጡር ስለሆነ ከአብ ያንሳል ሲል ተናግሯል።

በ320 ዓ.ም. የእስክንድሪያው ጳጳስ ወልድ የሆነው ክርስቶስ ዘላለማዊና ከአብም ጋር እኩል ነው በማለት አውጇል።

የአርዮስ ዘዴዎች አወዛጋቢ ነበሩ። መወያያ ሃሳቡን ግራ ሊያጋባ ይጥር ነበር። አርዮስ በ312 ዓ.ም. ከሥልጣን ወርዷል። ይሁን እንጂ ጨሌ ከመሆኑ የተነሳ በብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይወደድ ነበር። የኢየሩሳሌሙ ጳጳስ መርቀሪዮስ የኒኮሜደያው አሌቢዊስና የቄሳርያው ታሪክ ጸሐፊ አሌቡዊስን የመሳሰሉት ሰዎች ወዳጆቹ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች የእስክንድሪያውን ጳጳስ ከአርዮስ ጋር ሊያታርቁ ቢሞክሩም አልተሰካላቸውም። በ324 ዓ.ም. የሮም ቄሳር ኮንስታንቲን የቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ጉባኤ ይህንን ችግር እንደያጤን በሰሜን ምዕራብ እስያ ኒቂያ በተባለው ሥፍራ እንዲሰበሰቡ አድርጓል።

የኒቂያውን ጉባኤ ከሞላ ጎደል በእስፔይንና በፋርስ መካከል ከሚገኙት ከሁሉም አገሮች የተወጣጡ 318 ጳጳሳት ተገኝተውበታል። የሮሙ ቄሳር ኮንስታንቲን በዚህ ጉባኤ ላይ ቢገኝም የጉባኤው ሊቀ መንበር ታላቁ ክርስቲያን የኮርዶባው ሆሲዩስ ነበር። ጉባኤውን የተሳተፉት አብዛኛዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች

ለእምነታቸው የተሰደዱ ነበሩ። ለክርስቶስም ካላቸው ፅናት የተነሣ እጅና እግራቸው ተቆርጦ፣ ዓይናቸው ታውሮና ገላቸውም በእሳት ተጠብሶ ነበር። እነዚህ በቀደሙት ነገሥታት አስከፊ ሥቃይ የተቀበሉ ሰዎች አሁን የሮም ቄሳር ኮንስታንቲን ሞገስ ሰጥቷቸዋል።

ውይይቱ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር እኩል ነው ወይስ አይደለም ወደሚለው ክርክር ውስጥ ገብቶ ነበር። ለክርስቶስ አምላክነት ሽንጡን ገትሮ ይከራከር የነበረው ዋናው ሰው ዲያቆን አትናቴዎስ ነበር። ጳጳስ የነበረው አርዮስ ይህንን አስተሳሰብ ተቃውሞታል፤ እነዚህ ሁለቱም ከእስክንድሪያ የመጡ ነበሩ። በመጀመሪያ ላይ አንዳንዶች ደብዛው የጠፋ ማብራሪያ በመስጠት ሁለቱንም ወገኖች ሊያስደስቱ ጥረት አድርገዋል። ይሁን እንጂ በመጨረሻ ላይ ከ220 ልኡካን መካከል 218ቱ አርዮስን ተቃውመውታል። ከዚያም ጉባኤው ክርስቶስ "የእግዚአብሔር ልጅና የአብ እኩያ" መሆኑን አውጇል። ይህም ውሳኔ ከዚያ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እጅግ ጠቃሚ ሆኗል። ይሁን እንጂ የዚህ እምነት ሃሳብ የተገኘው ከዚህ ጉባኤ ነው ማለት ፈፅሞ የተሳሰተ ነው፤ ኢየሱስ ራሱ ቀደም ብሎ አስተምሮት ነበር።

አርዮስና ሁለት ባልደረባዎቹ ኢሊሪያ በተባለው ሥፍራ በግዛት ተቀምጠዋል። ይሁን እንጂ አትናቴዎስ የእስክንድሪያ ጳጳስ ሲሆን አርዮስን ወደ ቤተ ክርስቲያን እባልነቱ አልመልሰውም ስላለ ኮንስታንቲን አትናቴዎስን ትሬቬስ በተባለው ሥፍራ በግዞት አስቀምጦታል። ይህንን ያደረገው የአርዮስን ትምህርት ተቀብሎ ስላልደገፈ ነበር። አትናቴዎስ አምስት ጊዜ በግዞት የተቀመጠ ሲሆን አምስት ጊዜም ምህረት ተደርጎለት ነበር። በነዚህ ወቅቶች ሁሉ በእስክንድሪያ ወደሚገኘው ቤተ ክርስቲያኑ ሲመለስ ልባዊ አቀባበል ተደርጎለታል።

አርዮስ ዳግመኛ ተወዳጅ ለመሆን ብዙ ነገሮች ዶልቷል፤ ኮንስታንቲን በህይወት ሳለ የኒቂያ የእምነት መግለጫ እውነተኛ እምነትነት ምንም ጥርጥር አልነበረውም። ቢሆንም በኒቂያ የእምነት መግለጫ ያልተስማሙት የአርዮስ ወዳጆች የዚህን እምነት መግለጫ ደጋፊዎች የሚያጠቁባቸው መንገዶች ይፈልጉ ነበር። የኒኮሜዲያው ኦሴቡዊስ የአንፆኪያውን ጳጳስ አስታስ የእስክን ድሪያውን ጳጳስ አትናቴዎስና የአንሲራውን ጳጳስ ማርሴሉስ የመሳሰሉ አያሌ ጳጳሳትን ከሥፍራቸው የሚያስወግድባቸው መንገዶች አግኝቶ ነበር። በዚህ ወቅት አርዮስ ሞቶና ወዳጆቹም ረስተውት ነበር። አርዮስ ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ በ337 ዓ.ም. ኮንስታንቲን በኒኮመዲያው ኦሴቡዊስ ተጠምቋል። ኮንስታንቲን ከሞተ በኋላ አርዮስ በፈጠረው ውዝግብ ሦስት ልጆቹ ግዛቱን ሲከፋፈሉ ባስነሡት የአስተዳደር ሁከት ጋር ተደበላልቋል።

አትናቴዎስና ማርሴሉስ ስደተኞች ሳሉ ከ337-352 ዓ.ም. የሮም ጳጳስ የነበረው ጁሊየስ ሊተባበራቸው ሙሉ ፍቃደኛ ሆኖል። ይህም በሮምና በግሪክ ካህናት መካከል ግጭት ሲፈጥር በምሥቅርና በምዕራብ መካከል መከፋፈል ፈጥሯል። የሮሙ ቄሳር ኮንስታንቲኖስ ለግዛቱ ደህንነት ተስማሚ መስሎ ስለታየው የአርዮስን ትምህርት ደግፎታል። "አብያተ ክርስቲያናት የአርዮስ ተከታዮች ሁኑ ሲባሉ በጭንቀት ተውጠው ነበር" ሲል ጀሮም ጽፏል። የአርዮስን ትምህርት ለመቀበል አሻፈረኝ ያሉትን ሰዎች ኮንስታንቲኖስ አሳደቸዋል። የአርዮስን ትምህርት ከሥረ መሠረቱ የተሳሰተ መሆኑን የአንሲራው ባሲልና አትናቴዎስ ያምኑ ነበር። እነዚህ ሁሉት ሰዎች የነበራቸው ፅኑ እምነት የአስተዳደር ግፊቶችን ከመቀበል ይልቅ ግዞት ወይም ሰማዕትነትም እንኳ ቢሆን እንዲመርጡ አድርጓቸዋል።

አርዮስ የፈጠረው ውዝግብ ከ361 — 381 ዓ.ም. ቀጥሏል። ይሁን እንጂ አዳዲስ ሰዎችና ችግሮች ግጭቱን አብርደውታል። በዚህ ዘመን የንጉሡ አቋም ውዝግቡን ሊያባብሰው ወይም ሊያበርደው ይችል ነበር። ከ361 - 363 ዓ.ም. በጁሊያን ዘመን ማናቸውም ቡድኖች ተፅዕኖ አልተደረገባቸውም። በ363 ዓ.ም. ጁሊያን የኒቂያውን የእምነት መግለጫ ደግፎ ነበር፤ ይሁን እንጂ በሥልጣን ላይ የቆየው ለጥቂት ወራት ብቻ ነበር። ቀዳማዊ ቫለንቲኒያን ግዛቱን ወደ ቀድሞው የመከፋፈል ሁኔታው መልሶስታል፤ እርሱ ምዕራባዊውን ግዛት ሲመራ ወንድሙ ቫለንስ ምሥራቃዊውን ይመራ ነበር። ቫለንስ የአርዮስ ተከታይና

የኮንስታንቲኖፓል ጳጳስ የነበረውን አደክሲዮስንና በእርሱ እግር የተተካውን ዴሚፊለስን እንዲያስጠጋቸው ሚስቱ ተፅዕኖ አሳድራበታለች። ከእነዚህ ሁለት ጳጳሳት ጋር ለመተባበር እምቢተኛ የሆኑት ተሰደው ነበር።

በዚህ ዘመን የሥላሴን ትምህርትና የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት የሚመለከቱ አዳዲስ ችግሮች ተፈጥረዋል።

በ378 ዓ.ም. ቫለንስ ከሞተ በኋላ የምዕራባዊው ግዛት ገዢ ቴኦዶሱስ በ381 ዓ.ም. የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በኮንስታንቲኖፐል እንዲሰበሰብ ጥሪ አድርጓል።

## የኮንስታንቲኖፐሉ ጉባኤ

ቴኦደሱስ ጉባኤውን የሰበሰበው በግንቦት ወር 381 ዓ.ም. ነበር። የጉባኤው ሊቀ መንበርም የአንፆኪያው ሚሊቲዮስ ነበር። ይሁንና በጉባኤው ላይ እንዳሉ ሜለቲዮስ ስለሞተ እርሱን የሚተካ ሰውና የኮንስታንቲኖፐልን ጳጳስ ለመሾም ግጭት ተፈጥሯል። ከሚሊቲዮስ ካህናት መካከል ፍላቪያን የተባለው በአንፆኪያ የእርሱ ተተኪ እንዲሆን ጉባኤው ወስኖአል። የኮንስታንቲኖፐል ጳጳስ እንዲሆን የተመረጠው የመንግሥት ባለሥልጣን የሆነው ኔክታሪዮስ ነበር።

"ክርስቶስ ከአብ ጋር የባህርይ ልዩነት የለውም" በማለት ጉባኤው የኒቂያውን የእምነት መግለጫ እንደገና አፅድቋል። ቢሆንም የእምነት መግለጫው መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ያለውን ዝምድና ለማብራራት ጥረት አድርጓል ይኸውም መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር ይመለካል፣ ይከበራል በማለት ነበር። ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላ ይህ ሐረግ ደግሞ በምዕራብ የላቲን አብያተ ክርስቲያናትና በምሥራቁ የግሪክ አብያተ ክርስቲያናት መካከል ብዙ ውዝግብ ቀስቅሶአል። "ኮንስታንቲኖፐል አዲሲ ሮም ስለሆነች ጳጳሷ ከሮም ጳጳስ ቀጥሎ ያለውን ማዕረግ ያገኛል" የሚለውም የጉባዔው የመጨረሻ ዐረፍተ ነገር ብዙ ግጭት ፈጥሯል። ከዚህ ቀደም ይህ ሥልጣን የተሰጠው ለእስክንድሪያ ነበር።

ጉባዔው ያስተላለፋቸው ትምህርተ ክርስትናን የሚመለከቱ ውሳኔዎች የአርዮስ ተከታዮች ቤተ ክርስቲያንን በቁጥጥራቸው ሥር ለማዋል ያደረጓቸውን ጥረቶች ገትተዋል።

## የኤፌሶን ጉባዔ - 431 ዓ.ም.

የኮንስታንቲኖፐል ጉባዔ የክርስቶስን እውነተኛና ፍፁም ሰብአዊነት አውጀአል። ከዚያም ሌላ ጥያቄ ተፈጥሯል። ይኸውም - ክርስቶስ ፍፁም መለኮታዊና ሰብአዊ ከሆነ ማንነቱ የተከፈለ ይሆናል ወይስ አይሆንም? የሚል ነበር።

የኮንስታንቲኖፐሉ ጳጳስ ኔስቶሪዮስ ክርስቶስ ሰብአዊና መለኮታዊ ባህርያት ሲኖሩት ማንነቱ የተከፈለ ነው ብሎ ተናግሯል። የክርስቶስ ሰብአዊ ህይወት የቀመሳቸውን ሥቃዮች መለኮታዊ ተፈጥሮው አልተካፈለም ብሏል። ይሁን እንጂ የእስክንድሪያው ጳጳስ ቂሪሎስ እንደዚህ ማለት ኃጢአተኛ የሚድነው በአንድ ሰው ሥቃይ ነው፤ ሰው ግን ማዳን አይችልም ሲል ጠቁሟል። ይህም ውዝግብ ዳግማዊ ቴኦደሲዮስ የቤተ ክርስቲያንን ጉባዔ በኤፌሶን እንዲሰበሰብ አድርጎታል። አብዛኞቹ ልዑካን የክርስቶስ ማንነት ያልተከፈለ ነው ብለው ተከራክረዋል። ኔስቶሪዮስ ይህንን ሃሳብ ለማክሸፍ ሲል የክርስቶስ ማንነት የተከፈለ መሆኑን ተናግሯል።

የኔስቶሪዮስ ተከታዮች ከመድረሳቸው በፊት ጉባዔው ትምህርታቸውን አልቀበልም ስላለ እነርሱም በፊናቸው ተቀናቃኝ ጉባዔ አካሂደዋል። ንጉሡም የኔስቶሪዩስን ተከታዮች የሚቃረን ውሳኔ በወሰነበት ወቅት መንነው ገዳም ገብተዋል።

ኦቲቾስ (ዩቲከስ) የተባለ በኮንስታንቲኖፕል አካባቢ የሚገኝ የአንድ ደብር አለቃ ክርስቶስ ሰው ከሆነ በኋላ ሁለቱ ተፈጥሮዎች ተዋህደው አንድ ስለሆኑ ሁለት የተለያዩ ተፈጥሮዎች ጨርሶ ምንም ልዩነት የላቸውም በማለት ማስተማር ጀምሯል። ይህም የክርስቶስን ሁለት ተፈጥሮዎች በሚመለከት የተነሣውን ውዝግብ አባብሶታል።

ካህናት ማግባት የለባቸውም የሚለው ትምህርት በመስፋፋት ላይ ነበር። ብዙዎች ማርያም ምንጊዜም ድንግል ስትሆን "የእግዚአብሔር እናት" ተብላም ተጠርታለች ሲሉ አስተምረዋል። ማርያም የሰብአዊው ኢየሱስ እናት እንጂ የአምላክነቱ አይደለችም በማለት ኔስቶሪዮስ ይህንን ሃሳብ ተቃውሟል። ይህ የኔስቶሪዮስ ተከታዮች አስተሳሰብ ተስፋፍቶ በአሁኑ ዘመን በፋርስ የሚገኘውን የተለየ የኔስቶሪዮስ ተከታዮች ቤተ ክርስቲአይን እንዲፈጠር አድርጓል። ንጉሡም ይህ እንዳይሆን ሞክሮ ነበር፤ ይሁን እንጂ በ625 ዓ.ም. እስላሞች ስደት ቢያስነሡም እንኳ እስከ ቻይና ሊስራጭ ችሏል።

ከኤፌሶኑ ጉባዔ 20 ዓመታት በኋላ የኔስቶሪዮስን ትምህርት የተቃወመው ኦቲቾስ የመናፍቅ ትምህርት አስተምሯሃል ተብሎ ተከሷል። ኦቲቾስ ይዞት የነበረው ሃሳብ ክርስቶስ መለኮታዊ ተፈጥሮ ብቻ አለው የሚለውን ነበር። በቀልሴዶኑም ጉባኤ ተወግዟል።

## የቀልሴዶን ጉባዔ - 451 ዓ.ም.

የጉባዔው ውሳኔ ክርስቶስ በእርግጥ አምላክ በእውነትም ሰው መሆኑን ሁለቱ ተፈጥሮዎች መደበላለቅ፣ ለውጥ፣ መከፋፈል ወይም መለያየት ሳይኖር ተዋህደዋል የሚል ነበር።
ይህ ጉባዔ ቀድም ተብሎ እንደተደረጉት ቁርጥ ያለ መረጋጋት አላስገኘም። አንዳንዶች አሁንም ክርስቶስ አንድ ተፈጥሮ ብቻ አለው የሚለውን የኦቲቾስን ትምህርት እንደያዙ ነበሩ። እነዚህም ለኦቲቾስ ትምህርት ደጋፊዎች አመለካከት ተስማሚ የሆኑ ለውጦችን አድርጎ የቀልሴዶኑን የእምነት መግለጫ ትምህርት ያጸደቀው ሌላ ጉባዔ በ553 ዓ.ም. በኮንስታንቲኖፕል እንዲሰበሰብ ሊያስገድዱ ችለዋል።

ይህ ክርስቶስ አንድ ተፈጥሮ ብቻ እንዳለው የሚያስተምረው ትምህርት ባሁኑ ዘመን በሶሪያ ያዕቆባውያንና ምናልባትም በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታመንበታል።

## ታላቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች

### የፓንቲየሩስ ሒላሪ - 315 — 368 ዓ.ም.

ሒላሪ የላቲን ሥነ-ጽሑፍ ያጠናና በ350 ዓ.ም. ክርስቶስን የተቀበለ ሰው ነበር። የትውልድ ሀገሩ የፓንቲየርስ ጳጳስ እንዲሆን ተሹሞ ነበር። መጸሐፍ ቅዱስን አጥንቼ አምኜበታለሁ የሚለውን የኒቂያ የእምነት መግለጫ ትምህርት ተቀብሎ ነበር። የመንፈሳዊ ትምህርት ጽሑፎቹ ብዙና ግሩም ነበሩ።

### የሚላኑ አምብሮስ - 340 — 397 ዓ.ም.

አምብሮስ ሕግ የተማረ በጣሊያን ውስጥ በአስተዳደር ሥራ ላይ የተሾመ ሰው ነበር። በ374 ዓ.ም. የሚላን ጳጳስ ሲሞት በምትኩ እርሱ ጳጳስ እንዲሆን ተመርጧል። ጳጳስ በሆነበትም ወቅት ሐብቱን ሁሉ ለድሃ አከፋፍሏል። አምብሮስ ታላቅ መምህርና ሰባኪ ሲሆን የማይፈራ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል የነበረውን ግኙኝነት በሚመለከት ያቀረበው ትምህርት ለብዙ ትውልዶች ጠቃሚ ሆኗል። "ንጉሥ የቤተ ክርስቲያን አካል እንጂ የበላይ አይደለም" ሲል ተናግሯል። ምዕራባዊያን ግዛት ያላግባብ ከነጠቀው ከማክሲሙስ ጋር አልተባበርም ብሏል። ቴኦዶሲዮስን እንኳ ወንበዴዎች በተሰሎንቄ እንዲጨፈጨፉ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ ለ8 ወራት ያህል ቤተ ክርስቲያን እንዳይገባ

ከልክሎታል። ድፍረቱ እስከመጨረሻ ያው ነበር፤ እጅግ ብርቱ የነበሩትን መሪዎችም ተቋቁሟቸዋል። ህይወቱም የአውግስቲንን ህይወት ማርኳል።

## ኦሬሊዮን አውግስቲን - 354 — 430 ዓ.ም.

የአውግስቲን አባት አራሚ ሲሆን እናቱ ክርስቲያን ነበረች። በእናቱ ማግባባትና ፀሎቶች በጣም ተማርኳል። በክርቴጅ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ በነበረባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ህይወቱ ጋጠወጥ ነበር። በሲሰሮ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በአርስቶትልና በአዲሱ የፕሌቶ እምነት ጽሑፎች ተማርኮ ነበር። ለብዙ ዓመታት "እግዚአብሔር ሆይ! ንፅህናና ራስን መግዛት ስጠኝ፤ ነገር ግን ካሁኑ አትስጠኝ" ብሎ ፀልዮአል።

አውግስቲን በመንግሥት ተቀጥሮ የንግግር ስልት መምህር በነበረበት ወቅት ከጳጳስ አምብሮስ ጋር ይተዋወቃል። የአእምሮውና የልቡ ግጭት በጣም ታላቅ በመሆኑ እናቱ አዘውትራ ትነግረው የነበረውን ክርስቶስን ተቀብሎታል። መንፈሳዊ ለውጡም ፍጹም ስለነበር አቢይ ትምህርቱ ልክ እንደ ሐዋሪያው ጳውሎስ የእግዚአብሔር ጸጋ ሆኗል።

አውግስቲን በ395 ዓ.ም. በሰሜን አፍርካ ሂፖ በተባለው ሥፍራ ጳጳስ ሆኗል። መጽሐፍ በመጽሐፍ ላይ አያከታተለ ጽፏል፤ ከእነዚህ መካከል በጣም ተወዳጅ የሆኑት በኃጢአትና በፀጋ ላይ የተጻፉት ነበሩ። አንድ የእንግሊዝ መነኩሴ የአዳም ኃጢአት አለመኖሩን በካዳበትና ኃጢአተኛም ራሱን ሊያድን እንደሚችል በተናገረበት ወቅት አውግስቲን በእግዚአብሔር ፀጋ አማካይነት ካልሆነ በቀር ማንም እግዚአብሔርን ከልቡ ሊወድና በእርሱም ሊያምን እንደማይችል በጥብቅ ገልጿል። በኋለኛው ዘመን ሉተርና ኬልቪን ይህንን ትምህርት በጣም ተቀብለውታል።

አውግስቲን ውድ ከተማው ሂፖ ተወራ ሳለች በ430 ዓ.ም. ሞተ። አውግስቲን በዘመኑ ወደር የማይገኝለት ክርስቲያን መምህር ነበር። ይሁን እንጂ ባህልና ሥርዓቶችዋን ጨምሮ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ደህንነት እንደሌለ ያስተማረው ትምህርት ብዙ ግራ መጋባት ፈጥሯል። በተጨማሪ ሙታን በመከራ አማካይነት እንደሚነፁ የሚያስረዳውን ትምህርትና በገዳማት ውስጥ የመኖርን አስፈላጊነት አስተምሯል። ይሁንና ትምህርቱ የብዙ ክርስቲያኖችን ህይወት ነክቷል።

## ሦስቱ የቄጳዶቂያ ሰዎች

1. 329 — 379 ዓ.ም. - የቄሳሪያው ጳጳስ ታላቁ ባሲል
2. 332 — 394 ዓ.ም. - ወንድሙ የኒሳው ግሪጎሪና
3. 330 — 390 ዓ.ም. - ወዳጃቸው የናክሲያንዙስ ግሪጎሪ

እነዚህ ሦስት ሰዎች ለክርስቶስ ሲሉ ራሳቸውንና ሀብታቸውን ለመስጠት ዝግጁ የሆኑ ሁለንተናቸውን ያስረከቡ ክርስቲያኖች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች የኒቂያው የእምነት ትምህርት ደጋፊዎች ጥቃት ሲደርስባቸው ይህንን ትምህርት ለመጠበቅ በድፍረት ቆመዋል።

ጆን ክርሶስቶም ወይም ዮሐንስ አፈወርቅ - 347 — 407 ዓ.ም.

ክሪሶስቶም በቅድሚያ አንፆኪያ ከዚያም የኮንስታንቲኖፕል ጳጳስ ነበር። ታላቁ ምሁርና ከቤተ ክርስቲያን ታላላቅ መሪዎች መካከል አንዱ ነበር። ስሙ ሲተረጎም "ዮሐንስ አፈወርቅ" ማለት ነው። ታማኝ በሆነው የንስሐ ትምህርቱም ንግሥት አዶክሲያን አስቀይሟታል፤ በዚህም ሳቢያ በ403 ዓ.ም. ከሥልጣኑ ወርዶ

በግዞት ተቀምጧል። እስረኛ ሆኖ ፒቲዮስ ወደ ተባለው በጥቁር ባህር አካባቢ ወደሚገኘው ሥፍራ በመወሰድ ላይ ሳለ በደረሰበት መንገላታት ሞቷል።

## ጀሮም - 340 — 420 ዓ.ም.

ጀሮም ድልማጢያ በተባለው ሥፍራ ተወለደ። "ቮልጌት" የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ የላቲን ቅጂ የእርሱ ሥራ ውጤት ነው። ለ34 ዓመታት ያህል በቤተልሔም በዋሻ ውስጥ በመኖር በርካታ መጽሀፍት ጽፏል። ተገልሎና ሳያገባ በጃንደረባነት ስለመኖር የሚያስተምረውን የመናኝነት ትምህርት በመደገፍ ተሟግቷል። ይሁን እንጂ ዓለም አጅግ የተገለሉትን ሥፍራዎች እንኳ ሳይቀር እንዳጥለቀለቃቻቸው ተረድቷል።

ጀሮም በቶሉ ቱግ የሚልና በጣም ትዕግሥት የጎደለው ሰው ነበር፤ ቢሆንም ፍንክች የማይል ባህርይ ስለነበረውና ታላቅ ምሁር በመሆኑ የተደነቀ ሰው ነበር።

## ቀዳማዊ ሌዮ ወይም "ታላቁ ሌዮ" — 390 — 461

ሌዮ ቱስካኒ በተባለው ሥፍራ የተወለደ፣ በጳጳስ ሴሌስቲን ሥር ዲያቆን የነበረና በሣልሳዊ ሲክስቱስ ምትክ የሮም ጳጳስ የሆነ ሰው ነበር። ሌዮና በምትኩ ከእርሱ በኋላ በሮም የሚቀመጡ መሪዎች ብቻ "ጳጳስ" ተብለው እንዲጠሩ የቀልሴዶኑ ጉባዔ ሲስማማ "የጳጳሳት ቁንጮ" እንዲባል ያቀረበውን ጥያቄ ግን ውድቅ አድርጎታል።

ሌዮ የሮም ጳጳስ በጳጳሳት ቁንጮነት እንዲታወቅ አቅሙ የፈቀደለትን ያህል ተፍጨርጭሯል። ጴጥሮስ የጳጳሳት ቁንጮነት ስልጣን ተቀብሏል ሲል ለማቴ 16፥18 አዲስ ትርጉም ሰጥቶታል። የሌዮ ትርጉም ከአምብሮስ፣ ከጅሮምና ከአውግስቲን አተረጓጎም የተለየ ነበር። ሣልሳዊ ቫለንቲያን የተባለው ንጉሥ የጳጳሱን ትዕዛዛት መጋፋት ሕግን መጣስ ነው ሲል አውጇል።

የጳጳሳቱ ቁንጮ ለመሆን ያቀረበውን ጥያቄ የቀልሴዶኑ ጉባዔ ቢያፀድቀውም ግሪክ ተናጋሪ የሆኑት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ማለትም ቢዘንታይም ሶሪያና ግብፅ ከልብ አልተቀበሉትም። የሌዮ ሃሳቦች በኋለኞቹ ዘመናት ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድረዋል።

## ተለዋጭዋ ዓለም - 400 — 500 ዓ.ም.

አምስተኛው ምዕተ ዓመት የሮም ግዛት በወራሪዎች እጅ የወደቀችበት ዘመን ተደርጎ ይታሰባል።

ቅንጦት መሻት ብዙዎችን ወደ ከተሞች እንዲፈልሱ አድርጓቸው ነበር። የገጠር አካባቢዎች የህዝብ ብዛት የሳሳና የጀርመን ጎሳዎች ድንበሮችን ቀስ በቀስ እየገፉ ነበር። በ410 ዓ.ም. አላሪክ ወደ ሮም ገብቶ ዘረፉ አከናውኗል፤ ጀሮም በቤተልሔም ዋሻው ውስጥ ነበር፤ እርሱና ሌሎች ብዙ ሰዎችም የሮምን ውድቀት ሲሰሙ አልቅሰዋል።

ወረራውን ካካሄዱት አብዛኛዎቹ ጎሳዎች በሮማና በሌሎች ሥፍራዎች የብዙ ክርስቲያኖችን ህይወትና የቤተ ክርስቲያን ንብረት ያዳኑት "የአርዮስ ተከታይ የሆኑ ክርስቲያኖች" ነበሩ።

የመጨረሻው የሮማዊያን ሠራዊት ጎልንና ጣሊያንን ለማዳን ከእንግሊዝ የተነሣው በ410 ዓ.ም. ነበር። በጭካኔ የተሞሉ የአራሚ ጎሳዎች ጁስታውያን፣ አንግላዊያንና ሳክሶናውያን የሰሜንን ባህር በማቋረጥ ከሰሜናዊ ጀርመን መጥተው በምሥራቅ ኢንግላንድና በደቡብ ምሥራቅ እስኮትላንድ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ደምስሰዋል። የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ምንም ሳይደርስባት ያለፈች ሲሆን በምዕራብ

እንግሊዝና በአየርላንድ ብርቱ ነበረች። የኢንግላንድ ቤተ ክርስቲያን በምሥራቅ አራሚዎች አማካይነት ከአውሮፓ አብያተ ክርስቲያናት ተለይታና በዚህም ዘመን በአውሮፓ ከደረሱት ከአብዛኛዎቹ መንፈሳዊ ውድቀቶች ተጠብቃ ነበር።

ወራሪዎቹ ሮምን በቁጥጥራቸው ሥር ሲያደርጉ የጥንት ሮማዊያን ባህል ተለውጧል። አብዛኛዎቹ ወራሪዎች የሮምን ክርስትና ተቀብለው ክርስቲያኖች ቢሆኑም ይህ ለክርስትና በጣም አስቸጋሪ ነበር። አንድ የጀርመን ጎሳዎች ቡድን ንጉሥ የነበረ ክሎቪስ የተባለ ሰው ከ3000 ወታደሮቹ ጋር ተጠምቋል። ይህም የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ይዘት ዝቅ እንዲል ሲያደርግ ብዙ ስህተቶችና አጓጉል እምነቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን አስገብቷል።

የሮማዊያን ግዛት ውድቀት ወደ ኮንስታንቲኖፕል የተዛወረውን የሮምን ጳጳስ ክብር ከፍ አድርጎታል። ከዚያም ኮንስታንቲኖፕል "አዲሷ ሮም" የሚል አዲስ ስም ተሰይሞላታል። አላሪክ ወደ ሮም ከተማ ሲገባ ብዙ ልዑላንና ቤተሰቦቻቸው ወደ እስራኤል ኮብልለው ጀሮም በደስታ ተቀብሏቸዋል። የጥንታዊ ሮም ማሽቆልቆል ለኮንስታንቲኖፕል ከፍ ያለ ሥልጣን አስገኝቶላታል።

<u>ማጠቃለያ</u>

ቤተ ክርስቲያን ከአራሚ መንግሥታት ይልቅ ክርስትናን በሚደግፉ ነገሥታት ሥር ያነሰ ነፃነት እንዳላት ለመገንዘብ ምንም ያህል ጊዜ አልፈጀባትም። ለቤተ ክርስቲያን አመራር በመንግሥት በተሾሙት ሰዎች ላይ የነበረው ተፅዕኖ በኮንስታንቲን ዘመንም እንኳ ተከስቶ ነበር። ለመሪነት የሚመረጠው ሰው በጎረቤት አብያተ ክርስቲያናትም መታወቅ ስለነበረበት የአንድ አጥቢያ ማኅበረ ምዕመናን ነፃነት ውሱን ነበር። አንዲት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መከፋፈል ቢያጋጥማት ጉዳዩ የሚወሰነው በመንግሥት ባለሥልጣን ነበር። በ381 ዓ.ም. ገደማ ጥንታዊ ሮም ስትዳከም "የምሥራቅ ፓትሪያሪኮች" ማለት የእስክንድሪያ የአንፆኪያ የኮንስታንቲኖፕል እና በኋላም የኢየሩሳሌም ጳጳሳት ተጨማሪ ሥልጣን ጨብጠዋል። ይህም በጆን ክርሶስቶምና በኔስቶሪዮስ መካከል ለተፈጠሩት ግጭቶች ከፊል ምክንያት ነበር።

በክርስቲያን ነገሥታት ዘመን መናፍቅ ወይም አላማኒ መሆን ለግዛቱ ታማኝ እንዳለመሆን ይቆጠር ነበር። ከዚያም በቤተ ክርስቲያን ጉባዔዎች ሥልጣናቸውን የተገፈፉ ሰዎች የአስተዳደር ችግር እንዳያስነሡ ለመከላከል ወዲያውኑ በመንግሥት ባለሥልጣናት አማካይነት ወደ ግዞት ይወሰዱ ነበር።

በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ቤተ ክርስቲያን ከሞላ ጎደል ኅብረተሰብን በአጠቃላይ በቁጥጥሯ ሥር አድርጋለች። አንድ ጳጳስ ለህዝቡ ቁሳቁሳዊ ፍላጎቶች ተሟጋችና መንፈሳዊ መጋቢ መሆን ይጠበቅበት ነበር። በኅብረተሰቡ ውስጥ ብዙ የተሳኩ ክንዋኔዎች የሚገኙት ንግግሩ ለተገቢ ባለሥልጣናት ተግባር የሚሰጥ፣ ለፀጥታ አስከባሪ ወይንም ለግብር ሰብሳቢ ሹማምንት ዕርዳታ የሚለግስ የበላይ ጠባቂ ሲኖር ነው። ከዚያም ወዲያውኑ በሰማይ ተሰሚነት ሊኖራቸው የሚችሉ ቅዱሳን የባላይ ጠባቂዎች ሆነዋል። አንዳንዴም የጳጳሳት አማላጅነት በፍትሕ መካከል ጣልቃ ገብቷል።

ባሕታዊነት ወይም ለአንድ የበላይ አየታዘዙ በማኅበር መንኖ ገዳም መግባት ደግሞ የሚመረጥ ነበር። ከዚህ በኋላ ገዳማት ወዲያውኑ በኅብረተሰቡ ውስጥ ኃላፊነት መሸከም የሚሸሹ ወይም ኪሳራ የደረሰባቸውና የወንበዴዎችም ጭምር መጠራቀሚያ ሆነዋል። አንዳንዶቹ ምንም ሥራ ሳይሠሩ በምፅዋት መተዳደር የሚፈልጉ ነበሩ። ሌሎች ደግሞ አጓጉል ሥጋቸውን ማዳከሚያ ዘዴዎችን ይጠቀሙ ነበር።

ከኮንስታንቲን ዘመን ወዲህ የሮም ነገሥታት የጀርመን ጎሳዎችን በወታደርነት መጠቀም ጀምረው ነበር። እነዚህም ጎሳዎች አስተዳደርና ኅብረተሰብ ነክ የሆኑ ሁከቶችን መፍጠር ጀምረዋል። በኋላም የሮምን ውድቀት ያስከተለውን የሮማዊያን የአስተዳደር ሥልጣን ነጥቀዋል።

ወራሪዎቹ ግዛቱን በቁጥጥራቸው ሥር ባደረጉበት ወቅት ብዙዎቻቸው በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተጠምቀዋል። ይህም የምዕራብ ቤተ ክርስቲያንን ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል፤ ቤተ ክርስቲያንም ለእርዳታ ወደ እነርሱ እንድትመለከት አድርጓታል። አምስተኛው ምዕተ ዓመት በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል በተመሰረተ ብርቱ መተሳሰር አብቅቷል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ከ325-500 ዓ.ም. ያለውን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ዘመን በአጭሩ አስረዱ።
2. የአርዮስ ተከታዮች የክርስቶስን አምላክነት በሚመለከት ምን አስተማሩ?
3. የመጀመሪያውን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የሰበሰበው ማን ነበር? በስንት ዓ.ም.? በየት ከተማ?
4. የኒቂያውን ጉባኤ የተካፈሉት እነማን ነበሩ? የእነዚህን ሰዎች ማንነት ግለፁ።
5. የኒቂያው ጉባኤ አቢይ መወያያ ርዕስ ምን ነበር?
6. በክርስቶስ አምላክነት ላይ በተፈጠረው ጥያቄ ከፍተኛ ድምፅ አግኝቶ ያሸነፈው የትኛው ቡድን ነበር? በምን ያህል ድምፅ?
7. በኒቂያው ጉባኤ የክርስቶስን አምላክነት ይደግፍ የነበረው ዋና ተሟጋች ማን ነበር? ምን ያህል ጊዜስ ከቤተ ክርስቲያኑ ተገልሎ ነበር?
8. አርዮስ እንደገና ተወዳጅ ለመሆን የተጠቀማቸው ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?
9. አሲቦዮስ የአርዮስን እምነት የሚቃወሙትን ያጠቃቸው እንዴት ነበር?
10. ግሪክ ተናጋሪ በሆኑት የምሥራቅና ላቲን ተናጋሪ በሆኑት የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት መካከል መለያየት የፈጠረው ምንድን ነው?
11. ንጉሥ ኮንስታንቲዮስ የአርዮስን እምነት የደገፈው ለምንድን ነው?
12. በ361ና በ381 ዓ.ም. መካከል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጠሩት ውዝግቦች ምን ምንድናቸው?
13. ሁለተኛው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የተደረገው መቼና የት ነበር? ሰብሳቢውስ ማን ነበር?
14. እንደገና በኮንስታንቲኖፕል ጉባዔ የፀደቀው ነገር ምንድን ነው?
15. መንፈስ ቅዱስን በሚመለከት የኮንስታንቲኖፕል ጉባኤ የሰጠው መግለጫ ምንድነው?
16. ከፍተኛው ውዝግብ ያስነሣው ጳጳስን በሚመለከት ጉባዔው የሰጠው የመጨረሻ መግለጫ ምን ነበር?
17. የኮንስታንትኖፕል ጉባኤ የፈጠረው ጥያቄ ምንድነው?
18. ኔስቶሪዮስ ጥያቄውን ሊመልስ የሞከረው እንዴት ነበር?
19. ጳጳስ ቄሪሮስ የጠቆመው የኔስቶሪዮስ ስሕተት ምን ነበር?
20. የኤፌሶኑን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የጠራው ማን ነበር?
21. ጋብቻንና ማርያምን በሚመለከት የተሰጠው ትምህርት ምን ነበር?
22. የኔስቶሪዮስ ተከታታዮች ቤተ ክርስቲያን እስካሁን የሚገኘው የት ነው?
23. የቀልሴዶኑ ጉባኤ የክርስቶስን ሁለት ተፈጥሮዎች በሚመለከት የሰጠው ውሳኔ ምን ነበር?
24. የክርስቶስን ማንነት ከፋፍለው የሚያስተምሩ ምሁራን አሁንም ይኖራሉ? ይህ ትምህርት ይሰጥ የነበርው የት ነበር? ይህንን ትምህርት በመጀመሪያ ያስተማረው ከኮንስታንቲኖፕል አካባቢ የሚገኘው ደብር ዓለቃ ማን ይባላል?
25. የፖንቲየርሱ ሒላሪ የደገፈው የእምነት መግለጫ የትኛው ነው?
26. ቤተ ክርስቲያንንና መንግሥትን በሚመለከት የሚላኑ አምብሮስ ምን አስተማረ?
27. የአውግስቲን አቢይ ትምህርት ምን ነበር?
28. ደህንነትንና ቤተ ክርስቲያንን በሚመለከት አውግስቲን ያስተማረው ምንድነ ነው?
29. ሦስቱ የቁጽደቂያ ሰዎች ማን ማን ነበሩ? የትኛውን የእምነት መግለጫ የደገፉ ነበር?
30. ጆን ክሪሶስቶም ማን ነው? የስሙ ትርጉም ምንድነው? ንግሥት ኦዶክሲያን ያስቀየማት ትምህርቱ ምን ነበር?
31. ጀሮም በተለይ የሚታወቀው በምንድን ነው?

32. ታላቁ ሌዮ ማቴ 16፡18ን የተረጎመው እንዴት ነበር?
33. የሮማውያን ግዛት በሚመለከት በአምስተኛው ምዕተ ዓመት በተለይ የሚታወሰው ነገር ምንድን ነው?
34. በሮም ግዛት የገጠሩን ህዝብ ብዛት ያሳሳው ምንድን ነው?
35. ብዙዎቹ የምሥራቅ ኢንግላንድና የደቡብ ምሥራቅ እስኮትላንድ አብያተ ክርስቲያናት በሰሜናዊ ጀርመን አራሚ ጎሳዎች ሲደመሰሱ በምዕራብ እንግሊዚና አየርላንድ የምትገኘው የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ምን ደረሰባት?
36. በክሎቪስ ዘመን የቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ይዘት ዝቅ ያደረገው ምን ነበር?
37. ጀሮም የሮምን ጳጳስ ክብርና ሥልጣን ከፍ ያደረገው በምንድንነው?

## ምዕራፍ አምስት - የመካከለኛው ዘመን ጅማሬ

በስድስተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ የግሪክና የሮም ባህሎች ተቀባይነታቸው ቀንሷል። የጀርመንና የሮማዊያን አስተሳሰቦች በመደበላለቃቸው አዳዲስ አመለካከቶች ብቅ በማለት ላይ ነበሩ።

በጣሊያን ውስጥ የብዙ ሰዎች ሕይወት በጦርነትና በረሃብ አልቆ ነበር። ሎምባርዶች በ568 ዓ.ም. ሰሜናዊ ጣሊያንን ይዘዋል። እነዚህ ሰዎች በአርዮስ ትምህርቶች አማካይነት ከአራሚ እምነት ወደ ክርስትና ተለውጠዋል። የእነዚህ ሰዎች መኖር ጳጳሳትን በሥጋት ላይ ጥሏቸው ነበር።

በ476 ዓ.ም. የሮማውያን ግዛት ከወደቀ ወዲህ ከጣሊያን ውጪ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ክብር እንደገና አልተመለሰም። በእስፔይን በፈረንሳይና በግሪክ የሮም ጳጳስ የነበረው ተቀባይነት ቀንሷል። እንዲያውም በሰሜን አፍሪካ ከሞላ ጎደል ጨርሶ ጠፍቷል።

ከጀርመን ጎሳዎች መካከል ክርስትናን በመጀመሪያ የተቀበሉት ፍራንካውያን ነበሩ። አራሚው የፍራንካዊያን ንጉሥ ክሎቪስ በ496 ዓ.ም. ክርስትናን ተቀብሏል። ይሁንና የዚህ ንጉሥ ክርስትናን መቀበል ገና የሮምን ጳጳስ ሥልጣን ከፍ አላደረገውም።

በ586 ዓ.ም. ሬካርድ የተባለ የእስፔይን ንጉሥ የነበረ ምዕራብ ጎታዊ ሰው በአርዮስ ትምህርት አማካይነት ክርስቲያን ሆኗል። ይህም ለጳጳሱ መጽናናት ነበር፤ ይሁን እንጂ ሁለት መቶ ዓመታት እስኪያልፍ ድረስ ውጤቶቹ አልታዩም።

### ታላቁ ጳጳስ ግሪጎሪ - 590-604 ዓ.ም.

ግሪጎሪ በ540 ዓ.ም. ከሀብታም ቤተሰብ በሮም ተወለደ። ግሪጎሪ ታላቅ የአመራር ችሎታ የነበረውና የሮም ከተማ ከንቲባ የሆነ ሰው ነበር። ምሥራቃዊ ጣሊያን ሮምን ከሎምባርዳውያን ለመከላከል አልቻለችም ነበር። ግሪጎሪ በድንገት ብቅ ብሎ ሥልጣኑን ሲረከብ በተሳካ ሁኔታ ተቋቁሟቸዋል። በአስተዳደር፣ በወታደራዊና በህዝባዊ ጉዳዮች ውስጥ የነበረውን ችሎታ አስመስክሯል።

በ574 ዓ.ም. ግሪጎር የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰምቶ ሕይወቱን በሙሉ ፍቃደኝነት ለሃማኖታዊ ኑሮ ሰጥቷል። መሬቱን ሸጠ ለድሃ መርጃና በሲሲሊ ለስድስት ገዳማት ማሠሪያ እንዲውል ሰጥቷል። በኋላም የሮም ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ እንዲሆን ተመርጠ ጳጳስ ግሪጎሪ የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል።

በ579 ዓ.ም. ጳጳስ ዳግማዊ ፔላግዮስ ግሪጎሪን የውጭ ግኙኝነትን በሚመለከት ጠቃሚ ልምድ ወዳገኘበት ወደ ኮንስታንቲኖፕል አምባሳድር አድርጎ ላከው። በ586 ዓ.ም. በሮም የነበረበት ገዳም አለቃ ሆኗል። በ590 ዓ.ም. በጳጳስነት ተመርጧል። ግሪጎሪ በእግዚአብሔር ፊት ራሱን የጣለ፣ ሙሉ በሙሉ ራሱን የሰጠና ትሑት ሰው ነበር፤ ይሁን እንጂ በአንጻል ነገሮች ያምንና ለሥልጣን ይጠማ ነበር። በጣሊያን ታላቅ የአስተዳደር ሰው ሆኖ ነበር። በሮም አቅራቢያ፣ በሲሲሊ፣ በኮርሲካ፣

በካላብሪያ፣ በድልማጢያ፣ በጎል ወይም በፈረንሳይና በአፍሪካ የነበሩትን የቤተ ክህነት እርስቶች የመቆጣጠር አስደናቂ ችሎታ ነበረው። ይህም የጳጳሱን ሥልጣን ለማጽናት ረድቶታል።

ግሪጎር የሮም ጳጳስ ሥልጣን በሌሎች አገሮች እንዲሰፍን ሳያስልስ ጥረት አድርጓል። በአውሮፓ የሚገኙትን በርካታ የአሪሚ ጎሳዎች ማስተማር እንደሚያስፈልግ ተገንዝቧል። በገዳማት የተቀመጡት መነኮሳት ለአላማኒዎች ወንጌልን እንዲሰብኩ የመላክ ጥረት አድርጓል። ይህ የሮምና የኮንስታን ቲኖፕል ጳጳሳት ለመበላለጥ እርስ በእርስ የሚፎካከሩበት ዘመን ነበር።

ግሪጎር በአስቸጋሪ ዘመን የሮምን ቤተ ክርስቲያን አጠናክሯል። በተጨማሪ ከእርሱ በኋላ ስልጣን የሚጨብጡትን ተከታዮች የበላይነት እንዲያገኙ ጥርጊያ መንገዱን አዘጋጅቷል።

## ክርስትና በእንግሊዝ

በ596 ዓ.ም. ጳጳስ ግሪጎር አውግስቲን የተባለውን መነኩሴ ከሮም ወደ ኢንግላንድ ሄዶ እንግላዊያንንና ሳክሶናውያንን ክርስቲያን እንዲያደርግ ልኮታል። ሆኖም ከዚህ ዘመን ቀደም ሲል በሮማዊያን ዘመን በሦስተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ ወንጌል በእንግሊዝ አገር ተፋፍቶ ነበር። በምዕተ ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የነበረው ተርቱሊያንና ከአርባ አምስት ዓመታት በኋላ ደግሞ የነበረው ኦሪጂን በኢንግላንድ የነበረውን የወንጌል መስፋፋት ስምተው በጽሑፎቻቸው ውስጥ ጠቅሰውታል። በአንዳንድ ጉባኤዎች የኢንግላንድ ቤተ ክርስቲያን ልዑካን ተካፍለዋል። በ449 ዓ.ም. ከጀርመን የመጡ እንግላዊያንና ሳክሶናዊያን ወራሪዎች በምሥራቅ ኢንግላንድና በደቡብ ምሥራቅ እስኮትላንድ ክርስትናን አጥፍተዋል። ይሁን እንጂ በምዕራብ ኢንግላንድና አየርላንድ የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ክርቲያንነቷ እንደተጠበቀ ቀይቶ ከአየርላንድና ከእስኮትላንድ ጋር ኅብረት ፈጥራለች።

በ597 ዓ.ም. አውግስቲንና ተከታዮቹ ታኔት የተባለች ደሴት ደርሰው ኢብስፍሊት ላይ አረፉ። አየና በተባለው ሥፍራ ቅዱስ ኮሎምባ የሞተው በዚሁ ዓመት ነበር። ኮሎምባ በእስኮትላንድና በትውልድ አገሩ በአየርላንድ ወንጌላዊ ነበር።

ሚስቱ የፓሪስ ክርስቲያን ልዕልት የነበረችው የኬንት ንጉሥ ኤቴልበርት አውግሲቲንና ተከታዮቹን ከተቀበለ በኋላ አዲሱን እምነት እስኪያጠናው ጊዜ እንዲሰጡት ጠይቋቸዋል። በ9 ወር ጊዜ ውስጥ የኬንት ንጉሥና አሥር ሺህ ህዝብ አዲሱን ትምህርት ተቀብሎታል። አውግስቲንም ዋና ማዕከሉን ካንተርበሪ በሚገኘው በቅዱስ ማርቲን ቤተ ክርስቲያን መሥርቷል። በካንተርበር የሚገኘው ታላቁ ደብር ከኢንግላንድ የሃይማኖት አኗኗር ጋር በጣም የተሳሰረ ነው።

በ604 ዓ.ም. ሚሊተስ የተባለው ሰው የቅዱስ ጳውሎስን ቤተ ክርስቲያን ከቀረቀረ በኋላ የመጀመሪያው የለንደው ጳጳስ ሆኗል። በዚሁ ዘመን አካባቢ ጀስተስ የሮቸስተር ጳጳስ ሆኗል።

አውግስቲን የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ከሮም ጳጳስ ጋር እንድትተባበር ለማድረግ አልተሳካለትም። የሴልቲክ ተከታዮች ነጻነታቸውን ላለማስነካት ብርቱ አቋም ነበራቸው። በኋላ በመላ አገሪቱ ውስጥ ተቀባይነቱ እያደገ የሄደው የካንተርበሪ ደብር መሥራች በመሆኑ አውግስቲን ዝነኛው ሰው ነው፤ አውግስቲን በ604 ዓ.ም. ሞቷል።

ፓሊኑስ የተባለ አንድ ወንጌላዊ ከካንተርበሪ ወደ ሰሜን እአብሪያ ግዛት ሄዷል። በ625 ዓ.ም. ንጉሥ ኤድዊንና የቤተ መንግሥቱ አባላት ተለውጠዋል። ይሁን እንጂ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ኤድዊን በአሪሚ ንጉሥ በተገደለበትና ፓሊኑስ ሸሽቶ ባመለጠበት ወቅት በዚያ የነበረው አገልግሎት ጨርሶ ተደምስሷል።

ፓትሪክ አየርላንድ ከደረሰበት ከ432 ዓ.ም. ጀምሮ ወንጌል በአገሪቱ ውስጥ ሰፍኖ ነበር። የሮምን ሥልጣን ይቀበል እንደነበር የሚጠቁም ማስረጃ አይገኝም። በ397 ዓ.ም. ኒኒያን በእስኮትላንድ ውስጥ ዊትሆርን በተባለው ሥፍራ ቤተ ክርስቲያንና ገዳም አሠርቶ ለፒክታዊያን ወንጌል ሰብኳል፤ ከዚያም ብዙ ሌሎች ቅዱሳንና ሰባኪዎች ተከትለውታል፤ ከእነዚህም መካከል ዝነኛው በ563 ዓ.ም. ከአየርላንድ የመጣው ኮሎምባ ነበር፤ ኮሎምባ ታላቅ የአስተዳደር ሰው፣ ወንጌላዊና የደብር አለቃ ነበር። በታሪክም ውስጥ እጅግ በጣም የሚታወስ ሰው ነው።

በ635 ዓ.ም. የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ለሰሜን እምብሪያ ህዝብ ወንጌል ሊሰብክ ሞክሮ ነበር። ኤደንና ባልደረቦቹ በሰሜን እምብረ ምድር ጫፍ ላይ ወደምትገኘው ሊንድስፋርን የተባለች ትንሽ ደሴት ተጉዘዋል። በሠላሳ ዓመታት ውስጥ ሰሜንና ደቡብ እምብሪያን እስከ ቴምስ ወንዝ ድረስ በወንጌል አዳርሰዋል።

ኮሎምባነስ ከሰሜን አየርላንድ ባንጎር ከተባለው ሥፍራ ተነሥቶ ወደ ቡርጋንዲ ሄዷል። በዚያም በርካታ ዝነኛ ገዳማት መሥርቷል። ቀዳማዊ ግሪጎርን ያከብረው ነበር፤ ይሁን እንጂ በሃሳብ ሁሌ አይስማማም። ኮሎምባነስና ሌሎች የአየርላንድ መነኮሳት በጀርመን፣ በስዊዘርላንድ፣ በሐንጋሪና በጣሊያንም ጭምር አገልግለዋል። ስየአየርላንድ መነኮሳት ከሮም ከመጡት በብዙ ነጥቦች ልዩነት ነበራቸው። ለመላው አውሮፓ ወንጌልን ያዳርሳሉ የሚል ግምት ነበር። በ664 ዓ.ም. በሰሜን እምብሪያ ዊትቢ በተባለው ሥፍራ በተደረገው ስብሰባ የሮም ወንጌላዊያን ብልጫ ስላሳዩ የአየርላንድ መነኮሳት ሥፍራውን ለቀው ወደ ሰሜን ተጉዘዋል።

በ636 ዓ.ም. ደቡብ አየርላንድ ከሮም ጳጳስ ጋር ኅብረት የፈጠረች ሲሆን ሰሜን አየርላንድም በ697 ዓ.ም. እጅ ስጥታለች። ከዚህ ወቅት ወዲህ የሴልቲክ እምነት በመላ እንግሊዝ ውስጥ የነበረው ተቀባይነት ቀስ በቀስ ሊቀንስ ችሏል።

## <u>የቤተ ክርስቲያን ገፅታ መቀየር</u>

የታላቁ ጳጳስ የግሪጎር የአመራር ዘመን የሮምን ቤተ ክርስቲያን አጠናክሯታል። የተፈጠረው ሁኔታ ከመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ቤተ ክርስቲያን ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ይህ ነው ሊባል እስከማይችል ከፍተኛ ነው።

ለምሳሌ -

1. የሮም ጳጳስ ሥልጣን

   ጳጳስ ልክ እንደ መጀመሪያው ምዕተ ዓመት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ራሱን ዝቅ ያደረገ መጋቢ በመሆን ፋንታ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉና የጳጳሳት ሁሉ የበላይ መሆን ይገባኛል ይል ነበር። ውሎውም ከነገሥታትና ከአስተዳደር ሰዎች ጋር ነበር።

2. የጌታ እራት

   የጌታ እራት የክርስቶስ ሞት መታሰቢያ ተደርጎ ቢቆጠርም እንኳ እንደ መስዋዕት መቆጠር ተጀምሮ ነበር። ሕብስቱና ወይኑ በካህን በሚቀደስበት ወቅት ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣል ብሎ የሚሟገተው ጽሑፍ እስከ 831 ዓ.ም. ድረስ በጽሑፍ አልሰፈረም ነበር። ይህም ጽሑፍ በ1215 ዓ.ም. በይፋ የሮም ቤተ ክርስቲያን ትምህርተ ክርስትና ተደርጓል።

3. ፑርጋቶሪ

ሙታን በእሳት ይነፃሉ የሚለው ትምህርት አውግስቲን ሙታን በእሳት ከኃጢአት ሊነፁ ይችላሉ የሚለውን ሃሳብ ካቀረበበት ወቅት አንስቶ ይህ ትምህርት እያደገ መጥቷል። በአራሚ ሃይማኖቶች ውስጥ ይህንን የመሰለው እምነት የተለመደ ነበር። ቀዳማዊ ግሪጎር ይህንን ትምህርት ይደግፈውና በሰፊውም ተቀባይነት አግኝቶ ነበር። ይሁን እንጂ በ1439 ዓ.ም. በፍሎሬንሱ ጉባዔ የሮም የቤተ ክርስቲያን የእምነት አንቀጽ እንዲሆን ከመደረጉ በፊት ተቀባይነት አላገኘም ነበር።

4. ለሞተ ሰው መጸለይና ለቅዱሳን የሚደረጉ ፀሎቶቹ የፑርጋቶሪ ትምህርት ተቀባይነት በጨመረ መጠን በራስ ፈቃድ እንደፈለጉት መኖርና ለሞተ ሰው የፍታት ፀሎት ማድረግ የተለመደ ነገር ሆኗል፤ ለቅዱሳንና ለሰማዕታት ከፍተኛ ክብር መስጠት የተጀመረ ሲሆን በእነርሱ ስም መጸለይ አስፈላጊ ነው ተብሎ ታምኖበት ነበር። ከዚህ በኋላ ለቅዱሳን ፀሎት ማድረግ የተለመደ ሆኖ ነበር። በ787 ዓ.ም. በሁለተኛው የኒቂያ ጉባዔ ይህንን የመሳሰሉ ፀሎቶች በይፋ ተቀባይነት አግኝተዋል።

5. የማርያም መወደስ

በ431 ዓ.ም. የኤፌሶኑ ጉባዔ ማርያም "የእግዚአብሔር እናት" መሆኗን አውጇል። ይህንን አስተሳሰብ ብዙዎቹ የተቃወሙት ቢሆንም መስፋፋትን ቀጥሏል። ለማርያም ክብር በዓላት ይከበሩና አምልኮም ይደረግላት ነበር። በ6ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ በስምዋ ጸሎቶች ይጸለዩ ነበር። ለሰዎች አድርጋለች ስለሚባለው አማላጅነት የሚገልፁ ብዙ ትምህርቶች ነበሩ።

6. የኃጢአት ኑዛዜ

ንስሐ የገባው ሰው ከቤተ ክርስቲያን ሕብረት ጋር ለመቀላቀል ኃጢአቱን መናዘዝ ከመጀመሪያው ጀምሮ አስፈላጊ ነበር። ቀደም ሲል ይህ ይደረግ የነበረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በህዝብ ፊት ነበር። ከ440-461 ዓ.ም. ከነበረው ከቀዳማዊ ሌዮ ዘመን ወዲህ ኑዛዜ በካህን ፊት የሚደረግ የግል ኑዛዜ ሆኗል። በዚህ ዘመን ለካህን መናዘዝ የተፈቀደ ቢሆንም ግዴታ የለበትም ነበር። በ763 ዓ.ም. ክርስቲያኖች ለካህን እንዲናዘዙ ትዕዛዝ ተሰጥቷል። እልፎ እልፎ በምዕመናን ፊት የሚደረግ ኑዛዜ ስም አጥፊ ሆኗል። በአውሮፖ የነበሩት የሴልቲክ ሰባኪዎች የሰዎች ሥነ-ምግባራዊ ህይወት ዝቅተኛ ሆኖ ስላገኙት ሊያምኑ የሚፈልጉ ሰዎች በግል መጥተው እንዲናዘዙና ትምህርት እንዲማሩ አደፋፍረዋል።

7. የአምልኮ ሥፍራዎች

ክርስቲያኖች ከበርቴ እየሆኑ በመጡ ቁጥርና በነገሥታትና በመኳንንት ፊት ተቀባይነት ሲያገኙ በጣም ብዙ ዋጋ የሚፈጁ ሕንጻዎችን ማሠራት ጀመሩ። በኮንስታንቲኖፐል የምትገኘው የቅድስት ሶፊያ ቤተ ክርስቲያንን በቀዳማዊ ግሪጎሪ ዘመን የነበሩት ሰባቱ የሮም አብያተ ክርስቲያናት በውድ ዋጋ ለተሠሩ የአብያተ ክርስቲያናት ሕንጻዎች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። ይህንን በሚመለከት 200 ዓመታት ቀደም ብሎ ጀሮምና ክሪሶስቶም ማስጠንቀቂያ ሰጥተው ነበር። "እውነተኛና ቅዱስ ሕይወት ብቻ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነው" ሲሉ ተናግረዋል። በ814 ዓ.ም. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምስሎች ይመለካሉ የሚል ሐሜት ይሰማ ነበር። ንጉሥ ሚሻል ለቻርለማኝ ልጅ ለፒዮሱ ሊዊስ ይህንን ጉዳይ የሚመለከት ጥያቄ ያዘለ ደብዳቤ ጽፎለታል። ከዚህ ቀደም ሲል ክርስቲያኖች በምስሎች ስለሚያመልኩ ጣኦት አምላኪ ናቸው በማለት እስላሞች ሊዘባበቱባቸው ጀምረው ነበር።

8. ካህናት

የካህናት ሥራ እያደገ በመጣ መጠን ቀድሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥፍራ ያልነበረው መሰዊያ ተፈላጊነቱ በጣም እየጨምረ ሄዷል። ይህም የቤተ ክርስቲያንን ሕንጻ ቅርጽ ለውጦታል። የአማኞች ሁሉ ካህንነት እስከናካቴው እንዲረሳ አድርጓል። ካህናት ልዩ ፀጋና መለኮታዊ ሥልጣን ያላቸው የበላይ ሹማምንት ተደርገው መቆጠር ጀምረዋል። ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርቡት በካህን አማካይነት ብቻ ነው የሚለው ትምህርት ተሰራጭቷል። የካህኑም ተግባር ልክ እንደ አራሚ ካህናት ሥራ አስማት ተደርጎ ተቆጥሯል። ካህኑ የክህነት ተግባር የሚያከናውንበት ሥፍራ በሕንጻው ውስጥ ከሚገኙት ሥፍራዎች ሁሉ እጅግ የተቀደሰ ተደርጎ ይታሰብና ለብቻው የተከለለ ነበር። ከዚህም የተነሣ ከህዝቡ መካከል የካህናትን ወገን መለየት ተጀምሯል።

9. አልባሳት - የካህናት ልብሶች

ኮንስታንቲን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲገቡ ያደረጋቸው የካህናት ልብሶች በክህነት አገልግሎት ውስጥ አስፈላጊ የሚሆኑበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ታሪክ ጸሐፊው ሶቅራጥስ በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ ካህናት የሚለብሱት ልብስ ቀለም ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ይወያዩ ነበር ሲል ጽፏል። ቅዳሴ መደረግ በተጀመረበት ወቅት ለከፍተኛ ቅዳሴ የሚያገለግሉ ልዩ ልብሶችና መለሰተኛ ቅዳሴ ሲከናወን የሚለበሱ ሌሎች ልብሶችን በማስከተል ልምዱ አድጓል።

10. ዕጣን

ዕጣን ለመጀመሪያ ጊዜ በአገልግሎት ላይ የዋለው የቤተ ክርስቲያንን ሕንጻዎች ለማጠን ብቻ ነበር። ለአራት ዓመታት ያህል ዕጣን ከአምልኮ ጋር ምንም ዝምድና አልነበረውም። ከ378-395 ዓ.ም. የሮማዊያን ንጉሥ የነበረው ቀዳማዊ ቴኦዶሲዮስ ዕጣን የሚታጠኑ የክርስቲያን ቤቶች እንዲወረሱ አዟል።

በ325 ዓ.ም. ተርቱሊያንና ላክታንቲዮስ ዕጣን ማጨስ "አራሚ" መሆን እንደሆነና የክርስቲያኖች ልምድ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

## <u>ማጠቃለያ</u>

በመካከለኛው ዘመን መጀመሪያ ላይ ቤተ ክርስቲያን ከአንደኛው ምዕተ ዓመት በጣም ትለይ ነበር። በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን መጠኗ ያነሰና ደካማ ስትሆን ጳውሎስና ሌሎችም ወንጌል የሰበኩላቸው ሰዎች የሰለጠኑ ነበሩ። ይኖሩ የነበረውም በመላ ግዛታቸው ውስጥ አውራ ጎዳናዎችን ባሠሩትና ሰላምና ሥርዓት ባስጠበቁት በሮማውያን ግዛት ነበር።

በመካከለኛው ዘመን መጀመሪያ ላይ ቤተ ክርስቲያን መጠኗ የሰፋና በብርቱ የተደራጀች ስትሆን ከብዙ አቅጣጫዎች በክፉ ሁኔታ ብልሹ ነበረች። የሮማዊያን መንግሥት ተገንነት አጥታለች። በሮማውያን መንግሥት ፋንታ በርካታ ያልሰለጠኑ ሽፍቶች ግዛቶች ተመስርተዋል። ከቀድሞው ግዛት ውጪ የነበሩት ጎሳዎች አላማኒ፣ ያልተማሩና ያልተሻሻሉ ይሁኑ እንጂ ድንቁርና አለነበረባቸውም። አገሮቻቸውም መንገዶች ያልነበራቸው፣ ያልሰለጠኑና ኋላቀር ነበሩ። እነዚህ ሽፍታ ጎሳዎች ብዙ የተማሩ ሰዎችን በመግደል በርካታ መጻሕፍትን ድራሻቸውን አጥፍተዋል። ቤተ ክርስቲያን አህዛብን ክርስቲያን የማድረግና የማስተማር ድርብ ተግባር ነበራት።

በሽፍቶች ወራሪዎች ዘመን መነኮሳት በርካታ መጻሕፍትን የመጻፍና የማዳን ጠቃሚ የሆነ የሥራ ድርሻ ነበራቸው።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የሮማዊያን ግዛት የወደቀው መቼ ነበር?
2. ክርስትናን በመጀመሪያ የተቀበሉት የጀርመን ጎሳዎች የትኞቹ ነበሩ?
3. ሪካርድ ማን ነው?
4. ግሪጎር ሮምን ያዳናት ከማን ነው?
5. ግሪጎር የእግዚአብሔርን ጥሪ ሲሰማ ምን አደረገ?
6. የጳጳሰን ሥልጣን ለማጽናት የረዳው የግሪጎር ችሎታ ምንድነው?
7. ቀዳማዊ ሌዮና ቀዳማዊ ግሪጎር ያስፋፉት ጳጳሳትን የሚመለከት ትምህርት የትኛው ነበር?
8. የሮም ጳጳስ የጳጳሳት ቁንጮ እንዲሆን የቀረበውን ሃሳብ የተቃወማቸው ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?
9. ግሪጎር ለሮም ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ያደረጋቸው አስተዋፅዖዎች ምን ምንድን ናቸው?
10. አውግስቲን የመሰረተው ዝነኛ ደብር ማን ይባላል?
11. የለንደን የመጀመሪያ ጳጳስ ማን ነበር? መቼ ተሾመ?
12. ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋር አልቀላቀልም ያለችው የኢንግላንድ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?
13. ወንጌልን ወደ አየርላንድ የወሰደው ማን ነው? መቼ?
14. የአየርላንድ መነኮሳት ለወንጌል አገልግሎት ወዴት ሄዱ?
15. የአየርላንድ መነኮሳት በአገልግሎታቸው ወደ ደቡብ አውሮፓ ሊገፉ ያልቻሉት ለምንድነው?
16. የኢንግላንድ ሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን እንድትማረክ ያደረጋት ምንድን ነው?
17. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ወይም መሪ ተግባር በ6ኛው ምዕተ ዓመት እንዴት ተለወጠ?
18. የጌታ እራት በመታሰቢያነት ፋንታ ምን ሆነ?
19. የሙታን በእሳት የመንፃት ሃሳብ የመነጨው ከየት ነው?
20. በካህን ፊት መናዘዝ የተጀመረው እንዴት ነው?
21. የተጌጡ አብያተ ክርስቲያናትንና ምስሎቻቸውን በሚመለከት እስላሞች ክርስቲያኖችን የተነኮሷቸው እንዴት ነበር?
22. ካህናት ከተራው ህዝብ ተለይተው ከፍተኛ ወገን ሊሆኑ የቻሉት እንዴት ነው?
23. ካህናት ልዩ ልብሶችን መልበስ አለባቸው የሚለው ሃሳብ መቼ ተጀመረ?
24. ዕጣን በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በአገልግሎት ላይ እንዴት ሊውል ቻለ?

## ምዕራፍ ስድስት - የገዳም ሥርዓት

በገዳማት ውስጥ መኖር ሰውነትን ክፉኛ መጣልና እንዲያውም ጨርሶ መርሳት በጳውሎስ ዘመን ተስፋፍቶ ነበር። ጳውሎስ በቆላ 2፡23 ውስጥ ይህንን ነገር አውግዟል። ይህ ልማድ ክርስትና ከመጀመሩ በፊትም በምሥራቅ ነበር። የቡድሃ እምነት ተከታዮች ይለማመዱት ነበር።

በ251 ዓ.ም. በግብፅ ውስጥ ይህንን መለማመድ ከጀመሩት የመጀመሪያ ክርስቲያኖች መካከል ቅዱስ አንቶኒ ይገኝበታል። ቅዱስ አንቶኒ ሃብቱንና በህዝብ ላይ የነበረውን ሥልጣን ትቶ በተራሮች ሥር በሚገኙ ዋሻዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ቃል በጥሞና እያሰላሰለ ሊኖር ሄደ። ከዚያ ጥቂት ደቀመዝሙራት ሰብስቦ በበርሃ ውስጥ አንድ ማህበረሰብ መሥርቷል።

ከ296-346 ዓ.ም. የኖረው ፐኮሚዮስ ገዳማትን ወይም ማህበረሰቦችን ማደራጀት ጀምሯል። በላይኛው ግብፅ ውስጥ በአባይ ወንዝ ውስጥ በምትገኘው ደሴት ላይ አንድ ገዳም መሥርቷል። አትናቴዎስ ይህንን ማህበረሰብ በጎበኘበት ወቅት መዝሙሮችንና ጸሎቶችን ከሚያቀርቡ 3000 መነኮሳት ጋር ተገናኝቷል። ወዲያው ይህንን የመሳሰሉ ገዳማት በግብፅ ተቋቁመዋል፤ እንቅስቃሴውም ወደ ተለያዩ አገሮች ተሰራጭቷል።

አትናቴዎስ፣ ጀሮም፣ አምብሮስና አውግስቲን የደገፉት ቢሆንም እንኳ ይህ እንቅስቃሴ ከምስራቅ ይልቅ በምዕራብ ዕድገቱ በጣም ዝግ ያለ ነበር። በ4ኛው ምዕተ ዓመት ጎል በተባለው አገር ከነበሩት የምዕራብ መሪዎች መካከል አንዱ የቱርሱ ቅዱስ ማርቲን ነበር። በ397 ዓ.ም. ቅዱስ ኒኒያን የቅዱስ ማርቲንን ሥራ መመሪያው አድርጎ በመንግት በእስኮትላንድ ውስጥ ዊትሆርን በተባለው ሥፍራ ቤተ ክርስቲያኑንና ገዳሙን አቋቋሟል። ይህም በእስኮትላንድና በአየርላንድ የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል።

## የገዳም እንቅስቃሴዎች

1. የቤነዲክትዊያን ሥርዓት
   ይህ ሥርዓት የተመሰረተው በ529 ዓ.ም. በጣሊያኑ የኑርሲያ ነዋሪ በቤነዲክት አማካይነት ነበር። ትምህርቱ በጣም ጥብቅ ነበር። ሥርዓቱም በጣም ተወዳጅና የበለፀገ ሆኗል። ይሁን እንጂ ከብልፅግና ከድል ጋር የሥነ-ምግባር ውድቀትና ብልሹነት አብረው መጥተዋል።

2. የክሊኒ እንቅስቃሴ
   በ910 ዓ.ም. በፈረንሳይ ውስጥ ክሊኒ በተባለው ሥፍራ ባርኖን የሚባል ሰው ይህንን እንቅስቃሴ ጀምሯል። በቤኒደክታውያን ሥርዓት ውስጥ የሥነ-ምግባር ውድቀት መኖሩንና የጋለ ፍላጎት እንደሚጎድል ስለተመለከተ የመቃረን ሙከራ አድርጓል። ይህ እንቅስቃሴ ቤተ ክርስቲያን ከልዑላንና ከበላይ ጠባቂዎች ጣልቃ ገብነት ነፃ መሆን እንዳለበት አውጇል። ጳጳሳትንና የደብር አለቆችን በመነኮሳት አማካይነት የመምረጥ ነጻ ምርጫ ያካሂድ ነበር። የካህናትን ጀንደረባነት በሚመለከት መንቻካ ሃሳብ ነበረው።

3. ሲስቴርሳዊያን
   ይህ እንቅስቃሴ ጥብቅ የሆነውን የቤነዲክታውያንን መመሪያዎች መጠበቅ ይፈልጉ በነበሩ መነኮሳት አማካይነት በቡርጋንዲ ተመሠረተ። ዓላማቸው ቀለል ያለ ኑሮ መኖር እንደሆነ ግልጽ ነበር። 1115 ዓ.ም. በርናርድ የተባለው ሰው ክልርቮ በተባለው ሥፍራ ራቅ ባለ ሸለቆ ውስጥ በጣም ዝናኛ ገዳም መሥርቷል። በርናርድ እንደበተ ቀናና ተሰሚነት የነበረው ሲሆን በጣም ትዕግሥት የሚጎድለው ሰው ነበር። የሲስቴራውያን ሥርዓት ሰባት መቶ ገዳማት እንዲኖሩት አድርጓል። በርናርድ ብዙ መዝሙሮች ጽፏል።

4. የሜዲካንት ሥርዓቶች
   ፍራንሲስካዊያንና ዶሚኒካዊያን የእነዚህ ሥርዓቶች አባላት ትሁትና የማንንም መብት የማይገፉ ነበሩ። ይህም ሰዎችን ስለማረከ ሥርዓቶች ወዲያውኑ ከባድ ቅንዓት ያስነሣውን የሥርዓቶች ሥርዓት የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል። አንዱ ሥርዓት የተመሠረተው በጣሊያን ውስጥ በምትገኘው በአሲሲው ቅዱስ ፍራንሲስ ነበር። የዚህ ሥርዓት ተከታዮች ዓላማ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመምሰል የድህነት ኑሮ መኖር ነበር። በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ እጅግ ተቀባይነት ያገኘ ሥልጣን ነበራቸው። ቦናቬንቱራ፣ ዱንስ እስኮቱስና የኦካሙን ዊሊያም የመሳሰሉ ታላላቅ ሰዎች የዚህ ሥርዓት አባላት ሆነዋል። ከጊዜ በኋላ በሀብትና በዓለማዊነት ኑሮ ሳቢያ ከእነርሱ በፊት እንደነበሩት ሰዎች አሽቀልቁለዋል።

   በሮም ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ቅዋሜ በተነሳበት በ1215 ዓ.ም. ዶሚኒክ በተባለ የእስፔን ልዑል አማካይነት ሌላ ሥርዓት ተመሥርቶ ነበር። ዶሚንክ ተራውን ህዝብ ለመሳብ ያልተንዛዛ ቀላል ኑሮ በመኖር ላይ ያተኩር ነበር። ዶሚኒክ ከሙሉ ልብ የተለወጠና ነፍሳትን ለማዳን ራሱን የሰጠ ብርቱ መሪ ነበር። ሦስት ጊዜ የጵጵስና ማዕረግ ሲሰጠው አልቀበልም ብሏል።

ዶሚንክ ከፋርስ የመጣውን የአልቢጀናውያን እምነት የተባለውን የሐሰት ትምህርት በመቃወም በተቃጠለ ፍላጎት ሠርቷል። ይህ የሐሰት ትምህርት የምድር ኑሮ መንፈስና ቁስ አካል በሆኑት በብርሃንና በጨለማ አምላኮች መካከል የሚደረግ ትግል ነው የሚል ነበር። የዚህ እምነት ተከታች ሰብአዊ አገዛዝ መጥፎ ነው ሲሉ አስተምረዋል። ይህንን ጉዳይ የሚመረምረው ዓላማው የሐሰት ትምህርቶችን ሁሉ መንግሎ መጣል የነበረው የሮማዊያን ቤተ ክርስቲያን ፍርድ ቤት ነበር። በዚህ ነገር የተጠረጠሩ ሁሉ የዶሚኒቻውያን ሥርዓት አባላት በሆኑት መርማሪዎች ፊት ቀርበው ይመረመሩ ነበር። ተከሳሽ ሆኖ የቀረበው ሰው ጥፋቱን አምኖ ከተፀፀተ በነፃ ይለቀቅ ነበር፤ አምኖ ካልተፀፀተ ግን እንዲቀጣ ለሕዝባዊ ፍርድ ቤት አልፎ ይሰጥ ነበር፤ ቅጣቱም ዘወትር ሞት ሲሆን ይኸውም ከግንድ ጋር ታስሮ መቃጠል ነበር።

5. ወታደራዊ ሥርዓቶች

እነዚህ ሥርዓቶች በሙሉ ወታደር የነበሩ መነኮሳትን ያቀፉ ነበሩ።

ሀ. በ1048 ዓ.ም. በኢየሩሳሌሙ ቅዱስ ዮሐንስ አማካይነት ባለ ማዕረግ የነበሩ የመነኮሳት ሥርዓት ተመሰረተ።

ለ. በ1119 ዓ.ም. የመቅደስ ጠባቂ የነበሩ ባለ ማዕረግ የመነኮሳት ሥርዓት በፈረንሳይ ተጀመረ።

ሐ. በ1121 ዓ.ም. የጀርመን ቱቶናውያን ባለ ማዕረግ የመነኮሳት ሥርዓት ተቋቋመ።

የእነዚህ ሥርዓቶች አመሠራረት ዓላማ መናኞችን መደገፍና መንከባከብ ነበር። ይሁን እንጂ ወዲያውኑ ጠብ ፈላጊዎች ሆነው አቢይ ዓላማቸው እስላሞችን መውጋት ሆኗል። ተከታዮቻቸውም በጣም ከመበልፀጋቸውም በላይ ሥርዓታቸው ወደ ሌሎች አገሮች ተስፋፍቷል።

## ማጠቃለያ

በመጀመሪያ ላይ የተለያዩ ሥርዓቶች የነበራቸው ገዳማት መልካም ሥራ ሠርተዋል። ትምህርት ቤቶችን ከፍተዋል፤ እርሻን አስፋፍተዋል፤ ድሃን ደግፈዋል፤ እንዲሁም ለበሽተኞች ለተጣሉ እንክብካቤ አድርገዋል። ሆኖም መሥራቹ ሲሞት ያለማቋረጥ በማሽቆልቆል ከጊዜ በኋላ ከመሰረታዊ መመሪያዎቻቸው ርቀዋል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ሐዋሪያው ጳውሎስ ሰውነትን ጨርሶ መጣልንና መርሳትን በሚመለከት ምን ተናገረ?
2. በግብፅ ውስጥ በገዳማት መኖርን ከተለማመዱት የመጀመሪያ ክርስቲያኖች አንዱ ማን ነበር?
3. ፓኮሚዮስ ገዳም ያቋቋመው የት ነበር?
4. የገዳሞችን መቋቋም ይደግፉ የነበሩት አራት የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስም ጥቀሱ።
5. በእስኮትላንድ ገዳም የመሠረተው ማን ነበር? መቼ?
6. የቤኒዲክታዊያን ሥርዓት የተቋቋመው የት ነው? በየትኛው ዘመን?
7. የክሉኒ ሥርዓት የተቋቋመው መቼና የት ነበር? መሥራቹስ ማን ይባላል?

8. በርናር አዲሱ ሥርዓት እንዲያቋቁም ያነሣሣው ነገር ምንድን ነው?
9. የሲስቴርሳውያኑ ሥርዓት በቡርጋንዲ እንዲመሠረት ያነሣሣው ነገር ምንድንነው?
10. የሲስቴርሳውያኑ ሥርዓት በርናርድ በተለይ የሚታወሰው በምንድን ነው?
11. በፍራንሲስና በድሞኒክ የተመሠረቱት ሥርዓቶች በቀድሞዎቹ ሥርዓቶች ላይ የበላይነት ያገኙት ለምን ነበር?
12. ዶሚኒክ ማን ነው? ያስተማረውስ የትኛውን የሐሰት ትምህርት በመቃወም ነበር?
13. የወታደራዊ ሥርዓቶች ዓላማ ምን ነበር?
14. ከጊዜ በኋላ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ሁሉ ምን ሆኑ?
15. ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ያደረጉት መልካም ሥራ ምንድነው?

## <u>ምዕራፍ ሰባት - 590-604 ከቀዳማዊ ግሪጎር</u>
## <u>እስከ. 742 -814 - ቻርለማኝ</u>

ቀደም ሲል እንደተረዳነው ታላቁ ግሪጎሪ የሮም ጳጳስ ሲሆን ጠበቃና የሮም ከተማ ከንቲባ ሆኖ ለህዝብ ይሰጠው የነበረውን አገልግሎት ተወ። የጥንቱን ዓለም ጥበብ ወደ መካከለኛው ዘመን ለማስተላለፍ በነበረው ችሎታ የማይረሳ ሰው ነው። በጣም ጠለቅ ያሉ ሃሳቦችን የያዙ መጻሕፍትንም ጽፏል።

ታላቁ ቻርልስ ተብሎ ይጠራ የነበረው ቻርለማኝ የፍራንካውያን ንጉሥ ነበር። በኋላ በ800 ዓ.ም. በጳጳሱ አማካይነት ንጉሠ ነገሥት ተብሎ ዘውድ ጭኗል።

ፍትህ መጓደል በሰፈነበት ዘመን ቻርለማኝ ለሦስት ነገሮች ቆሟል-

1. ለሕግና ለሥርዓት - ይኸውም ለህዝብና ለንብረት ሰላምና ጥበቃ፣
2. ለሥልጣኔ ወይም ለባሕል - ይኸውም መሻሻልና ጥራት ለሚያስገኝ ዕውቀት
3. ለክርስትና - ይኸውም አዳኝና ጌታ አድርጎ በክርስቶስ ማመንን ማለት ነው። ሆኖም ቻርለማኝ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተጠቀመባቸውን ዘዴዎች ሙሉ በሙሉ መቀበል ያዳግታል።

ቻርለማኝ ካህናት ከፍተኛ ትምህርት የተማሩ ሊሆኑ እንደሚገባ ስለተሰማው ትምህርት ቤቶችን ከፍቷል። ሮምን በቁጥጥራቸው ሥር ያደረጓት አብዛኞቹ ወራሪዎች ትምህርትንና ባህል የሴታሴትነት ተግባር ይመስላቸው ነበር።

ቻርለማኝ ዘዴ የተሞላባችው ሕጋጋት አውጥቶ አሳገድዷቸዋል። ይህም ለግዛቱ ፀጥታና ሥርዓት አስገኝቷል። ቻርለማኝ ይበልጡን ዘመኑን ያሰለፈው በውጊያ ነበር።

የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ለቻርለማኝ ልዩነት አልነበራቸውም። ድሎችንም የተጎናጸፈው በመግደል፣ ክርስትናን እንዲቀበሉ በማስገደድና ብዙ ሕዝብ ወደ ተለያዩ ሥፍራዎች በመውሰድ ነበር።

በ814 ዓ.ም. ቻርለማኝ ሲሞት በዓለም ላይ ሦስት ታላላቅ ግዛቶች ነበሩ። ጥንታዊውና ከሁሉም ደካማ የነበርው ባልኸንን፣ እስያንና ደቡብ ጣሊያንን የሚያጠቃልለው የቢዘንታይን ወይም ምሥራቃዊው ግዛት ነበር። አዲሱና ከሁሉም የሚበረታው ሰሜናዊ ጣሊያንን፣ ከፊል እስፔይንን፣ ፈረንሳይን፣ ቤልጂየምን፣ ኔዘርላንድን፣ ከፊል ጀርመንና አውስትሪያን የሚያጠቃልለው የፍራንካውያኑ የቻርለማኝ ግዛት ነበር። ከሁሉም ይሰፋ የነበረው ከህንድ ጀምሮ ፋርስን፣ ሶርያን እስራኤልን፣ ሰሜን አፍሪካን እና ደቡብ አውሮፓን ያቀፈው <u>የመሐመድ ተከታይ የሆኑት የአረቦች ግዛት</u> ነበር።

## የእስልምና አጀማመር

የእስልምና መነሣት ክርስትናን ክፉኛ ተፎካክሮታል። በ570 ዓ.ም. በአረቢያ ውስጥ መካ በተባለው ሥፍራ መሐመድ ተወለደ። ገና በጨቅላነት ዘመኑ ወላጆቹ ሞቱበት። በብቸኝነትም ለብዙ ዘመን በበረሃ ኖረ። ሙሉ ሰው በሆነበት ወቅት ነፍሱን ሰቶ ድምፆችን እንደሚሰማ ይናገር ነበር። ከአይሁድና ከመናፍቃን ክርስቲያኖች ጋር ተገናኝቷል። አንድ እግዚአብሔር መኖሩን ከእነርሱ ተምሮ ነበር፤ ይሁን እንጂ ይኖሩት የነበረውን ሕይወት አልወደደውም። ክርስቲያን እንዳይሆን ያገደውም ይህ ሳይሆን አይቀርም። ብዙት የነበራቸውን የአረቢያ አምላኮችንም አልወደዳቸውም። ስለዚህ አንድ እውነተኛ የአላህ ሃይማኖት አለ፤ ይህንን ማሰፋፋት የሚገባኝ የአላህ ነቢይ እኔ ነኝ በማለት ስብከት ጀምሯል።

አርባ ዓመት ሲሞላው መሐመድ ቁርዓንን መጻፍ ጀምረ። ይህም የእስላሞች ቅዱስ መጽሐፍ ሆኗል። ከመልአኩ ገብርኤል የተሰጡኝ መለኮታዊ መገለጦች ናቸው የሚላቸውንም ጽፏቸዋል።

መሐመድ ተግባቢና ለጋስ ሰው ሲሆን በጠላቶቹ ላይ ደግሞ ሊጨክን የሚችል ነበር።

በስብከቱ ላይ የተነሣው ቅዋሜ በ622 ዓ.ም. መሐመድና ሁሉት መቶ የሚያህሉ ተከታዮች ከመካ ወደ መዲና እንዲሰደዱ አድርጓቸዋል። ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ በድል አድራጊነት እንደገና ወደ መካ ተመልሷል። በ632 ዓ.ም. ሲሞት መላውን አረቢያ በቁጥጥሩ ስር አድርጎ ነበር። ልክ ከመካ ከተሰደደ ከ90 ዓመታት በኋላ የመሠረተው የእስልምና ሃይማኖት ከህንድ እስከ አትላንቲክ ውቅያኖስ ድረስ ተሰራጭቷል። ከዚያም ወደ መካከለኛው እሲያ፤ ቻይናና ወደ ደቡብ እሲያ ተዳርሷል።

የእስላም ውጊያዎች ወይም ጦርነቶች ወንጌልን በመጀመሪያ ሰምተው ከነበሩት አገሮች ከሞላ ጎደል ጨርሶ ቤተ ክርስቲያንን አጥፍተዋል። እልፎ እልፎ ጥቂት ክርስቲያን ህብረተሰቦች ብቻ ተርፈዋል። ሆኖም ድል አድራጊዎቹ የእስላም ሠራዊት ከእስፔይን ወደ ፈረንሳይ ሲሻገሩ በመጡበት እንዲመለሱ ተደርጓል። የፍራንካዊያን ንጉሥ የቤተ መንግሥት ከንቲባ የነበረው ቻርለስ ማርቴል ክርስቲያን ኃይላትን በማሰባሰብ መርቷል። በፈረንሳይ ውስጥ በምትገኘው ቱርስ በተባለችው ሥፍራ የእስላም ሠራዊትን ድል አድርገው ወደ መጡበት መልሰዋቸዋል።

## የጀርመን ጎሳዎች ክርስትናን መቀበል

እስልምና ብዙዎቹን ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናት በዘጋበት ወቅት ወንጌል ለጀርመን ጎሳዎች በመዳረስ ላይ ነበር። ኮሎምባነስና የእንግሊዝ ሴልትክ ቤተ ክርስትያን ወንጌላውያን አውሮፓን በወንጌል የማዳረስ ሙከራ ሊያደርጉ ተሰማርተው ነበር። በጣም የሰመረ አገልግሎት ያከናወኑት ሁለቱ እንግሊዛዊያን ዊሊብሮረድና ቦኒፌስ ወይም ዊንፍሪዝ ነበሩ።

በ690 ዓ.ም. የእንግሊዝ መነኩሴ የነበረው ዊሊብሮርድ በጀርመን ጎሳዎች መካከል የሮምን ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ሲጣጣር ብዙ ቅዋሜ ደርሶበታል። ይሁን እንጂ ከሞላ ጎደል የፍሬሺያ አካባቢ ባጠቃላይ ክርስትናን ተቀብሎ ነበር።

ቦኒፌስ የተባለው ሌላ እንግሊዛዊ መነኩሴ "የጀርመን ሐዋሪያ" በሚል መጠሪያ ይታወቅ ነበር። ባቫሪያ በተባለው ሥፍራ ለሮም ቤተ ክርስቲያን ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንና ገዳማትን አቋቁሟል። በ732 ዓ.ም. በኤጲስ ቆጶስ ሆኗል። ቦኒፌስ ፀጥ ለጥ ብሎ ለጳጳስ ይገዛ ነበር። ቦኒፌስ የወጣው ከሴልቲክ ቤተ

ክርስቲያን ውስጥ በመሆኑ የሴልቲክን አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት በሮም ቤተ ክርስቲያን ሥር እንዲተዳደሩ አድርጓል።

ቻርለማኝ ሳክሶናውያን ክርስትናን እንዲቀበሉ አስገድዷቸዋል። ክርስትና በጠላቶቻቸው በፍራንካውያን በኩል ወደ እነርሱ በማምጣቱ ሳክሶናዊያን አልወደዱትም። በቅጣት መልክ ቻርለማኝ 4500 ሳክሶናውያን በአንድ ቀን ውስጥ እንዲሰየፉ አድርጓል። ከሠላሳ ዓመታት ውጊያ በኋላ በመጨረሻ ሰላም ተመሥርቷል። ከዚያም ቀየት ብሎ ቻርለማኝ “ሳክሶናውያንን በንግግርና በሰይፍ ሊለውጥ” ከተጠቀመባቸው መንገዶች ይልቅ ወንጌላዊያን ወንጌልን ለማሰራጨት የሚረዳቸው የተሻለ ዘዴ ባገኙበት ጊዜ ብዙዎችም ክርስቶስን ወደ ማወቅ ደርሰዋል።

## ፍራንካውያን መሪዎችና ቅዱሱ የሮማውያን ግዛት

በ8ኛው ምዕተ ዓመት ላይ በሮም ጳጳስና በፍራንካዊያን መሪዎች መካከል ቃል ኪዳን ተመሥርቷል። ሎምባርዳዊያንና ሌሎች ጠላቶችም ጭምርት በሮም አስነስተውት ከነበርው ቀዋሚ የተነሣ ጳጳሱ የፍራንካውያንን መሪዎች ድጋፍ ፈልጎ ነበር። ፍራንካውያን መሪዎች ለጳጳሱ ድጋፍ ትልቅ ግምት ሰጥተዋል። በ752 ዓ.ም. ፔፒን ከሌሎች ሰዎች የነጠቃቸውን መሬቶች ለጳጳሱ ሰጥቶታል፤ ይህም የጳጳሳት አገዛዝ መጀመሪያ ነበር።

በ799 ዓ.ም. የሮም ህዝብ ጳጳሱ የከፋ በደሎችን ፈጽሟል ብለው ከሰውታል። ቻርለማኝ ጳጳሱን ከሮም ህዝብ ቀጣ አድኖታል። በተጨማሪ ከሎምባርዳውያንም አትርፎታል። የገና በዓል በተከበረበት ዕለት ጳጳሱ ቻርለማኝን የቅዱሱ የሮማዊያን ግዛት ንጉሥ ነገሥት አድርጎ ዘውድ ጭኖለታል። የጳጳሱ ሥልጣን በቤተ ክርስቲያን ላይ እንጂ በመንግሥት ላይ አይደለም በማለት ብዙዎቹ የቻረለማኝን ሥራ ተቃውመዋል። ይህ የጳጳሱ ሥልጣን ለብዙ ዓመታት በርካታ ግጭትና ምሬት አስከትሏል። የሮም ጳጳስ የጴጥሮስ ምትክ ነኝ በማለት ለብዙ ምዕተ ዓመታት በጠቅላላ የአውሮፖ ክርስቲያኖች መካከል በማናቸውም ዓይነት ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ ገብቷል።

የቻርለማኝ ሕግጋት በመንግሥት ጉዳዮች ላይ ተግባራዊ የሚሆኑትን ያህል በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ተግባራዊ ነበሩ። ካህናት ሚስቶች ወይም ዕቁባቶች እንዳይኖራቸው፤ ወደ መሸታ ቤቶች እንዳይሄዱ፣ ለአደን እንዳይወጡ ወይም በማናቸውም ዓለማዊ ተግባራት ራሳቸውን እንዳያጠላልፉ ቻርለማኝ ከልክሏቸው ነበር። ጳጳሳት እና የደብር አለቆች የራሳችው የሆኑ ትምህርት ቤቶችን እንዲያቋቁሙ አዟል። እያንዳንዱ ካህን ይህንን ተግባር እንዲፈጽም ይፈልግ ነበር። ቻርለማኝ ለትምህርት የሰጠው ከፍተኛ ግምት በግዛቱ ላይ ትልቅ እርዳታ ለግሷል። ይህም ለመካከለኛው ዘመን ትምህርታዊ ሥልጠና ጥርጊያ መንገድ አዘጋጅቷል።

## የምስሎች አምልኮ

በሰበተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ታላቁ ግሪጎር ሥዕሎችና ምስሎች በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በአገልግሎት ላይ እንዲውሉ ፈቅዷል። ግሪጎር እነዚህ ነገሮች ሊመለክባቸው እንደማይገባ ተናግሯል። ይሁንና በ8ኛው ምዕተ ዓመት ላይ በእነዚህ ነገሮች ስም ፀሎቶች ይደረጉ ነበር። ይህም ክርስቲያኖች ጣዖት አምላኪዎች ናቸው ብለው እስላሞች እንዲከሷቸው ሊያደርግ የሚችል አጉል ልማድ ሆኗል። ከውበታቸው የተነሣና ያልተማሩ ሰዎችን ለመርዳት ሲባል ወደ ቤተ ክርስቲያን የገቡት ነገሮች ጣዖታት ሊሆኑ ችለዋል።

ምስሎችና ሥዕሎች መሳለም አማይቻልበት ከፍተኛ ሥፍራ እንዲሰቀሉ ሣልሳዊ ሌዮ አዟል። የኮንስታንቲኖፕሉ ጳጳስና ተከታዮቹ በዚህ ነገር በጣም ስለተቆጡ አመፅ ሊፈጠር ችሎ ነበር። ከዚያም ንጉሥና መማክርቱ እነዚህ ነገሮች ጨርሰው እንዲወገዱ ትዕዛዝ ሰጥተዋል። ወዲያውኑ በጳጳሱና በንጉሡ መካከል የከረረ ግጭት ተፈጠረ። ንጉሥ ሣልሳዊ ሌዮ ትዕዛዞቹ በጭካኔ ተፈጻሚ እንዲሆኑ አድርጓል። ጳጳሱ ሣልሳዊ ግሪጎርም ንጉሡን አውግዞታል።

በ734 ዓ.ም. አምስተኛው ኮንስታንቲን የተባለው ንጉሥ በኮንስታንቲኖፕል ከተማ አንድ ጉባዔ ሰብስቦ ነበር። ጉባዔው የምስል አምልኮ "የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን" አራሚና የክርስትናን ልማድ የሚንጻረር ነው በማለት እንዲቆም ወስኗል። ምስሎች እንደ ጣዖታት ተቆጥረው እና በፊታቸው ዕጣን ይጨስ ስለ ነበር ይህ አንገብጋቢ ጥያቄ ነበር። ግጭቱም በክርስቲያኖች ዓለም ውስጥ የፍትህ መጓደልን አስከትሏል።

በ787 ዓ.ም. በሁለተኛው የኒቂያ ጉባዔ ወቅት የአራተኛው ሌዮ ሚስት የነበረቸው ባልቴት ውሳኔውና የሣልሳዊ ሌዮ መመሪያ ሙሉ በሙሉ እንዲሻር አድርጋለች። የክርስቶስ፣ የማሪያም፣ የቅዱሳንና የመላዕክት ምስሎች መስራት እንደሚችሉ ጉባዔው ወስኗል። ለምስሎቹም ክብር የዕጣንና የጧፍ ሥጦታዎች ሊሰጡ እንደሚችሉ አፅድቀዋል።

በም ዕራብ የነበሩት ቻርለማኝና የፍራንካውያን ካህናት ምስሎች በአገልግሎት ላይ መዋል እንደሌለባቸው በመቃወም ፀንተው ቀመዋል። በ794 ዓ.ም. በፍራንክፈርቱ ጉባዔ ላይ በእነዚህ ነገሮች ላይ የተቃውሞ ንግግር አሰምተዋል። ቻርለማኝ በመጽሐፍቱ ውስጥ - "መመለክ ያለበት እግዚአብሔር ብቻውን ነው። ቅዱሳን ሊከብሩ ብቻ ይገባል። ምስሎች በምንም ዓይነት ጨርሶ ሊመለኩ አይገባም" በማለት ጽፏል።

ከ731-741 ዓ.ም. በነበረው የሣልሳዊ ግሪጎሪ ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ ሎምባርዳውያን የጣሊያንን ቤተ ክርስቲያን ለማጥፋት ዝተው ነበር። ይሁንና የባሰው አደጋ የደረሰው ፈረንሳይን አቋርጠው ወደ ሰሜን ከተጓዙት እስላሞች ነበር። ቻርለስ ሞርቴል የተባለው አዝማች እስላሞችን በመጡበት ለመመለስ በቂ ኃይል ሰብስቦ ነበር። ከዚያም በጳጳሱና በንጉሡ መካከል የሮማውያን ግዛት ተብሎ የተጠራ ህብረት ተመሥርቷል። የእያንዳንዱ ዓላማ የሌላውን ፍላጎቶች ማስቀደም ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምስሎችን መገልገል በምሥራቅና በሮም አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረውን ልዩነት አስፍቶታል።

## <u>የክለሳ ጥያቄዎች</u>

1. ታላቁ ግሪጎሪ በጽሑፎች አማካይነት ማድረግ የቻለው ነገር ምን ነበር?
2. ቻርለማኝ ሽንጡን ገትሮ ይቀመላቸው ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው?
3. ቻርለማኝ ድል ለማግኘት የተጠቀመባቸው አጠራጣሪ መንገዶች ምን ምንድን ናቸው?
4. በ814 የተፈጠሩትን ሦስት ታላላቅ ግዛቶች ስም ጥቀሱ?
5. መሐመድ የተወለደው የትና መቼ ነበር?
6. በሚያውቃቸው ክርስቲያኖች ላይ የተጣለው ነገር ምንድን ነው?
7. መሐመድ የአረቢያን የባህላዊ ሃይማኖት የተወው ለምንድነው ነው?
8. መሐመድ የቁርዓንን ጽሑፎች የመሠረታቸው በምን ላይ ነው?
9. እስልምና በዘጠና ዓመታት ውስጥ ከየት እስከ የት ተሰራጨ?
10. የፍሬሺያን አካባቢ በወንጌል ያዳረሰው ማን ነው?
11. "የጀርመን ሐዋሪያ" ተብሎ ይጠራ የነበረው ማን ነው?
12. ሳክሶናዊያን ክርስትናን የጠሉት ለምንድን ነው?

13.ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት አንድ እንዲሆኑና በሕብረት እንዲሠሩ ያደርጋቸው ምንድን ነው?
14.የአንድ መንግሥትንና የአንዲት ቤተ ክርስቲያንን መፈጠር ሃሳብ በሚመለከት የብዙዎች አፀፋ ምን ነበር?
15.ቻርለማኝ በዘመነ መንግሥቱ ያስገኛቸው ጥቅሞች ምን ምንድን ናቸው?
16.ሥ ዕሎችና ምስሎች በአብያተ ክርስትያናት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲገቡ የተደረገው ለምንድን ነው?
17.ሥዕሎችና ምሳሌዎች ሁሉ እንዲወገዱ ያዘዘው ማን ነበር?
18.የምስል አምልኮ "የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን አራሚና ፀረ-ክርስቲያን ልማድ" ብሎ የጠራው ንጉሥ ማን ነበር?
19.ምስሎች በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መኖር አለባቸው በማለት የወሰነው የትኛው ጉባዔ ነው?
20.ምስሎችን በሚመለከት ቻርለማኝ የተናገረው ነገር ምንድን ነው?

## ምዕራፍ ስምንት - ሁከትና ሴራ

### መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የሚያተኩረው በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ባለው ግኑኙነት ነው። ይህ ቀላል ጥያቄ አይደለም፤ ብዙ የተለያዩ መልሶች የተሰጡትም ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ መንግሥት ደከም ባለበት ወቅት የተፈጸሙትን ድርጊቶችና ከዚያ ቤተ ክርስቲያን በምድሪቱ ላይ የበላይነት ሥልጣን ይገባኛል ማለቷን ብቻ እንመለከታለን። የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች የእግዚአብሔር ቤተሰቦች አገልጋዮች በመሆን ፋንታ መሪዎች መሆን ጀምረዋል፤ ለመምራት ይጥሩ የነበረውም ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያለውን አካባቢ ጭምር ነበር። ይህም የዝንባሌዎች ግጭት ከመፍጠሩም በላይ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ ያለችበትን ዓላማ እንድትዘነጋ አድርጓታል።

### ሐሰተኛ ትዕዛዞች

የሮም ጳጳስ የፍራንካዊያን ነገሥታት የነበሩትን በ752 ዓ.ም. ፔፒንና በ800 ዓ.ም. ቻርለማኝን እንዴት እንዳነገሡ ተመልክተናል። ይህም የሮም ጳጳሳት በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ መግባት የጀመሩበት ዘመን ነበር። ለምዕራብም ቤተ ክርስቲያን ሥልጣን አስገኝቶላታል። ጥቂቶች ይህንን ሃሳብ ለማጠናከር ከጅለው የቤተ ክርስቲያን ጉባዔዎች የጳጳሳት ውሳኔዎች ናቸው የሚሏቸውን አንዳንድ ትዕዛዛት አውጥተው ነበር።

በ850 ዓ.ም. አካባቢ አንድ ፍራንካዊ ካህን ጥቂት ትዕዛዛትን ሰብስቦ የያዘ አንድ ጥራዝ አዘጋጅቷል። ካህኑ ይህንን ጥራዝ የሰበሰበው የሰባተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ታላቅ ጸሐፊና የእስፔን ጳጳስ የነበረው የሲቪሉ ኢሲዶር ነው ብሏል። እውነተኛ የሆኑት የጳጳሳት ትዕዛዛት የተሰጡት ከ384-398 ዓ.ም. ሲሆን በዚህ ጥራዝ ውስጥ ግን በመጀመሪያ ምዕተ ዓመት የተጻፉ ናቸው የተባሉ ደብዳቤዎች ውሳኔዎችና ሕግጋት ይገኙበት ነበር። እነዚህን የሐሰት ሰነዶችና ትዕዛዞች ያዘጋጀው ሰው ብልሃተኛና በሚገባ የተማረ ነበር።

የእነዚህ የሐሰት ጽሑፎች ዓላማ ጳጳሱ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥትን ልገዛ ይገባኛል ማለቱን መደገፍ ነበር። የሮም ቤተ ክርስቲያን የይገባኛል ጥያቄና ሥልጣን የተገነባው በእነዚህ መሠረቶች ላይ ነበር። በኋላ በ15ኛው ምዕተ ዓመት ላይ ምሁራን እነዚህ ሰነዶች የተሳሰቱ መኖናቸውን አረጋግጠዋል። ይሁንና ይህ የሮምን ቤተ ክርስቲያን ብዙም አልለወጣትም።

## የኮንስታንቲን አስተዋፆ

ሌላው የተሳሰተ ሰነድ ኮንስታንቲን በ324 ዓ.ም. በጳጳስ ሲልቬስተር መጠመቁን ይናገራል። ይሁን እንጂ ኮንስታንቲን የተጠመቀው በ337 ዓ.ም. በኒኮመዲያው ኢዩሲቢዮስ እንጂ በሲልቬስተር አልነበረም። ይህ የተሳሳተ ሰነድ 500 ዓመታት ቀደም ብሎ የሮም ጳጳስ ምድራዊ ሥልጣን ባገኘበት ዘመን የተጻፈ ለማስመሰል ጥረት ተደርጓል። በየዋህነት ተነሳስተው ሊሆን ይችላል እንጂ የኋለኞቹ ትውልዶችም ጳጳሳት ከፍተኛ ሥልጣን ይገባናል ያሉት እነዚህን የሐሰት ሰነዶች ተመርኩዘው ነበር።

ከ858-867 ጳጳስ የነበረው ቀዳማዊ ኒኮላስም - "ጳጳስ የሚወስነው ነገር ሁሉ መከበር እንዳለበት" አውጇል። ቀዳማዊ ኒኮላስ ሥልጣኑ ተነጥቆ የነበረ አንድ ጳጳስን ወደ ቀድሞ ሹመቱ ለመመለስና ንጉሥ ዳግማዊ ሎቴር የፈታትን ንግሥት መልሶ ሚስቱ እንዲያደርጋት ለማስገደድ በነበረው ሥልጣን ተጠቅሞበታል። በንጉሡ ሴራ ውስጥ ስለተባበሩ ሁለት ጳጳሳትን ከሥልጣን አውርዷቸዋል።

## ሁከት በቤተ ክርስቲያን

ዳግማዊ ሎቴር የሥነ-ምግባር ስህተት ስለፈፀመ ቀዳማዊ ኒኮላስ በእርሱ ላይ የነበረው ተቃውሞ ስምርለታል። ከእርሱ ቀጥለው ሥልጣን የያዙት ሁለት ጳጳሳት ከ 867-972 ዓ.ም. የነበረው ዳግማዊ ሐድርያንና ከ872-882 ዓ.ም. የነበረው ስባተኛው ጆን በአስተዳደር ነክ ግጭቶች ውስጥ ጣልቃ የመግባት መብት አለን ብለው ነበር። ይህም በጳጳሳትና በነገስታት መካከል የከረረ የአስተዳደር ነክ ጠቦች ዘመን አስከትሏል። የቻርለማኝ ልጆች በጣም ችሎታ የጎደላቸውና የላሸቁ ስለ ነበሩ "ቻርልስ ዱባው" ተብሎ ይጠራ የነበረው የመጨረሻ ንጉስ ሥልጣኑን ተነጥቋል። ይህም የቻርለማኝ ግዛት እንዲያከትም አድርጎታል።

ቻርልስ ዱባው ከሥልጣን ከወረደ በኋላ ከእስካንዲኔቪያ የመጡ የሮርዝሜን ወራሪዎች የጀርመንንና የፈረንሳይን ድንበሮች ወርረው የባህር ወደቦችን ደምስሰዋል። በኋላም ክርስትናን ተቀብለው በኖርማንዲ ሰፍረዋል። እዚያ ሆነው እ1066 ዓ.ም. ኢንግላንድን ወግተዋል። የእስላም ሠራዊት በ9ኛው ምዕተ ዓመት ላይ ከአፍሪካ በመነሳት ሲሲሊንና ደቡብ ጣሊያንን በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል። ከምሥራቅ በኩል የሐንጋሪዎቹ ማጂያራዊያን ስጋት ፈጥረው ነበር። እነዚህ ነገሮች በአጠቃለይ በሐይማኖታዊና ህዝባዊ ኑሮ ላይ ብጥብጥ አስከትለዋል። ከዚህ በኋላ የጣሊያን መሳፍንት በጣም አይለው የበላይነት ክብር ለማግኘት እርስ በእርስ ይዋጉ ነበር። ይህም ሁከት በቤተ ክርስቲያን ላይ ብዙ መከራ አምጥቷል። አንድ ጳጳስ ሌላውን ተከትሎ ከሥልጣን ይባረር፣ ይታሰርና ይገደል ነበር። ከ50 ለበለጡ ዓመታት ያህል መሳፍንት ሮምንና የጵጵስናን አገልግሎት በቁጥጥራቸው ሥር አድርገዋል። በዚህ ዘመን በሮም ጳጳሳት የነበሩት ሥነ-ምግባር የጎደላቸው ይሁኑ እንጂ ከፍተኛ ደረጃና ጠንካራ አዕምሮ የነበራቸው ቴኦዶራና ሁለት ሴቶች ልጆችዋ ነበሩ።

አሁንም ብዙዎች ጥንታዊው የሮማዊያን ግዛት እንዲያንሰራራ ይፈልጉ ነበር። እያሌ ሙከራዎች የተደረጉ ቢሆንም አልተሳኩም። በ960 ዓ.ም. አጅግ መጥፎ ከሚባሉት ጳጳሳት አንዱ ጳጳስ ጆን ስባተኛው የጀርመን ንጉሥ የነበረውን ቀዳማዊ ኦቶን ከጣሊያን ንጉሥ ከዳግማዊ በረንጀር እንዲጠብቀው ለምኖታል። ኦቶም ከእርሱ በፊት ከፔፒንና ቻርለማኝ እንዳደረጉት ጳጳሳትን ደግፏል። በኋላ ጳጳስ ጆን ኦቶን ስለተቃወመው ሊበቀለው የጵጵስና ማ ዕረጉን ነጥቆታል። ኦቶ ታላቅ ንጉስና የጵጵስናን አገልግሎት ሥነ-ምግባር ለመጠበቅ የረዳ ሰው ነበር። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ነጻነቷን አጥታለች።

በ1044-1046 መካከል ጳጳስ ልንሆን ይገባል የሚሉ ሦስት ሰዎች ተነስተዋል። እነርሱም ቤነዲክት ዘጠነኛ ሣልሳዊ ሲልቬስተርና ግሪጎሪ ስድስተኛው ነበሩ። በ1046 ዓ.ም. አንድ ጉባዔ ንጉሥ ሳልሳዊ ሔንሪ

ወደፊት ጳጳሳት የሚሆኑትን ሰዎች እንዲሰይም አድርጓል። ይህም በዚያ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን አድኗታል። ከዚያም ሒልዴብራንድ የተባለው መነኩሴ እንደ የተሃድሶ ቡድን በሮም ይመራ ነበር። ሒልዴብራንድ ጳጳሳትን የመምረጥ ተግባር የንጉሥ ወይም የቤተ ክርስቲያን ጣልቃ ገብነት ሳይጨመርበት ላካህናት እንዲሰጥ ይደግፍ ነበር። ሒልዴብራንድ ይጠቀምባቸው የነበሩት ዘዴዎች ጭካኔ የተሞላባቸው ሲሆኑ በወታደራዊ ኃይልም ይገለገል ነበር።

## የክርስትና በአውሮፓ መስፋፋት - 800-1073 ዓ.ም.

በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ አንስጋር የተባለው ሰው ወንጌልን ይዞ ወደ ዴንማርክና ኖርዌይ ሄደ። ሆኖም እስከ 11ኛው ምዕተ ዓመት ድረስ የእስክንዲኔቪያን አገሮች በሙሉ ክርስቲያን አልሆኑም።

በ864 ዓ.ም. የአውስትሪያ የሞራቪያ መሪ አገሩን የስም ክርስቲያን ማድረግ እስኪሳካለት ድረስ በስሩ የነበሩትን ሰዎች ጨፍጭፏል። በ848 ዓ.ም. 14 ቦሔማዊያን የሆኑ የቼኮዝላቫኪያ ልኡላን ተጠምቀዋል። ይሁን እንጂ ክርስትና የመጣላቸው በጀርመን ሰዎች አማካይነት በመሆኑ ህዝቡ ክርስትናን ተዋግቶታል። በ806 ዓ.ም. የቡልጋሪያ ንጉሥ የነበረው ቦሪስ አገሩን ክርስቲያን ለማድረግ ሲጣጣር ብዙ ህዝብ ፈጅቷል። ከ973 ዓ.ም. ወዲህ የሐንጋሪዎቹ ማጊያራዊያን ፒልግሪም በተባለ ሰው ሥራ አማካይነት በክርስትና ሊሳቡ ችለዋል።

በግሪክ ቤተ ክርስቲያን ወንጌላዊያን አማካይነት ሩሲያውያን በ988 ዓ.ም. ከኮንስታንቲኖፕል ወንጌልን ተቀብለዋል። እነዚህ ሰዎች የተላኩት ንጉሥ ብላድሚር ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ነበር። እስልምና በሌሎች አካባቢዎች በሰፈነበት ወቅት የግሪክ ቤተ ክርስቲያን መሸሸጊያ ከሆኑት ሥፍራዎች መካከል አንዷ ነበረች።

በ13ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ ከፊንላንድና ከላፕላንድ በስተቀር ቢያንስ የስም ክርስትና በመላው አውሮፓ ሰፍኖ ነበር።

## ማጠቃለያ

በምዕራብ ግዛቶች ውስጥ የመንግሥት ሥልጣን እየተዳከመ ሲሄድ ሥርዓቱን ለማስጠበቅ ጳጳሳት ሥልጣን ለማጠናከር እንዲያመች ያልታወቀ ሰው የሐሰት ሰነዶችን አቅርቧል።

ከዚህ ቀጥሎ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሁከት ዘመን ተፈጥሮ ነበር። ቀዳማዊ ኦቶ ከእርሱ በፊት እንደነበሩት እንደ ፔፒንና ቻርለማኝ አዲስ ግዛት አስተባብሯል፤ ቢሆንም ቤተ ክርስቲያን ነጻነቷን አጥታለች።

ሒልዴብራንድ በተባለ መነኩሴ አማካይነት በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሃድሶዎች ተደርገዋል። ወንጌል በአውሮፓ ውስጥ መስራጨቱን ስለቀጠለ በ13ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ ከፊንላንድና ከላፕላንድ በስተቀር መላው አውሮፓ የስም ክርስቲያን ሆኖ ነበር።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንዳንድ ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ሥልጣን ለማጠናከር የተጠቀሙባቸው ዘዴዎች የትኞቹ ናቸው?
2. የሐሰት ትምህርት ጸፈዋል ተብለው የተጠረጠሩትን ሁለት ሰዎች ስም ጥቀሱ።

3. ቀዳማዊ ኒኮላስ ጳጳሱን በሚመለከት ያወጀው አዋጅ ምን ነበር?
4. የቻርለማኝ ግዛት ውድቀት ምክንያት ምንድን ነው? የወደቀውስ መቼ ነበር?
5. የጣሊያን መሳፍንት ለከፍተኛ ክብር በተፋጩባቸው ዓመታት የተፈጸመው ድርጊት ምንድን ነው?
6. የ12ኛው ጀን ዕርዳታ የጠየቀው ከማን ነበር?
7. የቀዳማዊ ኦቶ ጣልቃ ገብነት ምን አስከተለ?
8. የሰሜን ወራሪ ጎሳዎች እነማን ነበሩ? የደቡብና የምሥራቅስ?
9. ጳጳስ መሆን ይፈልጉ የነበሩት ሦስት ሰዎች ማን ማን ነበሩ?
10.በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሃድሶ ያስደረገው ሰው ማን ነበር?
11.እስካንዲኔቪያውያን ክርስትናን የተቀበሉት በየትኛው ምዕተ ዓመት ነበር?
12.የቼኮዝላቫኪያና የኦስትሪያ ህዝብ ክርስትናን የተቃወሙት ለምንድነው?
13.ወንጌልን ወደ ሩሲያ የወሰደችው ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?
14.ከአውሮፓ አገሮች መካከል በ13ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ ገና የስም ክርስትናን እንኳ ያልተቀበሉት ማንና ማን ነበሩ?

## ምዕራፍ ዘጠኝ - ከግሪጎሪ ሰባተኛው እስከ ቦኒፌስ ስምንተኛው

## 1073 -1294 ዓ.ም.

### የጵጵስና ሥልጣን የዕድገት ደረጃ

በ1073 ዓ.ም. ሒልዴብራንድ ጳጳስ ሆኗል። ግሪጎር ሰባተኛው የሚል ስያሜም ተሰጥቶታል። የክርስቶስ እንደራሴና የጴጥሮስ ተወካይ እንደመሆኔ መጠን ግዛቶችን መንግሥታትንና የሰዎችን ሁሉ ንብረት ልወስድ እችላለሁ ሲል አውጇል። ከንጉሡ አንስቶ እስከ ጢሰኛው ገበሬ ያለው ሰው ሁሉ እኔን አሜን ብሎ መቀበል አለበት የሚል ሃሳብ ነበረው።

ሒልዴብራንድ የሮም ቤተ ክርስቲያን ካህናት ሁሉ ሚስት ማግባት የለባቸውም በማለት ከልክሏል። ከዚያም ለካህንነት ዕጩ ሆኖ ለመቅረብ የሚሰጠውን የገንዘብ ስጦታ አስቁሟል። ምክንያቱም አንዳንድ መሳፍንት የተቀደሱ ሹመቶችን የመንፈሳዊ ህይወት ብቃት የሌለው ቢሆንም እንኳ ከፍተኛ ዋጋ ለሚከፍል ተጫራች ይሸጧቸው ነበር።

በአብዛኛው የሮማዊያን ግዛት ውስጥ በዚያ ዘመን ሰፍኖ በነበረው የተለመደ የመሬት ይዞታ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ወይም ሰዎች መሬቱን በተጠቃሚነት የያዙት መሆኑን የሚጠቁሙት በአንዳንድ ክበረ በዓላት አማካይነት ብቻ ነበር። በዚህ ጊዜ መሬቱን እንዲጠቀሙበት ባለቤቱ ሕጋዊ መብት ይሰጣቸው ነበር። ለመንግሥትም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን ሥልጣኖች ይሰራበት የነበረው ልማድ አንድ ዓይነት ነበር። ሒልዴብራንድ ቤተ ክርስቲያንን ከመንግሥት በላይ ነች ሲል ይህንን ሕግ መቀናቀኑ ነበር። መንግሥትም ደግሞ በፊናው ቤተ ክርስቲያን በትክክል የራሷ ንብረት ያልሆኑ ሰፋፊ መሬቶችን ይዛለች ሲል መልሶ ተዋግቷታል። በመጨረሻም ሒልዴብራንድ ልማዳዊውን ሕግ በመጣስ በመሬት አጠቃቀም ረገድም ሆነ ሹማምንትን በመሾም ቤተ ክርስቲያን የመንግሥት የበላይ ናት ሲል ተናግሯል።

በ1075 ዓ.ም. ሒልዴብራንድ የመሬት ይዞታን የሚመለከተውን ሕግ አልታዘዘም በማለት ንጉሡን ሔንሪ አራተኛውን እንደጉልተኛ በመቁጠር ወደ ሮም እንዲመጣ ጥሪ አድርጎለታል። ንጉሡ አልመጣም በማለት ጳጳሱን ከሥልጣን ለማውረድ አንድ የጀርመን ጉባዔ አስገድዷል። ይሁን እንጂ ንጉሡ ከዚያ ጊዜ ወዲህ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ግንኙነት እንዳያደርግ ተከልክሏል። ከንጉሡም ጋር ማንም ሊገናኝ ወይም ምግብና መጠለያ ሊሰጠው ተከልክሏል። ከንጉሡም ጋር ማንም ሊገናኝ ወይም ምግብና መጠለያ ሊሰጠው

ተክልክሏል። በዚህ ሁኔታ አንድ ዓመት ከቆየ በኋላ ንጉሥ ሚስቱና ልጆቹ ከጳጳስ ሒልዴብራንድ ጋር ሰላም ሊፈጥሩ በክረምት ወራት የኤልፐስን ተራሮች አቋርጠው ሄዱ። ንጉሥ ሔንሪ አራተኛው ወረዳ ጢሰኛ ገበሬ የሚያስመስል ልብስ ለብሶ ወደ ጳጳሱ ግቢ ገባ። ሒልዴብራንድም ለሦስት ቀናት በግቢው ውስጥ በበረዶ ላይ አቆመው። ጳጳስ በቤተ ክርስቲያን ተግባሮቹና በአስተዳደር ጉዳዮቹ መካከል በትግል ላይ ነበር። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ተፀፅቶ ሲመጣ የኃጢአቱን ስርየት ሊያገኝ ይገባል። ስለዚህ በአራተኛ ቀን ጳጳሱ ንጉሡን ተቀብሎ ኃጢአቱን ይቅር ሰላለው መንግሥቱ እንደገና ታድሷል። ይህም ለጵጵስና አገልግሎት ድል እንደሆነ ተገምቶ ነበር፤ ሆኖም ከብዙ ግጭቶች በኋላ ሔንሪ አራተኛ ሒልዴብራንድን ሊያስወግደው ችሏል።

ግሪጎሪ ከሞተም በኋላ የመሬትን ዝውውር በሚመለከት ትግሉ ለተጨማሪ 35 ዓመታት ቀጥሏል። በመጨረሻም በ1122 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት "የዎርምስ ኮንኮርዳት" የሚል ስያሜ የተሰጠው ስምምነት ላይ ደርሰዋል። መሬትን የማዘዋወር ሥልጣን ለንጉሥ ተሰጥቶታል። ዝውውሩም የሚከናወነው በነገሩ ጣልቃ ሳይገባ ጳጳሱ በተገኘበት ነበር። ረጅም የመሬት ጭቅጭቅ እንዲያከትም አድርጓል።

ከ1100 -1153 ዓ.ም. የነበረው የብሬሺያው አርኖልድ ቤተ ክርስቲያን በአዲስ ኪዳን ዘመን ወደ ነበረው ቀለል ያለ ኑሮ እንድትመለስ ተማፅኗል። ከገዳማት እንቅስቃሴዎች አንዱን ይመራ የነበረው የክሌርቮክሱ በርናርድ አርኖርድን ተቃውሞታል። በ1143 ዓ.ም. አርኖርድ በሮም የጋለ ልባዊ አቀባበል ተደርጎለታል። በጣሊያን ህዝባዊ መንግሥትም ታውጆ ነበር፤ ይሁን እንጂ በወቅቱ በተፈጠረው ግጭት አንድ ጳጳስ ሲገደል ይከተለው የነበረው ጳጳስ ወደ ፈረንሳይ ሸሽቷል።

ንጉሥ ፍሬደሪክ ባርባሮሳ ወይም ቀዳማዊ ፍሬደሪክ ወደ ጣሊያን ዘመቶ የሎምባርዶችን ከተሞች በቁጥጥር ሥር አድርጓል። በዚህ ወቅት የብሬሺያው አርኖርድ ተገድሏል። ፍሬደሪክ የጳጳሱን የበላይ ገዢነት ይቃውም ስለነበር ከጳጳሱ ጋር የነበረው ወዳጅነት የአጭር ጊዜ ነበር። በ1176 ዓ.ም. ፍሬደሪክ በሎምባርድ ማህበር ተሸንፏል። በጣሊያን ውስጥ ቬኒስ በተባለው ከተማ ፍሬደሪክ እጁን ሰጥቶ በጳጳስ እስክንድር ፊት ተንበርክኳል። የጳጳሱንም እግሮች ስም በየጎዳናዎቹ የጳጳሱን ፈረስ እየመራ ታይቷል። ይህም ለጳጳስ እስክንድር ሒልዴብራንድ ቀደም ባለው ምዕተ ዓመት በሔንሪ አራተኛ ላይ ከተቀዳጀው እጅግ የበለጠ ድል አስገኝቷል።

## <u>የመስቀል ጦርነቶች - 1095-1270 ዓ.ም.</u>

በ12ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ ቤተ ክርስቲያን የምሥራቅና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ተብላ ተከፍላና ጦርነት ቦጫጭቋት ነበር። እስልምና ሶሪያን፣ እስራኤልን፣ ግብፅንና ሰሜን አፍሪካን ከምሥራቅ ግዛት ነጥቆ ነበር። እስልምና ከአፍሪካ ወደ እስፔይንና ፈረንሳይ ባፋጣኝ ተሻግሮ ነበር። የመሐመድ ተከታዮች በፈጠሯቸው ውጊያዎች ሳቢያ ቤተ ክርስቲያን በምሥራቅ ብዙ ሰፋፊ አካባቢዎች ተወስደውበታል። በምዕ. 7 የሚገኘውን ካርታ ተመልከቱ።

ጳጳስ ግሪጎር ሰባተኛው ወይም ሒልዴብራንድ የምሥራቅና የምዕራብን አብያተ ክርስቲያናት ለማዋሐድ ይጓጓ ነበር። የመሐመድ ተከታይ የሆኑት ቱርኮች ሲወሩት የምሥራቁ ንጉሥ ግሪጎርን እንዲረዳው ስለለመነው ይህ ምሥራቅንና ምዕራብን ለማዋሐድ አመቺ ሁኔታ እንደሆነ አሰቦ ነበር። ግሪጎሪ የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያንን በማዳን ዓለማቀፍ የጵጵስና አመራር እመሰርታለሁ የሚል ተስፋ ነበረው።

ይህም የመስቀል ጦርነት ጅማሬ ነበር። በምዕራብ አውሮፓ የነበሩት አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ለምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን እስከዚህም በጣም አላሰቡም። ይሁን እንጂ ብዙዎቹ ወደ ቅዱስ ስፍራ ጉዞ አድርገው ስለ

ነበረ አሁን በማያምኑ ሰዎች እጅ መውደቁ ሰድብ መስሎ ታይቷቸው ነበር። ሃይማኖት አክራሪ የሆኑት እስላም ቱርኮች ክርስቲያኖችን አይወዱም።

ሒልዴብራንድ "የመስቀል ጦርነት" በማለት የጀመረው ሃሳብ በኋላ በሌሎች ጳጳሳት አማካይነት ተካሂዷል።

ከ1088-1099 ዓ.ም. ጳጳስ የነበረው ዳግማዊ እርባን የመጀመሪያውን የመስቀል ጦርነት አስደርጓል። ይህም ለእርሱና ለጽጽሰናው ሥርዓት ከፍተኛ ክብር ያስገኛል የሚል ግምት ነበረው። ሕዝቡ በጦርነቱ እንዲሳተፍ ለማሳመን በብዙ ነገሮች ተጠቅሟል። ከእነዚህም መካከል ከማንኛቸውም ዓይነት ኃጢአት ሁሉ ማስተሰረይ፣ በኃጢአት ለወደቁ ሰዎች ዘላለማዊ በረከት መስጠት ከዕዳ ሁሉ ነፃ ማድረግ ለወንጀለኞች ምህረት መስጠትና በመንገዳቸው እንዲረዳቸው ታምራት መፈጸም ይገኙባቸዋል። ሰው ሃጢአት ከሠራ በኋላ ጳጳሱ የደነገገውን ምፅዋት በሰጠ ቁጥር ኃጢአቱ ወዲያውኑ ይደመሰሰታል የሚለው ትምህርት በዘልማድ የኃጢአት ክፍያ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል ከዚህም የተነሣ ይህ ትምህርት በመስቀል ጦርነቶች ወቅት ከመጠን በላይ ተስፋፍቷል።

ሰዎች በመስቀል ጦርነቶች እንዲሳተፉ ያሳምን የነበረው ሌላው ሰው ባሕታዊው ጴጥሮስ ነበር። ይህ ሰው ሰድና ያልታረመ ሰባኪ ቢሆንም በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በመስቀል ጦርነቶች ውስጥ እንዲካፈሉ አድርጓል። በመስቀል ጦርነትም አለመሳተፍ እንደ ሐፍረት ተቆጥሮ ነበር። በ1096 ዓ.ም. በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወንዶች ሴቶችና ሕጻናት ችግሮቻችን በተዓምር ይቃለሉልናል በሚል ግምት ዘምተው ነበር። ከእነዚህ ቡድኖች ጋር ከተቀላቀሉት 275000 ሰዎች በሙሉ በብርድ ወይም በበሽታ ወይም የደረሱበት ሳይታወቅ አልቀው ቀርተዋል። ጴጥሮስ ራሱ የመጀመሪያውን የአደጋ ምልክት ሲመለከት ኮብልሏል።

የመጀመሪያው ይፋ የመስቀል ጦርነት 300000 ሰዎችን አስልፎ በነሐሴ ወር 1096 ዓ.ም. በኮንስታንቲኖፐል በኩል ዘምቷል። ብርድ የእርስ በእርስ ሹክቻዎችና ምቀኝነቶች ዘመቻውን አዳክመውታል። ጥቂት ኀበዞች ጉዞአቸውን ሳያቋርጡ በ1099 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም ደርሰዋል። ጉዞውን የፈጸሙት ከአውሮፓ ከተነሱት ውስጥ አንድ አሰረኛዎቹ ብቻ ነበሩ ኢየሩሳሌም ሲገቡ ሳራሰኞችን ወይም እስላም አረቦችን ጨፍጭፈዋቸዋል።

ሁለተኛው የመስቀል ጦርነት የታቀደው ቱርኮች ኦዴሳን ከክርስቲያኖች ነጥቀው በያዙበት ወቅት በ1144 ዓ.ም. ነበር፤ ይሁን እንጂ ውጤቱ ሽንፈት ሆኗል። በ1187 ዓ.ም. ኢየሩሳሌም እንደገና በሳራሰኞች መሪ በሳላዲን ስትያዝ ሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ታቅዷል። ሦስቱ ነገሥታት ፍሬደሪክ ባርባሮሳ የፈረንሳዩ ፊሊፐና የኢንግላንዱ አንበሳው ሪቻርድ ብርቱ ሠራዊት አስልፈው ወደ ቅዱስ ምድር ዘምተዋል። ፍሬደሪክ ሲሞት ፊሊፐና ሪቻርድ ምንም እንኳ ታላቅ ወኔ ቢኖራቸውም የመስቀል ጦርነቱን መፈጸም ተሰኗቸዋል።

አምስተኛው፣ ሰባተኛውና ስምንተኛው የመስቀል ጦርነቶች በሙሉ የተሳካ ውጤት አላስገኙም። በ1270 ዓ.ም. የመስቀል ጦርነቶቹ ሲያበቁ ከጳጳሱ በቀር አውሮፓ በሙሉ እሮይ ብሏል።

በመስቀል ጦርነቶች ውስጥ የተሳተፉት አብዛኞቹ ሰዎች ዓላማቸው የተሳሰተ ነበር። የሥነ-ምግባር ጉድለት ዘረፋና ጭፍጨፋ እንቅስቃሴውን አሳፋሪ አድርጎታል። ብዙዎችን ሰዎች ያነሳሳቸው እውነተኛ መንፈሳዊ ኃይልና ፍላጎት አልነበረም። በአመዛኙ ከሃማኖታዊ ይልቅ አስተዳደርና ሕብረተሰብ ነክ ምክንያቶች ነበራቸው።

## ጳጳስ ሳልሳዊ ኢኖሰንት - 1198-1216 ዓ.ም.

በጳጳስ ኢኖሰንት ዘመን ጵጵስና ከፍተኛ ሥልጣኑን ጨብጧል። የኢኖሰንት መመሪያ ከሒልዴብራንድ ጋር ተመሳሳይ ነበር፤ ይሁንና በማስፈጸም ረገድ እርሱ በጣም ተሳክቶለታል። የሔንሪ አራተኛውና በኋላም የፍሬደሪክ ባርባሮስ በቬኒስ መዋረድ ህዝቡን በጳጳስ የበላይነት እንዲያምኑ አድርጓቸዋል። የመስቀል ጦርነቶች የጳጳሳትን ክብር ከፍ አድርገውታል።

የሳልሳዊ ኢኖሰንት ድል የሚያስደንቅ ነበር። የኢንግላንዱ ንጉሥ ጆንና የፈረንሳዩ ፊሊፕ ተዋርደው ራሳቸውን አስገዝተዋል። የሳልሳዊ ኢኖሰንት የአስተዳደር ሥልጣን በክርስቲያን ምድሮቹ ሁሉ ላይ ሰፍኖ ነበር። አራተኛውን የመስቀል ጦርነት ያዘመተው እርሱ ነው። መናፍቃን ናቸው ብሎ ባሰባቸው በደቡብ ፈረንሳይ በሚገኙበት በጀግኖቹ አልቢጀንሳዊያን ላይ ጦርነት እንዲደረገ አዟል። ለጵጵስና ሥልጣን ከፍተኛ የነበረው ቤተ ክርስቲያን ደርሳበት የማታውቀውን የመጨረሻ ትልቅ ሥልጣን ያስገኘው በ1215 ዓ.ም. የተካሄደው የላተራን ጉባዔ ነበር።

## ጳጳስ ስምንተኛው ቦንፌስ - 1294 -1303 ዓ.ም.

የጵጵስና ከፍተኛ ስልጣን እስከ ቦንፌስ ስምንተኛ ዘመን አልተቋረጠም። ቦንፌስ መሪዎች ሁሉ በእኔ ሥር ናቸው ሲል አጥብቆ ተናግሯል። ቦንፌስ "ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ደህንነት ለማግኘት ለሮም ጳጳስ መገዛት ያስፈልገዋል እያልን እናውጃለን፣ እንናገራለን፣ እናስረዳለን፣ እንዲህም እንገልጻለን" ሲል ጽፏል።

የጳጳሳት ንግግሮች መረቀቅ በርካታ መሪዎችን ስላስቆጣ ብርቱ እመፆችን ፈጥሯል። የኢንግላንዱ ቀዳማዊ ኤድዋርድና የፈረንሳዩ ደጉ ፊሊፕ ቦንፌስን ተቃውመው በኋላ አስረውታል። እስኪሞትም ድረስ ክፉኛ ተንገላቷል። ይህም በመንግሥታት ዘንድ ጵጵስናን በሚመለከት የአቋም ለውጥ መደረጉን ጠቁሟል። በርካታ የጎሳ መሪዎችን በቁጥጥር ሥር ከማዋል ይልቅ አንድን ንጉሥ መቆጣጣር ይቀል ነበር። የጳጳሳትም ሥልጣን እያነሰ መሄድ ጀምሯል።

## የአቪኘኖን ጳጳሳት

ጵጵስናን ለማዳከም ቀጥሎ የተወሰደው እርምጃ ጳጳሳትን ከጣሊያን ወደ ፈረንሳይ ማዛወር ነበር። ከ1305-1313 ዓ.ም. ጳጳስ የነበረው ክሌመንት አምስተኛው በመጨረሻ በፈረንሳይ ወደምትገኘው ወደ አቪኘኖን እስኪዛወር ድረስ የንጉስ ፊሊፕ ሥልጣን በጣም ተጭኖት ነበር። ከዚያም ከሰባ ለበለጡ ዓመታት ያህል ጳጳሳት ከጣሊያን ውጪ ኖረዋል። ይህም ለፈረንሳይ ንጉሳዊ አገዛዝ በባርነት ማገልገያ ዘመን ነበር።

የጳጳሳት በሮም አለመኖር ከአስተዳደርም ሆነ ከሃይማኖት አንጻር ለቤተ ክርስቲያን የጉዳት ዘመን ነበር። ጳጳሱ ወደ ሮም እንዲመለስ ለማድረግ ብዙ ጥረቶች ተደረገው በ1377 ዓ.ም. አስራ አንደኛው ግሪጎሪ ከረጅም የግዞት ዘመን በኋላ ተመልሷል።

## "ታላቁ መከፋፈል" — 1378-1417 ዓ.ም.

አስራ አንደኛው ግሪጎር በ1378 ዓ.ም. ሲሞት ስድስተኛው እርባን የተባለው ጣሊያናዊ ጳጳስ ተሹሞ ነበር። በፈረንሳይ ጳጳሳት በአቪኘኖን ይኖር የነበረውን ሰባተኛውን ክሌመንት የተባለውን ፈረንሳዊ ጳጳስ ሾሞውታል። ጥቂት መንግሥታት የሮሙን ጳጳስ ደግፈዋል። ህዝቡ ደህንነታቸው የሐዋሪያው ጴጥሮስ ምትክ የሆነ ጳጳስ በመቀበል ላይ እንደሆነ ያምኑ ነበር፤ ሆኖም ይህ መብት ይገባኛል ብለው የቀረቡት ሁለት

ጳጳሳት ነበሩ። ይህም በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ታላቅ መደናገርና መከፋፈል ፈጥሯል። ሁለቱም ጳጳሳት እርስ በእርስ ተወጋግዘው ግንኙነታቸውን አቋርጠዋል። ይህም ለጳጳስ ይሰጠው የነበረውን ክብር አበላሽቷል።

በ1409 ዓ.ም. ፒሳ በተባለው ሥፍራ የተሰበሰበው ጉባዔ ሁለቱን ጳጳሳት ከሥልጣን አውርዶ አምስተኛውን እስክንድር አዲስ ጳጳሳት አድርጎ ሾሞታል። ይሁን እንጂ ከሁለቱ ጳጳሳ መካከል ማናቸውም የጳጳስና አገልግሎታቸውን ስላልተው የጳጳሳቱ ቁጥር ወደ ሦስት ከፍ ብሏል።

በመጨረሻ በ1417 ዓ.ም. የኮንስታንሱ ጉባዔ ማርቲን አምስተኛው የተባለውን ጣሊያናዊ ጳጳስ ሾሞታል። የቀደሙት ሦስት ጳጳሳት በግጭታቸው ተዳክመው ስለነበር ማርቲንን ደግፈውታል፤ "ታላቁ መከፋፈል" ፈውስ አግኝቶ የምዕራብ አውሮፓ ቤተ ክርስቲያን እንደገና በአንድ መሪ ሥር ሆናለች። ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በታላቁ መከፋፈል ለብዙ ዓመታት ተሰቃይታለች።

<u>ማጠቃለያ</u>

በ1045 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያን ምሥራቃዊ የግሪክና ምዕራባዊ የላቲን ቤተ ክርስቲያን ተብላ ተከፍላ ነበር። በ1073 ዓ.ም. ሒልዴብራንድ ሰባተኛው ግሪጎር ተብሎ ጳጳስ ሆኗል። ፍላጎቱም ሁለቱን አብያተ ክርስቲያናት አዋህዶ በሮም ሥር ዓለማቀፍ ቤተ ክርስቲያን ለመመስረት ነበር። ለኮንስታንቲኖፕል እንኳ ሳይቀር እስላም ቱርኮች ስጋት ፈጥረዋል። የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን የምዕራብን ቤተ ክርስቲያን ዕርዳታ በጠየቀችበት ወቅት ሒልዴብራንድ የመስቀልን ጦርነት ሃሳብ አፍልቋል። ለቅዲስቲቱ አገር ስምንት የመስቀል ጦርነቶች ተደርገዋል፤ ይሁን እንጂ በጦርነቱ ውስጥ የተሳተፉት ሰዎች በተሳሳቱ ዓላማዎች ስለተነሳሱ ሁሉም የተሳካ ውጤት አላስገኙም።

ከ1198-1216 ዓ.ም. በነበረው በሳልሳዊ ኢኖሰንት የጵጵስና ዘመን የሮም ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ከፍተኛው ሥልጣን ጨብጣለች። ከዚያም የጳጳሱን መኖሪያ ሥፍራ በሚመለከት በጣሊያንና በፈረንሳይ መካከል የተፈጠረው "ታላቁ መከፋፈል" ወይም መለያየት እንዲሁም ሁለት ጳጳሳት መመረጣቸው ከጳጳሳቱ ንግግር መራቀቅ ጋር ተዳምሮ የሮምን ቤተ ክርስቲያን አዳክሟታል።

<u>የክለሳ ጥያቄዎች</u>

1. ሒልዴብራንድ ጳጳስ ሲሆን ምን መጠሪያ ተሰጠው?
2. ሒልዴብራንድ በጳጳስነት ይገባኛል ያለው ነገር ምንድን ነው?
3. ሒልዴብራንድ የከለከላቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን ነበሩ?
4. ሒልዴብራንድ በሔንሪ አራተኛው ላይ የተጠቀመው ምን ዓይነት ሥልጣን ነበር?
5. ሒልዴብራንድ ለሔንሪ አራተኛው ይቅርታ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልነበረው ለምንድን ነው?
6. የመሬትን ዝውውር የሚመለከተው ጉዳይ የመጨረሻ መፍትሔ ያገኘው መቼ ነበር?
7. የብሬሺያው አርኖልድ አቋም የወሰደው በምን ላይ ነው?
8. ጳጳስ እስክንድር በሕዝባዊ መንግሥት ላይ የተጎናጸፈው ድል ምንድን ነው?
9. ለቅዲስቲቱ አገር የመስቀል ጦርነት በማድረግ ጳጳስ ሒልዴብራንድ ተስፋ ያደረገው ነገር ምንድን ነው?
10. ሕዝቡ ለመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት እንዲሰለፍ ጳጳስ ዳግማዊ እርባን የተጠቀመባቸው መቀስቀሻዎች ምን ምን ነበሩ?
11. እነዚህ መቀስቀሻዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የትኛውን ስርዓት አስጀመሩ?
12. የመስቀል ጦርነቶች ያልሰመሩት ለምን ነበር?

13.የሮም ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ከፍተኛ ሥልጣኗን የጨበጠችው በየትኛው ጳጳስ ዘመን ነበር?
14.የሮምን ጳጳስ ሥልጣን ያደከመው ምንድን ነው?
15.በሮም ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረው "ታላቁ መከፋፈል" ምን ነበር?
16.በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተፈጥሮ የነበረውን መከፋፈል በማስወገድ አንድነት የመሠረተው ጳጳስ ማን ይባላል?

## ምዕራፍ አስር - በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተቃወሞ መነሳት

በመካከለኛው ዘመን በሮም ቤተ ክርስቲያን እና በመንግሥት መካከል ትልቅ ትግል ነበር። በዚህም ግጭት ቤተ ክርስቲያን መደካከም ጀምራለች። "በታላቁ መከፋፈል" ወቅት የጣሊያንና የፈረንሳይ አብያተ ክርስቲያናት መለያየት ህዝብ በቤተ ክርስቲያን ላይ ዕርካታ የማጣቱ ጅማሬ ነበር።

በሰባተኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ገደማ በአርመኒያና በእስያ ጳውሎሳውያን የተሰኘ አንድ ቡድን የተሰኘ አንድ ቡድን ተነስቶ ነበር። በ10ኛው ምዕተ ዓመት ደግሞ በጎሚላዊያን ወይም ሲተረጎም "የእግዚአብሔር ወዳጆች" የተባለው ሌላ ቡድን በቡልጋሪያና በቦስኒያ ብቅ ብሎ ነበር። በኋላም ካታሪ ወይም "ንጹሐን" የሚል ስያሜ የተሰጠው ቡድንና ሌሎችም ከቦልካናውያን አካባቢ ጸሎተኞች የነበሩት ቤግሐርዳውያን በኔዘርላንድና በሪን ወንዝ አካባቢ ይኖሩ ነበር። በ12ኛውና በ13ኛው ምዕተ ዓመታት አልቢጀንሳውያን በፈረንሳይና ዋልዴንሳዊያን ደግሞ በጣሊያን ቁጥራቸው በዝቶ ነበር።

እነዚህ ሁሉና ሌሎችም ስማቸው ያልተጠቀሱ ብድኖች የሮምን ቤተ ክርስቲያን ስሕተቶች ስለተገነዘቡ እርሷን በመቃወም ሰብከዋል። በርካታ የሆኑ ታማኝ ሰዎችም የሮም ቤተ ክርስቲያን ስሕተቶች ተሰምቷቸው ከእነዚህ ቡድኖች ጋር ተቀላቅለዋል።

እነዚህ ቡድኖች ክርስትናን በጥንት ፋርሳውያን እምነት ሊበርዙት ሞክረዋል ስትል የሮም ቤተ ክርስቲያን አርሮዋን አሰምታለች።

ከእነዚህ ቡድኖች በአንዳንዶቹ ውስጥ የመናፍቃን ትምህርት ቢገኝባቸውም ሁሉም ኑሮአቸውን ለማፅናትና ከሮም ቤተ ክርስቲያን ነፃ ሆነው ለማምለክ ሞክረዋል። መጽሐፍ ቅዱስን የተመረኮዘ ፍጽም ለውጥ ያለው ሕይወትም ሽተዋል፤ እነዚህን ቡድኖች ያወገዟቸው ጳጳሳት በአጠቃላይ አልነበሩም።

በፈረንሳይ የአልቢጃንሳውያን ቁጥር አደጎና ከሁሉም በላይ እጅግ ታዋቂ ሆነው ነበር። በዘመናቸው የነበሩት ካህናት እውነተኛ የእግዚአብሔር ሰዎች ስላልነበሩ ብልሹ አድርገው ይቆጥሯቸውና የአምልኮ ስር ዓቶቻቸውንም ዋጋቢስ እንደሆኑ ይገምቱ ነበር። በእነዚህ ቡድኖች ላይ የተነሳው ስደት ለ20 ዓመታት የቀጠለ ሲሆን ከሞላ ጎደል ሁሉም ደምስሰዋል። ቤተ ክርስቲያን መናፍቅነትን ለመዋጋት በ"መርማሪ ቡድን" ወይም በልዩ ፍርድ ቤት ተጠቅማለች። የሮም ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ቡድኖች ለማጥፋት እርምጃ የወሰደችው በዚህ ልዩ ፍርድ ቤት አማካይነት ነበር። ዶሚኒካውያን የሚፈልጉትን ዕርዳታ ከተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ልዑካን ለማግኘት በዚህ ልዩ ፍርድ ቤት እንዲጠቀሙ ጳጳስ ግሪጎሪ ዘጠነኛ በ1231 ዓ.ም. ፈቃድ ሰጥቷቸዋል። በ14ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ የአልቢጀንሳውያን ቁጥር በጣም ቀንሶ ነበር። ሆኖም ውጫዊ ጭቆና ቢበዙባቸውም ብዙዎቹ ቡድኖች እስከ ተሃድሶ ዘመን ማለትም እስከ ሉተር ዘመን ድረስ ማመናቸውን አላቋረጡም። አብዛኞቹ ትምህርቶቻቸውና ሥነ-ምግባሮቻቸው የተደላደለችው የሮም ቤተ ክርስቲያን ካላት ይልቅ ትክክል ነበሩ።

## በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተነሳ ተቃውሞ

ተቃውሞ የነበረው ከውጭ ብቻ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ደግሞ ነበር። በ1324 ዓ.ም. ማርሴሊዮስ የተባለው ሐኪም ባንድ ፅሑፍ ውስጥ አቻ የለሹ መመዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ገልጿል። የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የበላይ የካህናት እና የምዕመናን ጉባዔ ሊሆን ይገባል፤ የጳጳሳት አገልግሎቶች ሰው የፈጠራቸው ናቸው ብሏል። ካህናት ለሕዝቡ በቀሙ ሕዝባዊ ባለሥልጣናት መመረጥ አለባቸው ብሎ ያምን ነበር። የጳጳሳት ውግዘትም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር መጣጣም ይኖርበታል ብሎ አስተምሯል።

የማርሴሊዮስ ሃሳቦች ጳጳሱን ይቃወሙ በነበሩ ሰዎችና በካህናት መካከል ዕድገት ታይቶባቸዋል።

ሌላው ታላቅ ሰው የአካሙ እንግሊዛዊ ዊሊያም ነበር። ይህ የፓሪስ ዩኒቨርሲቲ ዝነኛ ፈላስፋ በፍራንካውያን ሥርዓት ውስጥ መሪ ቢሆንም ከማርሴሊዮስ ጋር ተመሳሳይ ሃሳቦች ነበሩት። እነዚህን የመሳሰሉት ሰዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያስተማሯቸውን ነገሮች ሳይመረምሩ አሜን ብለው በጭፍን ላለመቀበል የቆረጡ ነበሩ።

## ጆን ዊክሊፍ - 1320-1384 ዓ.ም.

ጆን ዊክሊፍ በዘመኑ በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከነበሩት ታላላቅ ምሁራን አንዱ ነበር። የሮም ቤተ ክርስቲያን ካህን ቢሆንም የቤተ ክርስቲያን ብቸኛ ራስ ክርስቶስ መሆኑን ገልጿል። ሐብትና የአስተዳደር ሥልጣን ቤተ ክርስቲያንን ብልሹ ስላደረጓት ስር ነቀል ተሃድሶ አስፈላጊ ነው ብሏል። ቤተ ክርስቲያን ወዳልተንዛዛ ኑሮና እንዲያውም በሐዋሪያት ዘመን እንደነበረው ወደ ድህነት መመለስ አለባት ሲል ተናግሯል። ከቤተ ክርስቲያን ይልቅ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የእምነት መመሪያ ሊሆን ይገባል ብሎም አውጇል።

በዊክሊፍ ዘመን በአገልግሎት ላይ የነበረው ብቸኛ መጽሐፍ ቅዱስ "ቮልጌት" የተባለው በላቲን ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ነበር። የኢንግላንድ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንዲችሉ ዊክሊፍ ወደ እንግሊዝኛ ተርጉሞታል። በርካታ መጻሕፍትም ደግሞ ጽፏል።

የሮም ቤተ ክርስቲያን የእምነት ጉዳዮችን በሚመለከት እንከን አይገኝበትም የሚለውን አባባል ዊክሊፍ አስተባብሎታል። ዊክሊፍ በቃል ኑዛዜዎቹ ላይ የነበረውን እምነት ፑርጋቶሪን፣ ቅዱስ ጉዞዎቹን፣ ቅዱሳንን ማምለክ ሲነቅፍ የጥንት ቅዱሳንን ቅርስ ማክበር የእግዚአብሔር ቃል ድጋፍ የሌለው መሆኑን ገልጿል።

በርካታ ሰዎች ጳጳሱንና ካህናቱን በማውገዝ የትምህርት ክርስትና መለኪያ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ እንደሆነ ስላመኑ የዊክሊፍ ተከታዮች ቁጥር ጨምሯል። እነዚህም ተከታዮች ሎላርዳውያን ተብለው ተጠርተዋል። ዊክሊፍ ያልተንዛዛ ኑሮ የኖሩና በመላ አገሪቱ ውስጥ ሊሰብኩ የተሰማሩ ቡድኖች አደራጅቷል። ካህናት ሕዝቡን በእግዚአብሔር ቃል ሳያስለጥኑ ትተውት በነበረበት ዘመን እነዚህ ሰባኪያን ቃሉን አስተምረዋል።

ከዚያም የሮም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች መናፍቃን እንዲቃጠሉ የሚያወግዘውን ሕግ ለማውጣት ተሳክቶላቸዋል። ብዙ የዊክሊፍ ትምህርት ተከታዮችም ለእመንታቸው በሰማዕትነት ተቃጥለዋል። ዊክሊፍም በ1384 ዓ.ም. ሞቷል። በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ወንዶችና ሴቶች መነኮሳት የዊክሊፍን ጽሑፎች ተቀብለዋቸዋል። የዊክሊፍ ጠላቶች እርሱን ቢያቃጥሉት ደስታቸው ነበር፤ ሆኖም ፍርድ ቤቱ ከሃይማኖት

ይልቅ አስተዳደር ነክ በሆነ ምክንያት ጠብቀታል፤ ያም ሆነ ይህ ፍርድ ቤቱ የእግዚአብሔር መገልገያ ሆኗል። ይህም ለጳጳሱ ጠላትነታቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነበር። የዊክሊፍ ተከታዮ ራሳችውን ለመደበቅ ቢገደዱም እንኳ እስከ ተሃድሶ ዘመን ድረስ ዘልቀዋል።

## ጆን ሑስ - 1360-1415 ዓ.ም.

ጆን ሑስ ከገበሬ ቤተሰብ ቢወለድም የፐራግ ዩኒቨርሲቲ አለቃ ሆኗል። ከፓሪስና ከኦክስፎርድ ቀጥሎ በአውሮፓ ትልቁ ዩኒቨርሲቲ ይህ ነበር። ሑስ ዳግም ልደት ያገኘና በቦሔሚኛ ቋንቋ ሰባኪ የሆነ ሰው ነበር። የዊክሊፍ ትምህርቶች ጆን ሑስን ስበውታል። በአገሩም ውስጥ የዋልዴንሳውያን ቡድን ቁጥራቸው የበዛ ሲሆን ትምህርቱንም ተቀብለውት ነበር። ከስግብግብነታቸው፣ ከምቾታቸውና ከስንፍናቸው የተነሳ ካህናትን ስለተቃወማቸው መናፍቅ ነው ሲሉ ከሰውታል። መጻሕፍቱም በፐራግ ውስጥ በይፋ ተቃጥለዋል። በኮንስታንሱም ጉባዔ ፊት እንዲቀርብ ጥሪ ተደርጎለታል። የጀርመን ንጉሥ ምንም አይደርስብሕም የሚል ዋስትና ስለሰጠው ወደ ጉባዔው ሄዶ ነበር፤ ይሁን እንጂ እስር ቤት ተጥሎ ጭካኔ የተሞላበት መንገላታት ደርሶበታል። ለፍርድ ሲቀርብ የነበረው መከላከያ ሃሳብ ሳይሰማ በቀድሞ እምነቱ እንዲፀፀት በተፈጠረው ሁካታ ተውጦ ቀርቷል። በ1415 ዓ.ም. ከኮንስታንስ ከተማ ውጭ ተቃጥሎ የሰማዕታት ሞት ሞቷል።

ከጉባዔ ጋር ለጆን ሑስ ሞት ተጠያቂ የነበረው ጳጳስ ጆን ሃያ ሦስተኛው በጣም የከፋ ሰው ነበር። ጉባዔው ሳያበቃ በብዙ ወንጀሎች ተከሶ ሥልጣኑን እንዲለቅ ተገደል።

## ማጠቃለያ

በዚህ ዘመን አካባቢ 1/ ታላቁን መከፋፈል መፈወስ፣ 2/ በቤተ ክርስቲያን ተሃድሶዎችን ማምጣትና 3/ መናፍቅነትን መጨን ሦስት እጥፍ ዓላማ የነበራቸው ሦስት የቤተ ክርስቲያን ጉባዔዎች ተካሂደዋል።

ጉባዔዎቹ በሦስቱም ነጥቦች ላይ የተሳካ ውጤት አላስገኙም። ጆን ሑስ እንዲቃጠል የወሰነው ጉባዔ የጆን ዊክሊፍ ጽሑፎችና በድኑ ከመሬት ተቆፍሮ ወጥቶ እንዲቃጠል ደግሞ ወስኗል።

ከሦስት ለበለጡ መቶ ዓመታት ያህል ቤተ ክርስቲያን ስትቀሰቀስ ኖራለች። በኋላ በ1517 ዓ.ም. የተጀመረው ተሃድሶ የሚደረግበት ወቅት ደርሷል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በመካከለኛው ዘመን በቤተ ክርስቲያን እና በመንግሥት መካከል በተፈጠረው ትግል ሳቢያ ምን ተፈጸመ?
2. የቤተ ክርስቲያን መዳከም ምክንያቶች ምን ምንድን ናቸው?
3. ማርሴሊዮስበቸኛ የእምነት መለኪያ ሊሆን ይገባል ብሎ ያወጀው ምንን ነበር?
4. ጆን ዊክሊፍ ማን ነበር?
5. ዊክሊፍ የእምነት መመሪያ መሆን አለበት ያለው ምንድንነው?
6. ዊክሊፍ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ምን ቋንቋ ተረጎመ?
7. ጆን ሑስ ማን ነበር?
8. ጆን ሑስ ይሰብክ የነበረው በምን ቋንቋ ነው?
9. በዚያ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ሦስት እጥፍ ዓላማ ምን ነበር?

10.የኮንስታንሱ ጉባዔ በጆን ሑስ ላይ ምን ወሰነበት?
11.በጆን ዊክሊፍ ላይስ?
12.በቤተ ክርስቲያን ላይ የተነሳው ተቃውሞ የመጣው ከየት ነበር?

## መልሶች

### ምዕራፍ አንድ

1. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተጀመረው በበዓለ ሐምሳ ዕለት በኢየሩሳሌም ነበር።
2. ከግሪክ ባህል ወጥተው የወንጌል አገልጋዮች የሆኑት የቆጵሮሱ በርናባስና የጠርሴሱ ጳውሎስ ነበሩ።
3. አይሁድ ግዝረት አስፈላጊ ነው ብለው ቢያምኑም ጳውሎስ ይህ ነገር አስፈላጊ አይደለም ብሎ ሲያስተምር በ49 ዓ.ም. ከተሰበሰበው ከኢየሩሳሌም ጉባዔ ድጋፍ ማግኘቱ ነበር።
4. በኔሮ ዘመን በእስራኤል ውስጥ ለተነሱት አመፆች ተጠያቂ የአይሁድ ብሔራዊ የንቅናቄ ቡድን ቀናተኛ አባላት ነበሩ።
5. ኢየሩሳሌም ስትወረር ክርስቲያኖች በዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ ወደምትገኘው ወደ ፔላ ኮብልለው ነበር።
6. ቤተ መቅደሱ ሲደመሰስ የካህናት አገልግሎት ስርዓት ዓምልኮና በዓል ተቋርጧል።
7. ከሐዋሪያት መካከል በመጨረሻ የሞተው ዮሐንስ ሳይሆን አይቀርም፤ ይኸውም በ2ኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ላይ ነበር።
8. የክሌመንት መልዕክት የተጻፈው በ96 ዓ.ም. ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ነበር። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መከፋፈል ከመኖሩም በላይ በሐዋሪያት ምትክ በሥልጣን ላይ የተቀመጡትን መሪዎች አውርደው ነበር።
9. በርናባስ የሙሴን ሕግ በሚመለከት ከእውነት የራቀ ነገር ጽፏል። ሄርሜስ በጥምቀት የኃጢአት ይቅርታ ይገኛል የሚልና ሌሎችም ሕግ ነክ ሃሳቦችን ጽፏል።
10. ኢግናቲዮስ የአንፆኪያ ጳጳስ ነበር፤ ጽሑፎቹም የጳጳስን ስልጣን የሚያጠነክሩ ሲሆኑ መናፍቅነትን ለመዋጋት አይነተኛው መንገድ ጳጳሱን መታዘዝ እንደሆነ ያስተምራሉ።
11. የ2ኛው ምዕተ ዓመት እጅግ ተወዳጅ የቤተ ክርስቲያን አባት ፓሊካርፕ ነበር። የሐዋሪያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር ሲሆን በአንቶኒዮስ ፒዮስ ዘመን ከግንድ ጋር ታስሮ ተቃጥሏል።
12. ፕሊኒን ያስደነቀው የ2ኛው ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች መሐላ ከሌብነት፣ ከዝሙትና እምነታቸውን ከመካድ ለመራቅ ያደርጉት የነበረው መሐላ ነበር።
13. ቋድራቶስና አርስቴደስ የክርስትና እምነት ተሟጋቾችና ጠበቆች ነበሩ።
14. የ2ኛው ምዕተ ዓመት ወደር የለሽ ተሟጋች ጀስቲን ማርቲር ነበር።
15. የጀስቲን ማርቲር የመጀመሪያ መከላከያ ጽሑፍ የተጻፈው ለንጉሡ፣ ለምክር ቤቱና ለመላው ህዝብ ነበር። ሁለተኛው ለምክር ቤቱ ብቻ የተጻፈ ነበር። እጅግ ረጅም የሆነው የጀስቲን ጽሑፍ የተጻፈው ስለ ክርስትና እምነት ለአይሁድ ማብራሪያ ለመስጠት ነበር።

### ምዕራፍ ሁለት

1. በሁለተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ላይ ቤተ ክርስቲያን ያዳከሟት ሁለት የመናፍቅ ትምህርቶች የኖስቲክና የሞንታኒስ ትምህርቶች ነበሩ።

2. የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ዝርዝር ወይም የቤተ ክርስቲያን ጥራዝ ማለት በሮም ግዛት ውስጥ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሁሉ በአምልኮ አገልግሎቶች ወቅት ለመነበብ ተስማሚ በመሆናቸው የተሰበሰቡ መጻሕፍት ማለት ነው።

3. የጥንት ጽሑፎች የሚመዘኑባቸው ሁለት ጥያቄዎች፣

ሀ/ ጸሐፊው ሐዋሪያ ወይስ ከሐዋሪያት ጋር የቀረበ ግኑኝነት የነበረው ሰው ነው?

ለ/ ጽሑፉ ሐዋሪያት ካስተማሩት ዝቅ ያለ የግብረገብ ወይም የትምህርተ ክርስትና ትምህርቶች ያዟል? የሚሉ ነበሩ።

4. የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ወይም ጥራዝ እንዲዘጋጁ ያሰወሰኑት ሦስት ደረጃዎች፡

ሀ/ መለኮታዊ ምሪት

ለ/ በቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ማግኘትና

ሐ/ በይፋ መፅደቅ ነበሩ።

5. የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ወይም ጥራዝ ከመዘጋጀቱ በፊትና ብዙ ያአዲስ ኪዳን ቅጂዎች ባልነበሩበት ወቅት "የእምነት መመሪያ" ወይም የእምነት መግለጫ አስፈልጎ ነበር።

6. በተከታታይ በሥልጣን ላይ የተቀመጡት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥንት ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ላይ ብዙ ነገር ጨምረውበት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በእኩልነት ሊያስቀምጡት ሞክረዋል። ከዚያም እውነተኛ ትውፊት ስላልነበረ ሽክም ብቻ ሊሆን ችሏል።

7. ሽማግሌና ጳጳስ በተሰኙት ቃላት መካከል ምንም መለያ አልነበረም። ሁለቱን ቃላት አንዱን አገልግሎት ለመግለፅ ቀያይሮ መጠቀም ይቻል ነበር።

8. ኢሬኒዮስ የጻፋቸውና እስከአሁን በእጃችን የሚገኙት አምስት መጻህፍት ርዕስ "ፀረ-መናፍቃን" የተሰኘ ነው።

9. የካርቴጁ ሲፐሪያን የሚታወስባቸው ሦስት ነገሮች፡

ሀ/የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከፍተኛ መንፈሳዊ ብቃት እንዲኖራቸው አጥብቆ መናገሩ፣

ለ/ የጌታ እራት መስዋዕት መሆኑን እንዲሁም ሕብስትና ወይኑ ጠጅ ክርስቶስ ሥጋና ደም የሚለወጡ

መሆናቸውን የሚገልፀውን ሃሳብ ማፍለቁና

ሐ/ እያንዳንዱ ጳጳስ በገዛ ቤተ ክርስቲያኑ ተቀናቃኝ የሌለው ሥልጣን እንዳለው ማስተማሩ ናቸው።

ሁለተኛውና ሦስተኛው ነጥቦች ከዚያ ወዲህ በነበሩት ዓመታት ውስጥ ችግሮችን ፈጥረዋል።

10.በ3ኛው ምዕተ ዓመት እስክንድሪያ ዝነኛ የነበረችው በመንፈሳዊ ትምህርት ቤቷ ነበር።

11.በ190 ዓ.ም. የእስክንድሪያ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት መሪ ክሌመንት ነበር። በ203 ዓ.ም. ገደማ የዚህ ት/ቤት መሪ ኦሪጂን ሆኗል።

12.በዚህ ወቅት አቢይ መወያያ የሆነው ነጥብ ኦርጂን ይደግፈው የነበረው የክርስቶስ አምላክነት ሃሳብ ነበር።

13.ኦርጂን የሰው ነፍስ ተደጋግሞ በሥጋ መገለጡና በመጨረሻ ሰው ሁሉ እንደሚድን ያስተማረው ነበር።

14.ኦርጂንን በምቀኝነት ከስልጣን ያወረደው የእስክንድሪያው ጳጳስ ዲሜትሪዮስ ነበር።

<u>ምዕራፍ ሦስት</u>

1. በሦስተኛው ም ዕተ ዓመት እኩሌታ ላይ የቤተ ክርስቲያን ወዳጆች የነበሩትን እስክንድር ሰቨረስና አረባዊው ፊልጶስ ነበሩ።
2. ከ250 እና 260 ዓ.ም መካከል ቤተ ክርስቲያንን ክፉኛ ያሳደዷት ዴሲዮስና ቫለሪያን ነበሩ።
3. ከቫለሪያን የስደት ዘመን በኋላ ቤተ ክርስቲያን ለ10 ዓመታት አርፋለች።
4. የእግዚአብሔር ቤት መቅደስ የሆነው የሰው አካል መንገላታት የለበትም የሚል ነበር።
5. ኮንስታንቲን ቄሳር የሆነው በ306 ዓ.ም. ነበር።
6. ኮንስታንቲን እንደተቀበለው የሚነገርለት ራዕይ "በዚህ ምልክት ድል አድርግ" የሚል ጽሑፍ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈበት በእሳት የሚንበለበል መስቀል በሰማይ ላይ ማየቱ ነበር።
7. የኮንስታንቲን የክርስትና እምነት የተምታታው በክርስትናና "ድል አድራጊው ፀሐይ" በተባለው የአራሚ የፀሐይ አምላክ መካከል ያለውን ልዩነት በግልፅ መለየት ባለመቻሉ ነበር።
8. የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ማስጠበቅ ተግባሩ እንዲሆን ኮንስታንቲን ይሰማው ነበር።
9. ኮንስታንቲን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎችን አዘጋጅቶ በስደት የተደመሰሱትን አብያተ ክርስቲያናትም አሠርቶ ነበር። ለቤተ ክርስቲያን የዕርዳታ ተግባር የሚውል የገጠር የግብር ገቢ ወስኖ ነበር።

10.ኮንስታንቲን በትዕቢት ተነፍቶ ውድ የሆኑ ካባዎችን መልበስ ከመውደዱም በላይ ጥቂት ካባዎችን ለኢየሩሳሌም ጳጳስ ሥጦታ ሰጥቶ ነበር። በቤተ ክርስቲያን ካባ መልበስ የተጀመረው በዚህ ዘመን ነበር።

11.የመንግሥት በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ መግባት የኮንስታንቲን በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ውስጥ ተሳትፎ የማድረጉ ውጤት ነበር። ከእርሱ ድጋፍ የተነሳም ብዙ ካህናት በትዕቢት ተነፍተው ነበር።

12.ሀ/ የሴቶች ሁኔታ እጅግ ተሻሽሏል።
ለ/ በባርነት ሥርዓት ላይ ተፅዕኖ ተደርጓል።
ሐ/ የጌታ ቀን የአምልኮና የዕረፍት ቀን ተደርጓል።

13.የኮንስታንቲን ልጆች የአርዮስን እምነት ይደግፉ ነበር።

14.የኮንስታንቲን ልጆች ዘመዶቹን ስለፈጁበት ጁሊያን ክርስትናን አውግዞ የአራሚን እምነት እንደገና ሊያድስ ሞክሯል።

<u>ምዕራፍ አራት</u>

1. ከ325-500 ዓ.ም. በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የከፋ ውዝግብ የተፈጠረበት ዘመን ነበር። ጥቂቶቹ በሥጋዊ ኃይል ድል ለመቀዳጀት የሞከሩበት ዘመን ነበር።
2. የአርዮስ ተከታዮች ክርስቶስ ፍጡርም ስለሆነ ከአብ ያነሰ ሲሆን ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ሕልውና አልነበረውም ሲሉ አስተምረው ነበር።
3. በሰሜን ምዕራብ ኢሲያ ኒቂያ በተባለችው ከተማ በ324 ዓ.ም. የመጀመሪያውን የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ የሰበሰበው ኮንስታንቲን ነበር።
4. የኒቂያው ጉባዔ የተካፈሉት ከእስፔይን እስከ ፋርስ ካሉት አገሮች ሁሉ የተወጣጡ 318 ጳጳሳት ነበሩ። እነዚህም ለእምነታቸው ሲሉ መከራ የተቀበሉ ሰዎች ነበሩ። እነዚህም ሁሉ በስደት አካለ ስንኩላን የተደረጉ ዓይናቸውን የታወሩና ሰውነታቸውን በእሳት የተጠበሱ ሰዎች ነበሩ።
5. የኒቂያ ጉባዔ ክርክር ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል ነው ወይስ አይደለም የሚል ነበር።
6. ከ220 ድምጾች ውስጥ 218ቱን አግኝቶ ያሸነፈው ክርስቶስን መለኮታዊ ነው ወይም ከአብ ጋር እኩል ነው የሚለው ቡድን ነበር።
7. በኒቂያ ጉባዔ የክርስቶስን አምላክነት ይደግፍ የነበረው ዋና ተሟጋች የእስክንድሪያው ዲያቆን አትናቴዎስ ነበር። አትናቴዎስ አምስት ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ተገልሎ እንደገና ተመልሷል።
8. አርዮስ እንደገና ተወዳጅ ለመሆን ብዙ ዱለታ አድርጓል።
9. የአርዮስን ትምህርት ለማስፋፋትና አያሌ ጳጳሳትን ከሥልጣናቸው ለማወረድ ኦሲቪዩስ በብዙ ዘዴዎች ተጠቅሟል።
10. የሮሙ ጳጳስ አትናቴዎስንና ማርሴሉስን በስደተኛ ስም ተቀብሎ ከኅብረቱ ጋር ቀላቅሏቸው ነበር፤ ይህም በምሥራቅና በምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት መካከል መለያየት ፈጥሯል።
11. የሮሙ ቄሳር ኮንስታንቲዮስ የአርዮስን ትምህርት የደገፈው ከአስተዳደር አንጻር ለግዛቱ ደህንነት ተስማሚ መስሎ ስለታየው ነበር።
12. በ361 እና በ381 ዓ.ም. መካከል ሰላሴና የክርስቶስን ማንነት በሚመለከት አዳዲስ ውዝግቦች በቤተ ክርስቲያን ተፈጥረዋል።
13. በኮንስታንቲኖፕል የተደረገውን ሁለተኛ የቤተ ክርስቲያን ጉባዔ በ381 ዓ.ም. የሰበሰበው የሮሙ ቄሳር ቴኦዶሲዮስ ነበር።
14. እንደገና በኮንስታንቲኖፕል ጉባዔ የጸደቀው "ክርስቶስ በባህርይ ከአብ ጋር አንድ ነው" የሚለው የኒቂያው የእምነት መግለጫ ነበር።
15. የኮንስታንትኖፕል ጉባዔ-
"መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር አብሮ ይመለካል፣ ይወደሳል" ብሏል።

16. ከፍተኛ ውዝግብ ያስነሳው መግለጫ "ኮንስታንቲኖፐል አዲሷ ሮም ስለሆነች ከሮም ጳጳስ ቀጥሎ ያለው ሥልጣን ለኮንስታንትኖፐል ጳጳስ ሊሰጠው ይገባል" የሚለው ነበር።
17. የኮንስታንትኖፐሉ ጉባዔ የፈጠረው ጥያቄ - "ክርስቶስ ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው ከሆነ ሁለቱ ተፈጥሮዎች በአንድ አካል ውስጥ የሚጣመሩት እንዴት ነው?" የሚል ነበር።
18. ኔስቶሪዮስ ጥያቄውን ለመመለስ ክርስቶስ ሰባዓዊና መለኮታዊ የሆኑ ሁለት የተለያዩ ባህሪያት ነበሩት፤ መለኮታዊውም ባህሪይ የክርስቶስን መከራ አልተካፈለም ሲል ተናገሯል።
19. ጳጳስ ሲሪል የጠቀመው የኔስቶሪዮስ መልስ ትርጉም ኃጢአተኛ በአንድ ሰው መከራ ይድናል ማለት እንደሆነ ነበር። ይሁን እንጂ የአንድ ሰው መከራ ሰውን ሊያድን እንደማይችል በትክክል አመልክቷል።
20. የኤፌሶኑን ጉባዔ የሰበሰበው የሮሙ ቄሳር ዳግማዊ ቴኦዲሲዮስ ነበር።
21. ካህናት ማግባት የለባቸውም፣ የኢየሱስ እናት ማሪያም ምን ጊዜም ድንግልና "የእግዚአብሔር እናት ናት" የሚል ነበር።
22. የኔስቶሪየስ ተከታዮች ቤተ ክርስቲያን አሁንም በፋርስ ይገኛል።
23. የክርስቶስን ሁለት ተፈጥሮዎች በሚመለከት የቀልሴዶኑ ጉባዔ የሰጠው ውሳኔ ክርስቶስ በእርግጥ አምላክና በእውነት ሰው መሆኑና ሁለቱም ተፈጥሮዎች መደባለቅ፣ ለውጥና ልዩነት ሳይኖር እንዲሁም ማንነቱ ሳይከፋፈል መጣመራቸውን ነበር።
24. አዎን። በአሁኑ ዘመን የክርስቶስ ማንነት ተከፋፍሏል ብለው የሚያስተምሩት የሶሪያዎቹ ያዕቆባዊያንና ምናልባትም የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ናቸው። ይህንን ትምህርት በመጀመሪያ ያስተማረው ኦቲችስ ነበር።
25. የፖንቲየርሱ ሒላሪ የደገፈው የኒቂያውን የእምነት መግለጫ ነበር።
26. አምብሮስ - "ንጉሥ የቤተ ክርስቲያን አካል እንጂ ራስ አይደለም" በማለት አስተምሯል።
27. የአውግስቲን አቢይ ትምህርት የእግዚአብሔር ፀጋ ነበር።
28. አውግሲቲን ከሮም ቤተ ክርስቲያን ውጭ ደህንነት እንደሌለና ሙታን በመከራ ውስጥ ሊነፁ ይችላሉ የሚለውን ትምህርት ወይም ፑርጋቶሪን አስተምሯል።
29. ሦስቱ የቂጳዶቀያ ሰዎች፡ የቂሳሪያው ጳጳስ ታላቁ ባሲል የኒሲያው ጳጳስ ወንድሙ ግሪጎርና የናዚያዙስ ጳጳስ ወዳጃቸው ግሪጎር ነበሩ። የኒቂያውን የእምነት መግለጫ በመደገፍ በድፍረት ቆመዋል።
30. ጆን ክሪሶስቶም በመጀመሪያ የአንፆኪያ በኋላም የኮንስታንቲኖፐል አብያተ ክርስቲያናት ጳጳስ ነበር። ስሙ ሲተረጎም "ዮሐንስ አፈወርቅ" ማለት ነው። ንግሥት ኦዶክሲያን ያስቀየማት ስለ ንስሐ ያቀረበው ትምህርት ሲሆን በ403 ዓ.ም. ከሥልጣኑ ወርዶ ታስሯል።
31. ጀሮም በተለይ የሚታወቀው "ቮልጌት" የተባለውን ያላቲን ቅጂ መጽሐፍ ቅዱስ በማዘጋጀት ነበር።
32. ታላቁ ሌዮ ማቴ 16፥18ን የተረጎመው- "ጴጥሮስ የዓለማቀፍ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያ ጳጳስ ነበር" በማለት ነበር።
33. በአምስተኛው ምዕተ ዓመት የሮማውያን ግዛት መውደቁ ነበር።
34. ምቾትን በማፍቀር ብዙው የገጠር ህዝብ ወደ ከተሞች ኮብልሎ ነበር። ይህም የገጠሩን ህዝብ ብዛት ስላሳሳው ለሰሜን ጎሳዎች መግቢያ በር አዘጋጅቶላቸዋል።
35. የምዕራብ እንግሊዝና የአየርላንድ ቤተ ክርስቲያን በምሥራቅ የአራሚ ጎሳዎች አማካይነት ከአውሮፓ ተገንጥላ ስለነበር በዚያ ዘመን በአውሮፓ ከደረሰው መንፈሳዊ ውድቀት ድናለች።
36. የጀርመን ወረራዎች ንጉሥ የነበረው ክሎቪስ ከ3000 ወታደሮቹ ጋር ተጠምቆ ነበር፤ ይህም የወራሪዎቹን ስህተቶችና አጉል እመንቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማግባት እንድትዳከም አድርጓታል።
37. ጀሮም ከእስራኤል የኮበለሉትን ሮማውያን መሳፍንትና ቤተሰቦቻቸውን ስላስጠጋቸው በሮም ጳጳስ ዘንድ ተወዳጅነቱ አድጓል።

## ምዕራፍ አምስት

1. የሮም ግዛት በ476 ዓ.ም. ወደቀ።
2. ክርስትናን በመጀመሪያ የተቀበሉት የጀርመን ጎሳዎች ፍራንካውያን ነበሩ።
3. የምዕራብ ጉትሉ ሪካርድ የእስፔይን ንጉሥ ነበር።
4. ግሪጎር ሮምን ከሎምባርዳውያን አድኗታል።
5. ግሪጎር የእግዚአብሔርን ጥሪ ሲሰማ መሬቱን ሸጦ ገንዘቡን ለድሃ መርጃና በሲሲሊ ውስጥ ለስድስት ገዳማት ማሰሪያ እንዲውል አድርጓል።
6. የሮምን ጳጳስ ሥልጣን ለማጽናት የረዳው የግሪጎር ችሎታ በበርካታ አገሮች ውስጥ የነበሩትን የቤተ ክህነት እርስቶች የመቆጣጣር ችሎታው ነበር።
7. ቀዳማዊ ሌዮና ቀዳማዊ ግሪጎር ያስፋፉት ትምህርት የሮም ጳጳስ የኮንስታንቲኖፕልና የእስክንድሪያ ጳጳሳት የበላይ ነው የሚለው ነበር።
8. "የጳጳስ ቁንጮ" የመሆንን ሃሳብ የተቃወመችው የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ነበረች።
9. አንግላውያንንና ሳክሶናውያንን ወደ ክርስትና እንዲያመጣ ግሪጎር አውግስቲን የተባለውን መነኩሴ ወደ እንግሊዝ ልኮታል።
10. በአውግስቲን የተመሠረተው የእንግሊዝ ዝናኛ ደብር የካንተርበሪ ደብር ተብሎ ይጠራል።
11. በ604 ዓ.ም. ሚሊተስ የቅዱስ ጳውሎስን ቤተ ክርስቲያን ካቋቋመ በኋላ በለንደን የመጀመሪያው ጳጳስ ሆኗል።
12. ከሮም ቤተ ክርስቲያን ጋር አልቀላቀልም ያለችው የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ነበረች።
13. በ532 ዓ.ም. ወንጌልን ወደ አየርላንድ የወሰደው ፓትሪክ ነበር።
14. የአየርላንድ መነኮሳት ለወንጌል አገልግሎት ወደ ጀርመን፣ ስዊዘርላንድ፣ ሐንጋሪና ጣሊያን ሄደዋል።
15. በ664 ዓ.ም. በሰሜን እምብሪያ በተካሔደው ስብሰባ የሮም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአየርላንድ መነኮሳትን ስለረቷቸው ወደ ስሜን ሊሄዱ ተገደዋል።
16. አየርላንድ ራሷን በጳጳሱ ሥር ለማስተዳደር ፍቃደኛ ስትሆን የሴልቲክ ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት እየቀነሰ መምጣት በመጀመሩ ነው።
17. ጳጳሱ ትሁት መጋቢ መሆኑ ቀርቶ በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ላይ አምባገነን የበላይ ስለሆነ ነበር።
18. የጌታ እራት በመታሰቢያነት ፋንታ መስዋዕት ሆኖ ነበር።
19. የሙታን በእሳት የመንፃት ሃሳብ የመጣው ከአላማኒያን ሃይማኖቶች ነበር።
20. ኃጢአትን መናዘዝ ከቤተ ክርስቲያን ጅማሬ ወቅት አንስቶ አስፈላጊ ነበር። የሲልቲክ ቤተ ክርስቲያን ሰባኪዎች መጥፎ ሥነ-ምግባሮች ሰላጋጠሟቸው ሰዎች በግላቸው ቀርበው እንዲናዘዙና ትምህርት እንዲሰጣቸው መገፋፋት ጀምረዋል።
21. ክርስቲያኖች በምስሎች ሰላመለኩ ጣዖት አምላኪ ናቸው ብለው እስላሞች ከሰዋቸዋል።
22. ለካህናት መናዘዝና ለካህናት የአገልግሎት ሥፍራ ተደርጎ መሰዊያ መዘጋጀት ሲጀምር የአማኞቹ ሁሉ ካህንነት ተዘንግቷል።
23. ካህናት ልዩ ልብሶች መልበስ የጀመሩት ኮንስታንቲን ለጳጳሱ ውድ የሆኑ ካባዎች በስጦታ ካቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ነበር።
24. ዕጣን ለመጀመሪያ ጊዜ በአገልግሎት ላይ የዋለው አብያተ ክርስቲያናትን ለማጠን ተግባር ነበር።

## ምዕራፍ ስድስት

1. ቆላ 2፡33ን ተመልከቱ።
2. በ251 ዓ.ም. በግብፅ ውስጥ የምነናን ኑሮ ከጀመሩት ገዳም ካቋቋሙት ሰዎች መካካል አንዱ ቅዱስ አንቶኒ ነበር።
3. ፐቾሚዮስ ገዳም የመሠረተው በላይኛው ግብፅ በአባይ ወንዝ ውስጥ በምትገኘው ደሴት ላይ ነበር።

4. የገዳም ሥርዓትን ይደግፉ የነበሩት አራት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አትናቴዎስ ጀሮም አምብሮስና አውግስቲን ነበሩ።
5. በእስኮትላንድ ውስጥ ዊትሆርን በተባለው ሥፍራ ገዳም የመሠረተው ሰው ኒኒያን ይባላል፤ ይኸውም በ397 ዓ.ም. ነበር።
6. የቤኒዲክታውያን ማሕበር በ529 ዓ.ም. በጣሊያን ተመሰረተ።
7. ቤርኖን የተባለው ሰው በ910 ዓ.ም. የክሊኒን ማህበር በፈረንሳይ አገር ክሉኒ በተባለው ሥፍራ አቋቋመ።
8. በርኖን አዲስ ሥርዓት እንዲያቋቁም ያነሳሰው የቤኒዲክታውያንን ማሕበር ብልሹነት መረዳቱና መቃወም መፈለጉ ነበር።
9. የሲስቴርሳዊያን ማሕበር የተመሠረተው ጥብቅ የሆነውን የቤንደክታዊያንን የውስጥ ደንብ ማክበር ፍላጎት ባላቸው ሰዎች ነበር።
10. የሲስቴርሳውያንን በርናርድ በተለይ የሚታወሰው በመዝሙሮቹ አማካይነት ነው።
11. የፍራንሲስና የዶሚኒክ ሥርዓቶች ትሕትና የተሞሉና የሰውን ሙብት የማይጋፉ ስለሆኑና በሰዎችም ዘንድ ተቀባይነት ስላገኙ ነበር።
12. ዶሚንክ የእስፔይን መስፍን ነበር። የአልቢጀንሳውያንን የሐሰት ትምህርት በመቃወም አስተምሯል።
13. የወታደራዊ ማሕበሮች ዓላማ መናኞችን መንከባከብ ነበር።
14. ከጊዜ በኋላ ሃይማኖታዊ ማሕበሮች ሁሉ ብልሹ ሆነዋል።
15. ሃይማኖታዊ ማሕበሮች ትምህርት ቤቶችን ከፍተዋል፤ እርሻን አስፋፍተዋል፤ ለድሆች እንክብካቤ አድርገዋል እንዲሁም ለበሽተኞች ለተቸገሩ መስተንግዶ አድርገዋል።

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

1. ታላቁ ግሪጎሪ በጽሑፎች አማካይነት የጥንቱን ዓለም ጥበብ ወደ መካከለኛው ዓለም ማስተላልፍ ችሏል።
2. ቻርለማኝ ሀ/ ለሕግና ለሥርዓት ለ/ ለሥልጣኔና ለባህል እንዲሁም 3/ ለክርስትና ሽንጡን ገትሮ ቆሟል።
3. ቻርለማኝ ድል ለማግኘት ሰዎችን መግደሉ በግድ ማሳመኑና ካገር ማስወጣቱ ነበር።
4. ቢዘንታይን ወይም ምሥራቃዊ የሮም ግዛት ቻርለማኝ የመሠረተው የፍራንካውያን ግዛትና የመሐመድ ተከታዮች የአረቦች ግዛት በ814 ዓ.ም. ታላላቅ ግዛቶች ነበሩ፤ ይህም ቻርለማኝ የሞተበት ዓመት ነበር።
5. መሐመድ በአረቢያ ውስጥ መካ በተባለው ሥፍራ በ570 ዓ.ም. ተወለደ።
6. መሐመድ ያውቃቸው የነበሩትን ክርስቲያኖች አኗኗር ይጠላ ነበር።
7. መሐመድ ብዙዎቹን የአረቢያ አምላኮች አልወደዳቸውም። ስለ ክርስትና አንድ አምላክ ሰምቶ ነበር።
8. መሐመድ ተቀብልኳቸው ብሎ የጻፋቸውን መለኮታዊ መገለጦች አግኝቻቸዋለሁ ያለው ከመልአኩ ገብርኤል ነበር።
9. እስልምና በዘጠና ዓመታት ውስጥ ከህንድ እስከ አትላንቲክ ውቅያኖስና በመካከለኛውና በደቡብ እሲያ እንዲሁም በቻይና ተሰራጭቷል።
10. የፍሬሺያን አካባቢ በወንጌል ያዳረሰው እንግሊዛዊ መነኩሴ ዊልብሮድ ይባላል።
11. "የጀርመን ሐዋሪያ" ተብሎ ይጠራ የነበረው እንግሊዛዊ መነኩሴ ቦኒፌስ ይባላል።
12. ሳክሶናውያን ክርስትናን የጠሉት በጠላቶቻቸው በፍራንካዊያን በኩል ስለመጣላቸው ነበር።
13. በሎምባርዳውያን አማካይነት በፍራንካውያን ላይ የመጣባቸው ዛቻ ቤተ ክርስቲያን እና መንግሥት ለዕርዳታ እንዲፈላለጉ አድረጓቸዋል።

14.ብዙዎች የቤተ ክርስቲያንን እና የመንግሥትን መጣመር ይቃወሙ ስለነበር ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ግጭት አስከትሏል።
15.የቻርለማኝ ዘመነ መንግሥት በርካታ ትምህርት ቤቶችንና መልካም ሕግጋት ለግዛቱ አስገኝቷል።
16.ስዕሎች ምስሎች ለመጀመሪያ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ሊገቡ የቻሉት ለውበታቸውና ያልተማሩ ሰዎችን ለማስተማሪያ ነበር።
17.ሥዕሎችና ምስሎች ከአብያተ ክርስቲያናት እንዲወገዱ ያዘዘው ንጉሥ ሳልሳዊ ሌዮ ነበር።
18.የምስል አምልኮ "የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን አራሚና ፀረ ክርስቲያን ልማድ" ብሎ የጠራው ንጉሥ አምስተኛው ኮንስታንቲን ነበር።
19.ምስሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖር አለባቸው ሲል የወሰነው ሁለተኛው የኒቂያ ጉባዔ ነበር።
20.ቻርለማኝ "ሊመለክ የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ቅዱሳን ሊከብሩ ብቻ ይገባል። ምስሎች በምንም ዓይነት መመለክ የለባቸውም" ሲል ተናግሯል።

## ምዕራፍ ስምንት

1. አንዳንድ ካህናት የጳጳሳትን ስልጣን ለማጠናከር የተጠቀሙባቸው ዘዴዎች የሐሰት ሰነዶችን ማዘጋጀት ነበር።
2. የሐሰት ትምህርት ጽፈዋል ተብለው የተጠረጠሩት ሁለት ሰዎች በእስፔን የሲቪል ነዋሪ የነበረው ኢሲዶርና ኮንስታንቲን ነበሩ።
3. ቀዳማዊ ኒኮላስ "የጳጳሱን ውሳኔ ሁሉ ማክበር አለበት" ብሏል።
4. ብልሹነትና የችሎታ ማነስ የቻርለማኝ ግዛት በ887 ዓ.ም. እንዲወድቅ አድርጓል።
5. በጣሊያን መኳንንት ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ላይ ብዙ መከራ ደርሶባታል።
6. 12ኛው ጆን ዕርዳታ የጠየቀው የጀርመኑን ንጉሥ ቀዳማዊ ኦቶን ነበር።
7. ቀዳማዊ ኦቶ 12ኛውን ጆንን ከስልጣን በማውረድ አዲስ ግዛት መሥርቷል። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያን ነፃነቷን አጥታለች።
8. ከሰሜን ኖርስሜኖች ከደቡብ የእስላም ሠራዊትና ከምሥራቅ ደግሞ የሐንጋሪ ማጊያራውያን ነበሩ።
9. ዘጠነኛው ቢነዲክት፣ ሳልሳዊ ሲልቬስትሪና ስድስተኛው ግሪጎር በ1044ና 1046 ዓ.ም. መካከል ጳጳስ ነን ባዮች ነበሩ።
10.በሮም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሃድሶ ያስደረገው ሒልዴብራንድ የተባለው መነኩሴ ነበር።
11.እስካንዲኒቪያውያን ክርስትናን የተቀበሉት በ11ኛው ምዕተ ዓመት ነበር።
12.የቼኮዝላቫኪያ ሕዝብ ክርስትናን የተቃወመው በጀርመን ሕዝብ በኩል ስለመጣለት ነበር።
13.ወንጌልን ወደ ሩሲያ የወሰደችው የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ነበረች።
14.የሰም ክርስትናን እንኳ ያልተቀበሉት ሁለት የአውሮፓ አገሮች ፊንላንድና ላፕላንድ ብቻ ነበሩ።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

1. ሒልዴብራንድ ጳጳስ ሲሆን ሰባተኛው ግሪጎር ተብሏል።
2. ሒልዴብራንድ የክርስቶስ እንደራሴና የጴጥሮስ ተወካይ እንደመሆኑ መጠን ግዛቶቹን መንግሥታትንና የሰው ሁሉን ንብረት ልወስድ ይገባኛል ብሎ ነበር።
3. ሒልዴብራንድ የሮም ቤተ ክርስቲያን ካህናት ጨርሶ እንዳያገቡ ከልክሏል። ለክህነት አገልግሎት እጩ ተወዳዳሪነት የሚከፈለውን ገንዘብ አስቀርቷል።
4. ሒልዴብራንድ የመሬትን ባለቤትነትን ሕግ ተቃውሞ ከንጉሥ ሔንሪ አራተኛው ጋር የነበረውን ግንኙነት አቋርጧል።
5. ይቅርታ ማድረግ ለሔንሪ አራተኛው መንግስቱን ያድስለት ስለነበር ሒልዴብራንድ ፈቃደኛ አልነበረም።

6. "የወርምስ ኮንኮርዳት" የተሰኘው ስምምነት የመሬት ዝውውርን በሚመለከት ለነበረው ግጭት የመጨረሻ መፍትሔ ሰጥቶቷል።
7. የብሬሺያው አርኖርድ አቋም የወሰደው ቤተ ክርስቲያን ወደ ቀላሉ ያልተንዛዛ የአዲስ ኪዳን ኑሮ እንድትመለስ ነበር።
8. ፍሬደሪክ በሎምባርዳውያን ማሕበር ሲሸነፍ ራሱን ለጳጳስ አሰክንድር አስገዝቷል። ይህም ቤተ ክርስቲያን በመንግሥት ላይ ለተጎናጸፈችው የበላይነት ሥልጣን ተጨማሪ ድል ነበር።
9. ጳጳስ ሔልዴብራንድ ተሰፋ ያደረገው የምስራቅና የምዕራብን አብያተ ክርስቲያናት አዋህዶ የሮም ጵጵስናን ዓለምቀፍ ሥልጣን ለማስጨበጥ ነበር።
10. የመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት መቀስቀሻዎች ከማናቸውም ኃጢአት መንጻትን በኃጢአት የወደቁ ሰዎች ዘላለማዊ በረከት ማግኘትን ከዕዳ ነፃ መሆንን የወንጀለኞች ይቅር መባልንና በመንገዳቸው ላይ የሚረዳቸው ተዓምራት መደረግን በሚመለከት የተሰፋ ቃሎች መስጠታቸው ነበር።
11. ወደ መስቀሉ ጦርነቶች ለሚዘምቱ ሰዎች ካደረጋቸው ተስፋዎች የተነሣ የተጀመረው የኃጢአት ይቅርታ በገንዘብ የመግዛት ስርዓት ነው።
12. በመስቀል ጦርነቶች ውስጥ የተሳተፉት ሰዎች የተነሡባቸው ዓላማዎች የተሳሳቱ ነበሩ። ከሃይማኖትም ይልቅ አስተዳደርና ኅብረተሰብ ነክ ነበሩ።
13. የሮም ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻ ከፍተኛ ሥልጣኗን የጨበጠችው በጳጳስ ዳግማዊ ኢኖሰንት ዘመን ነበር።
14. የጳጳሳት ማናለብኝነት የጎሳ መሪዎች ቁጥር ማደግ፣ የጳጳሱን መቀመጫ ሥፍራ በሚመለከት በጣሊያንና በሮም መካከል የተፈጠረው መከፋፈልና ግጭት ሁሉም ለሮም ቤተ ክርስቲያን መዳከም የበኩላቸውን አስተዋፅዖ አድርገዋል።
15. በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረው "የታላቁ መከፋፈል" መንስኤ በጣሊያንና በፈረንሳይ የሚቀመጡ ሁለት ጳጳሳት በመሾማቸው ነበር። በኋላም ሦስተኛ ጳጳስ የተመረጠ ሲሆን የቀደሙት ሁለት ጳጳሳት ሥልጣናችንን አንለቅም ብለዋል።
16. በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለተፈጠረው መከፋፈል የመጨረሻ መፍትሔ የተገኘው የጣሊያኑ አምስተኛው ማርቲን ጳጳስ እንዲሆን በተሾሙበት ወቅት ነበር።

<u>ምዕራፍ አስር</u>

1. በቤተ ክርስቲያን እና በመንግሥት መካከል በተፈጠረው ሽኩቻ ሳቢያ ቤተ ክርስቲያን ተዳክማች።
2. የቤተ ክርስቲያን መዳከም ምክንያቶች፤
   - "ታላቁ መከፋፈል"
   - የቤተ ክርስቲያንን ተሃድሶ ይጠባበቁ የነበሩት በርካታ ቡድኖች
   - በሮም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረው ተቃውሞና
   - የማርሲሊዮስ፣ የኦካሙ ዊልያም፣ የዊክሊፍና የሁሉ ትምህርቶች ነበሩ
3. ማርሲሊዮስ የእምነት መለኪያ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሊሆን ይገባል ብሏል።
4. ጆን ዊክሊፍ የሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ካህንና የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ምሁር ነበር።
5. ዊክሊፍ መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ ቤተ ክርስቲያን የእምነት መመሪያ ልትሆን አይገባም ብሏል።
6. ዊክሊፍ የላቲኑን መጽሐፍ ቅዱስ ወደ እንግሊዘኛ ተርጉሟል።
7. ጆን ሑስ የፕራግ ዩኒቨርሲቲ አለቃ ነበር።
8. ጆን ሑስ ይሰብክ የነበረው በቦሔሚኛ ቋንቋ ነበር።
9. የቤተ ክርስቲያን ጉባኤዎች ሦስት እጥፍ ዓላማ
   ሀ. ታላቁን መከፋፈል መፈወስ
   ለ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሃድሶ ማምጣትና
   ሐ/ መናፍቅነትን ማውገዝ ነበሩ።

10. ጆን ሑስ በእሳት እንዲቃጠል ተደረገ።
11. የዊክሊፍ ጽሑፎች እንዲደመሰሱና አፅሙ ከመሬት ተቆፍሮ ወጥቶ እንዲቃጠል ጉባዔው ውሰኗል።
12. በቤተ ክርስቲያን ላይ ተቃውሞ የተነሳው ከውጭም ከውስጥም ነበር።